# የቤ/ጉ/ክ/ጠ/ሚ/ቤት

# ኮሚሽን

# የ5 ዓመት

# ስትራቴጂክ ዕቅድ

## ረቂቅ ሰነድ

ሐምሌ 2012 ዓ.ም

አሶሳ

# ማዉጫ


ማዉጫ ........ i
ሀ. መግቢያ ........ iii
ለ. የስትራቴጂክ ዕቅድ አስፈላጊነት ........ 1
ሐ. የስትራቴጂክ ዕቅድ ዓላማዎች ........ 1
መ. የዕቅድ ወሰን ........ 1
ሰ. የስትራቴጂክ ዕቅድ የተዘጋጀበት ሂደት ........ 2
1. ክፍል-አንድ ........ 3
1.1. የ2ኛ ዙር የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የዕቅድ ትግበራ ዘመን አፈፃፀም ግምገማ ........ 3
1.2. በስትራቲጂክ ዕቅድ ዘመኑ ኮሚሽኑ ካከናወናቸው ተግባራት መካከል የስኬት ........ 10
ምንጭ የሆኑ ስራዎች፡- ........ 10
1.3. በስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመን የነበሩ ጠንካራና ደካማጎኖች ........ 11
1.3.1. ጠንካራ ጎን፡- ........ 11
1.3.2. ደካማጎኖች፡- ........ 11
1.4. የማ/ቤቶች ኮሚሽን የተገልጋይ ፤ የባለድርሻ ፤ የአጋር እና ተባባሪ አካላት ፍላጎት ትንተና ........ 13
1.4.1. የተገልጋይ አካላት ፍላጎት ትንተና፡- ........ 13
1.4.2. የባለድርሻ አካላት ፍላጎት ትንተና ........ 15
1.4.3. የተባባሪ አካላት ትንተና ........ 20
1.5. የተቋሙ ጥንካሬ ፣ ድክመት ፣ መልካም አጋጣሚና ስጋቶች ትንተና፤ ........ 21
1.5.1. የጥንካሬና ድክመት መግለጫዎች፡- ........ 21
1.5.2. የመልካም አጋጣሚና ሥጋት መግለጫዎች ........ 25
1.6. አስቻይና ፈታኝ ሁኔታዎች፣ ........ 27
1.6.1. አስቻይ ሁኔታ፡- ........ 27
1.6.2. ፈታኝ ሁኔታዎች፡- ........ 28
2. ክፍል-ሁለት ........ 29
2.1. የኮሚሽኑ ራዕይ ፣ ተልዕኮ ፣ እሴት እና ስልጣንና ተግባር ........ 29
2.1.1. የኮሚሽኑ ራዕይ፡- ........ 29
2.1.2. ተልዕኮ፡- ........ 29
2.1.3. ........ 29

2.2. የኮሚሽኑ ስልጣንና ተግባር 30
2.3. የክልል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን የስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮችና ዋና ዋና ግቦች 31
2.3.1. ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች 31
2.3.1.1. ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮችና ውጤቶች 31
2.3.1.2. ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች መግለጫ 32
2.4. ስትራቴጂያዊ ግቦች 34
2.4.1. ለሁሉም ተቋማዊ ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች የተጠቃለሉ ግቦች በእያንዳንዱ እይታ እንደሚከተለው ተካተዋል 34
2.4.2. ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች ለማሳካት የተጣሉ ግቦች 36
2.5. የተጠቃለሉ የስትራቴጂካዊ ግቦች 38
2.5.1. የተጠቃለል የስትራቴጀክ ግቦች ማፕ 39
2.5.2. የግቦች መግለጫ 40
2.7. ግቦች መለኪያዎችና ተደራሽ ኢላማዎች፡- 55
2.8. ስትራቴጂክ ግቦችን ለማሳካት ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች 60
2.9. በልማትፕላኑ ዘመኑ 2013 -2017 ዓ.ም በካፒታል ፕሮጅክት የሚሰሩ ስራዎችና ለስራው የሚያስፈልግው የበጀት ግምት 61
2.10. የልማት ፕላን የሠው ኃይል ፍላጎት በትምህርት ደረጃ /በሙያ መስክ 63
3. ክፍል-ሦስት 64
3.1. የክትትል ፣ ግምገማና ግብረ- መልስ ሥርዓት 64
3.1.1. ስትራቴጂውን በማስተዋወቅ ወደ ትግበራ መግባት 64
3.1.2. በዳይሬክቶሬት ደረጃ የሚደረግ የክትትል ድጋፍና ግምገማ አግባብ፣ 64
3.1.3. የመስክ ክትትልና ግምገማ 65
3.2. በስትራቴጂክ ዘመኑ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና 66
3.2.1. ለችግሮቹ የተቀመጡ የመፍተሄ ሀሳቦች 66
3.2.1.1. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች፡- 66
3.2.1.2. ለችግሮቹ የተቀመጡ የመፍተሄ ሀሳቦች፡- 66

## ሀ. መግቢያ

ሀገርቱ የሰላም ፤የልማትና የዲሞክራሲ ግንባታ ሂደቶችን በማጠናከርና ጠንካራ የማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ መሰረቶችን በመገንባት ከድህነትና ኃላቀርነት ተላቃ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ መሰለፍ የሚያሰችሉ ሀገራዊ ፖሊሲና ስትራቴጂክ ቀርፆ ዓለማውን ለማሳካትም ላለፉት ሁለት ዘመናት (2003-2007 / 2008-2012) በሀገር፤በክልልና በተቋማት ደረጃ የስትራቴጂክ ዕቅድ ተዘጋጅቶ በከፍተኛ ትኩረት ተግባራዊ ስደረጉ ቆይቷል፡፡

የቤ/ጉ/ክ/መ/ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽንም አገራዊና ክልላዊ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽ ዕቅዱ ለፍትህ ዘርፉ ተቋማት ከተቀመጡ የትኩረት አቅጣጫና ከተቋሙ ተግባርና ኃላፊነት መነሻ ተቋማዊ ሠላምና ደህንነት በማረጋገጥ የታራሚዎች አያያዝ ፣ አስተዳደር ፣ የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ፣ የማረም ማነፅ /ተሃድሶ ግንባታ/ ማረም ማነፅ /ተልዕኮን መፈፀም የሚያስችል ስትራቴጂካዊ የትኩረት አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ የዘርፉን ስራ ተግባራዊ ተደረጓል፡፡ ኮሚሽኑ በስትራቴጂክ ትግባራ ዘመን በሀገር ፣በክልላዊ ደረጃ የተጀመረ የሪፎርም ትግበራ ስርዓትን በተቋም ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ በ2010 በጀት ዓመት የሪፎርም ስራውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ተቋማዊ አቅጣጫ በማስቀመጥ በተቋሙ የሚስተዋሉ ችግሮችን መለየት የሚያስችል ተቋማዊ የዳሰሳ ጥናት ስራ ተግባራዊ በማድረግና የጥናት ግኝቱን መነሻ በማድረግ በተሰሩ ስራዎች በማ/ቤቶች የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ስያስከትሉ የነበሩ የመዋቅር ፣የአሰራር ማሻሻያ ስራዎችን ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል ፡፡

በኮሚሽኑ የተጀመሩ የሪፎርም ስራ በሙሉ አቅም ተግባራዊ በማድረግ ተቋማዊ የለውጥ ሂደት በአስተማማኝ ደረጃ ላይ ለማድረስ በውስጡ መሟላት የሚገባቸው በርካታ የአገልግሎት መስጫ ማዕከላትን ያሉ በመሆናቸውና እነዚህን ማዕከላትን ለማደራጀትምከፍተኛ ሀብትና ጊዜን የሚጠይቅ በመሆኑ በሪፎርም ስራ የተገኙ ለውጦችን በግብአትነት በመጠቀም ቀር ስራዎችን ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችሉ ስትራቴጂክ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ተቋማዊ ቀጣይነትን አጠናክሮ በማስቀጠል በማ/ቤቶቻችን የሚከናውን የታራሚ አያያዝና አስተዳደር እና የማረም ማነፅ ተልዕኮ አፈፃፀም ውጤታማነትን ማረጋገጥ የሚያስችል ከ2013-2017 ዓ/ም በ5 ዓመት በመካከለኛ ዘመን ተግባራዊ የሚደረግ ስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመን ተዘጋጅቷል፡፡

## ለ. የስትራቴጂክ ዕቅድ አስፈላጊነት

የቤ/ጉ/ክ/መ/ማ/ቤቶች ኮሚሽን ተቋማዊ ራዕይና ተልዕኮ በማሳካት እና በሕግ የተሰጠው ተግባርና ኃላፍነት ለመወጣት ባለፉ ዘመናት የመካከለኛና የአጫጭር ጊዜዕቅዶችን በማዘጋጀት ተግባራዊ ስያደርግ የቆየ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በሀገርና በክልል ደረጃ የተጀመሩ የለውጥ እንቅስቃሰዎችን መሰራት በማድረግ ከተነደፉ ሀገራዊ ፖሊሲና ስትራቴጂ መነሻ የኮሚሽኑ የለውጥ ሂደት ቀጣይና ዘለቀታዊነትና በውጤታማነት የረጅም ዘመን እይታንታሳቢ ባደረገ መልኩ መፈፀም የሚያስችሉ ስትራቴጂክ ትኩረት በማስቀመጥ እና በተቀመጡ የትኩረት መስኮች ላይ በማቶኮር ተቋማዊ ዕድገት እና የታራሚው ተጠቃሚነትን የማረጋገጥ ስራ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

## ሐ. የስትራቴጂክ ዕቅድ ዓላማዎች

የታራሚዎች የአገልግሎት መሸጫ መሰረተ ልማቶች ፣ የመሰረታዊ ፍላጎት አቅርቦቶችን ማሟላት የታራሚውን ሰብዓዊ ክብር ማስጠበቅ ፣ የማ/ቤቱንና የታራሚውን ሠላምና ደህንነት ማረጋገጥ የሚያስችል አስተማማኝ የጥበቃ ደህንነት ስርዓት በመፍጠር ፣ ታራሚውን በዕውቀት ፣ በክህሎት እና በልማታዊ አስተሳሰብ በመገንባት የታረመና የታነፀ አምራች ዜጋ ማፍራት የሚያስችል የማረም ማነፅና የተሃድሶ ልማት ተግባራትን በብቃትና በጥራት መፈፀም የሚያስችል ጠንካራ የአሰራር ስርዓት ያለው ተቋም መገንባት ነው፡፡

## መ. የዕቅድ ወሰን

ያለፈውን የ2ኛ ዙር የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተተገበሩ ስትራቴጂካዊ አፈፃፀም ግምገማን መሰረት በማድረግ በቀጣይ 5 ዓመታት / ከ2013-2017 / ዕቅድ ዘመን የተግልጋይ ማህበረሰብ ፣ የባለድርሻና ተባባር አካላት ድጋፍና እገዛ ታክሎበት በኮሚሽኑ ባሉት በሁሉም የስራ ዘርፎችዞን ማ/ቤቶች መምሪያ እና የሚተገበር ስትራቴጂክ ዕቅድ ነው፡፡

## ሰ. የስትራቴጂክ ዕቅድ የተዘጋጀበት ሂደት

- በ2ኛ ዙር የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ከ2008 እስከ 2012 ዓ/ም ድረስ በኮሚሽኑ ተዘጋጅቶ የተተገበረውን የአምስት አመት ስትራተጅያዊ ዕቅድ መነሻ የተዘጋጁ የአፈፃፀም የግምገማ ሪፖርት ሰነድ
- ከሀገራዊ የለውጥ አቅጣጫ መነሻ በ2010 ዓ/ም በኮሚሽኑ ከተካሄድ ተቋማዊ የደሰሳ ጥናት መረጃ ፤
- በፌደራል ማ/ቤቶች ደረጃ የተዘጋጀ ሀገራዊ የታራሚ ማረም ማነፅ ስታንደርድ ለዕቅድ ዝግጅት ስራ በግብዓትነት በመጠቀም
- ለስትራቴጂክ ዝግጅት ስራ ከተገልጋይ ማህበረሰብ የተሰበሰቡ መረጃዎችን በግብዓትነት በመጠቀም
- ከሀገራዊ ስትራቴጂክ አቅጣጫ መሰረት በፌደራል ማ/ቤቶች ኮሚሽን የተዘጋጅ የ10 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ለስትራቴጂክ ዝግጅት ስራ መነሻ በማድረግ ስትራቴጂውን ማዘጋጀት ተችሏል
- የክልሉ መንግስት ኮሚሽኑ ያለበትን የአስራርና የአደረጃጀት ችግር ለመፍታት ለሚያደረገው ጥረት እያሰጠው ያለው ድጋፍና እገዛ ጠንካራ መሆኑ

# 1. ክፍል-አንድ

## 1.1. የ2ኛ ዙር የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የዕቅድ ትግበራ ዘመን አፈፃፀም ግምገማ

ኮሚሽኑ በ2ኛ ዙር የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የተቀርያ 4 ዋና ዋና የስትራቴጂክ ትኩረት መስኮች ፡-

- **የላቀ የታራሚ አያያዝና አስተዳደር**
- **የላቀ የእርምትና የህንፀት አገልግሎት**
- **አስተማማኝ የጥበቃ ደህንነት ስርዓት**
- **የተሻለ የአሠራርና አደረጃጀት ስርዓት** ሲሆኑ ከላይ ከተቀረፁ 4 የትኩረት መስኮችን መነሻ 16 የስትራቴጂክ ግቦችን በማስቀመጥ ባለፉት 5 ዕቅድ ዓመታት ስራዎችን ተግባራዊ ስያደረግ ቆይቷል፡፡

በስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመኑ ተግባራዊ የተደረጉ የዋና ዋና የግቦች አፈፃፀም

### 1.1.1 የመሰረታዊ ፍላጎት አቅርቦትን በማሻሻል የታራሚ እርካታን ከማሳደግ አንፃር

በስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመኑ የታራሚዎች እርካታ ለማሳደግ የመሰረታዊ ፍላጎት አቅርቦትን ተደራሽነትን ለማሻሻል የታራሚዎች የቀን ቀለብ ሂሳብ በማሻሻል ከ10.50 ብር ወደ 26.00 ብር እንድሻሻል ፤ የውሃ አቅርቦት ችግር ለመፍታት ተጨማር የዉሃ መስመር ዝርጋታ ፤ የሁለት ማ/ቤቶች የህክምና ማዕከላት የደረጃ የውስጥ አደረጃጀት ማሻሻያ ፤ በውስጥ ገቢ አቅም በአሶሳና መተከል ዞን ማ/ቤቶች የታራሚዎች ማደሪያ ቤት የማስፋፍያ ግንባታ እና በማ/ቤቶች እና በአጋር አካላት ድጋፍና እገዛ የታራሚ መኝታ አቅርቦቶችን የማሟላት ስራዎችን ተግባራዊ በማድረግ የስትራቴጂክ ግቡ ተግባር አፈፃፀም 68% ተግባራዊ ማድረግ የተቻለ ሲሆን

**በዘርፉ የነበረው ችግር**፡- ከሀገራዊ የገበያ አለመረጋጋት እና በሀገራዊና በክልላዊ ደረጃ የተከሰቱ የፀጥታ ችግር ወደ ማ/ቤት የሚገቡ ታራሚዎች ቁጥር መጨመር ፤የታራሚዎች የማደሪያ ቤቶች ጥበት ሁኔታ አለመገንባት በታራሚዎች የመሰረታዊ ፍላጎት አቅርቦቱ ጥራት ተደራሽነት ላይ አሉታዊ ጫና ያስከተሉ ጉዳዮች ናቸው፡፡

### 1.1.2. የታራሚዎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ከማሻሻል አንፃር

ታራሚዎች ያሉባቸው የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና ለመቀነስ ከተጎጅ ወገን ጋራ የእርቅ ስምምነት መፈፀም፤የዝውውር ፤ማህበራዊ ጉዳይ የማስፈፀም ፤በጠያቂ ወገኖቻቸው የመጎበኜት እና በግልና በማህበር ተደራጅቶ የገቢ ማስገኛ ስራ ዕድል ተጠቃምነትጉዳዮች በመቀበል በአሰራር ስርዓት እና በህገ መንግስታዊ ድንጋጌዎች መሰረት ታራሚዎች የማህበራዊ አገልግሎት እና የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ የስትራቴጂክ ግብ ተግባር አፈፃፀም 92% ለማከናወን የተቻለ ቢሆንም

**በዘርፉ የነበሩ ውስንነቶች፡-** የታራሚዎች የእርቅ አገልግሎት ተጠቃሚነት ከማስፋት አንፃር የባለድርሻ አካለት ድጋፍና እገዛ አናሳ መሆኑ በአፈፃፀም ላይ ያስከተለውን ክፍተት ለማስተካከል ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት የሚያስችሉ የአሰራር ስርዓት መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

### 1.1.3. የታራሚዎች ፍትህ አገልግሎት ተጠቃምነትን ማሻሻል

በቀጠሮ ፣ በክስ ፣ በይግባኝ እና በእርምት ሂደት ላይ የሚገኙ ታራሚዎች የህግ ድጋፍ አገልግሎት ፤የአመክሮ እና የይቅርታ አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ የህግና የአሰራር ስርዓቱን ተከትሎ እንድፈፀም ተገቢ የክትትል ድጋፍና የምልመላ ምዘና ተግባራትን በማከናውን በስትራቴጂ ዘመኑ ለ9,904 የታራሚዎች የህግ ድጋፍ አገልግሎት ፤ የአመክሮ እና የይቅርታ ዕድል ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ ለ12,226 ታራሚዎች አገልግሎቱን ተደራሽ በማድረግ የስትራቴጂክ ግቡ አፈፃፀም 100% ተግባራዊ ሲሆን

**በዘርፉ የነበሩ ውስንነቶች**፡- የጊዜ ቀጠሮ መዘገየት፤የታራሚዎች የይቅርታ አዋጅ የአሳታፍነት ውስንነት እና የህግ ድጋፍ አገልግሎት በሁሉም ታራሚዎች ተደራሽ ከማድረግ አንፃር ውስንነት ያለበት በመሆኑ ውስንነቱን ለመፍታት ከባለድረሻ አካላት ጋር የተጠናከረ ግንኙነት በመፈጠር ያለው ውስንቶችን እንድፈቱ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### 1.1.4. የማ/ቤት የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ስርዓት ከማሻሻል

ገቢ መሰብሰብ የማ/ቤት ዋና ዓላማ ተደረጎ ባይወሰድም በማረም ማነፅ ተልዕኮ አፈፃፀም ውስጥ ለሚመነጨውን ሀብት በአግባቡ ማስተዳደር የሚያስችል የአሰራር ማዕቀፍ ተቀምጦ ገቢውን የተቋማዊ አላማ ማሳከት በሚያስችሉ ተግባራት ላይ ለመዋል የወጣ የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም መመሪያ በማሻሻልና የገቢ አሰባሰብ ስርዓቱን በማጠናከር በስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመኑ

14,885,360 ብር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 14,496,906 ብር ገቢ በመሰብሰብ የስትራቴጂክ ግብ አፈፃፀም 100% ተግባራዊ የተድረግ ሲሆን የተሰበሰበ ገቢ የፋይናስ አሰራር ሂደትን ተከትሎ ስራ ላይ እንድውል በማድረግ ለማ/ቤት ተልዕኮ አፈፃፀም ወሳኝ በሆኑ ተግባራት ላይ እንድውልም ተደርጓል፡፡

**በዘርፉ የነበሩ ውስንነቶች**፡-የሀብት አስተዳደር ሂደቱ ከክራይ ሰብሳብነት አሰራር ነፃ በሆነ አግባብ ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ስርዓቱ ተከታታይነት ባለው የኦዲትና እንስፔክሽን ስራ ክፍተቶችን በመፈተሽ የማስተካከያ እርምጃ የመውሰድ ውስንነቶች መኖር፡፡

## 1.1.5. የታራሚዎች የስነ ልቦና ምክር ፣የህግና የስነ-ምግባር ማሻሻል ት/ት አሰጣጥ

በማ/ቤት የሚገኙ ታራሚዎችን አስተሳሰብና ግንዛቤ ለማሻሻል የንቃቱ ህግ ፣የስነ- ምግባር ማሻሻያ ት/ት እና የስነ-ልቦና ምክር አገልግሎት ድጋፍ አገልግሎት ተደራሽነትን በድግግሞሽ ለ103,806 ታራሚዎች ተደራሽ ለማድረግ ታቅዶ በስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመኑ ለ104,552 አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግ ተችሏል፡፡

**በዘረፉ የታየ ውስንነት፡-** ከፍትህ አካላት ጋር በመቀናጀት የንቃተ ህግ ት/ት አሰጣጥ ሂደት አናሳ መሆን ፣በተቋም ደረጃ የሚሰጡ የስነ-ልቦና ምክር አገልግሎት እና የስነ- ምግባር ማሻሻያ ስራዎች በጥናት ላይ ተመስርቶ የታራሚዎችን የስነ- ምግባር ችግር በሚፈታ መልኩ አለመስራት የዘርፉን ስራ ለማጠናከር የሚደረግ የድጋፍ ክትትል ውስንነት መኖር፡፡

## 1.1.6. የቀለም ት/ትና የሙያ ስልጠና ተጠቃሚነት ከማሳደግ አንፃር የነበረ አፈፃፀም

የታራሚዎችን አስተሳስብ እና የሙያ ክህሎት ደረጃ ለማሻሻል የታራሚዎች የቀለም ት/ት ተጠቃሚነትን ለማሳደግ በአሶሳና በመተከል ዞን ማ/ቤት ከ1ኛ ደረጃ ወደ ሁለተኛ ደረጃ የት/ት ቤት ደረጃ ማሻሻያ እንድደረግ የታራሚዎች የሙያ ክህሎት ስልጠና ተደራሽነትን በማስፋት ከመንግስት እና ከግል ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት ጋር ስምምነት በመፍጠር በስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመኑ 9,594 ታራሚዎችን በቀለም ት/ትና ስልጠና ተሳታፍ ለማድረግ ታቅዶ 8,177 ታራሚዎች ተሳታፍ በማድረግ ከስትራቴጂክ ግብ ተግባር አፈፃፀም አንፃር 67% ተግባራዊ ተደረጓል፡፡

**በዘርፉ ያሉ ውስንነቶች** ፡- የመምህርን እጥራት ፣ የተደራጃ የስልጠና ማዕከላት ፣ የግብዓት አቅርቦት ውስንነት በት/ትና ስልጠና ዘርፍ ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ጫና ያስከተለ በመሆኑ በቀጣይ

ስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመን የነበሩ ውስንነቶችን ማሻሻል የሚያስችሉ ስትራቴጂካዊ አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ  እና የአጋርና የባለድርሻ አካላት ትብብርና ድጋፍን የማጠናከር ስራ መስራት ይገባል፡፡

## 1.1.7. የግብርና ልማት ስራ አፈፃፀም ፡-

ከማረም ማነፅ ዘርፍ ስራዎች የግብርና ልማት ስራ አንዱ ሲሆን ታራሚዎች በዚህ ዘርፍ ስራ በሚከናውኑ የሰብል ፤የመስኖ ልማት የእንስሳት ሀብት ልማት ስራ ላይ በማሳተፍ ልማታዊ አስተሳሰብ እንድፈጥሩ በስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመንበግብርና ልማት ስራ ስምርት ድግግሞሽ 40,258 የህግ ታራሚዎችን በማሰማራት በዘርፉ የዕውቀትና ክህሎት ሽግግር እንድፈጠርላቸው የተደረገ ሲሆን በስትራቴጂክ ዘመኑ 75 ሄክታር መሬት የተለያዩ የሰብል ልማት እና የበጋ መስኖ ልማት ስራዎችን በማከናውን የተቋሙን የገቢ አቅም ከማሳደግ ባሻገር የአከባቢ ገበያን ማረጋጋት የሚያስችሉ የቋምና የጓሮ አትክልት ሰብሎችን በማምረት በተመጣጣኝ ዋጋ ለአከባቢው ማህበረሰብ ተደራሽ ማድረግ ያስቻሉ ተግባራት እንድከናወኑ ሲደረግ የግብርና ልማት ስራ ውጤታማነትን ለማረጋገጥ ከተለያዩ የግብርና ልማት ስራ የሚገኝ ገቢ ለማ/ቤቶች ተልዕኮ ስኬት ማስፈፀሚያነትን ዓላማ ላይ በማዋል የግብርና ልማት ስራውን መካናይዝድ ለማድረግ 1 የእርሻ ትራክቴር ግዥ ተከናወኖ አገልግሎት እንድሰጥ ተደረጓል እንዲሁም በእንስሳት ሀብት ልማት ስራን ለማሳደግ በአሶሳና በመተከል ዞን ዘመናዊ የእንስሳት ማድለብያ ቤቶች ግንባታ ስራዎችን በማከናውን የእንስሳት ማድለብ ስራ ተግባራዊ እንድሆን እና የእንስሳት እርባታ ስራን በማጠናከርና በማስፋት በዕቅድ ዘመኑ 1,200 የእንስሳት ሀብት ልማት ስራ ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዶ 1,314 ተግባራዊየተድረግ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ለማከናውን የተቻለ ቢሆንም የስትራቴጂክ ግብ ተግባር አፈፃፀም 86% ተግባራዊ ተደረጓል፡፡

**በዘርፍ ያሉ ውስንነቶች፡-** በማ/ቤት በህግ ጥላ ስር የሚገኝ አምራች የሰው ኃይል በግብረና ልማት ስራ ላይ በስፋት በማሰማራት ታራሚውን ለምርታማነት የሚያበቃ የዕውቀት ሽግግር ለመፍጠርና የማ/ቤትን የተጀመሩ የልማት ስራዎችን በበለጠ በማጠናከርና የማልማት አቅም በማሳደግ የመንግስት የወጭ ጫና መጋራት የሚያስችል አቅም ለመፍጠር የእርሻ መሬት አቅርቦት ለሁሉም ማ/ቤት በስፋት ተደራሽ ያለመሆን ፤ግብርና ልማት ስራን በስፋት ማከናውን የሚያስችል የምርት ግብዓት አቅርቦት በባለድርሻና ተባባር ተቋማት ሙያዊ ድጋፍ ውስንነት መኖር፡፡

## 1.1.8. የማ/ቤት የጥበቃ ድኅንነት ስርዓትን ማሻሻያ ስራ አፈፃፀም

የማ/ቤቱንና የታራሚውን ሠላምና ደህንነት ፤ሰብዓዊ መብት ጥበቃን መሰረት ያደረገ የታራሚዎች ህግ ተገዥነትና ስርዓት አክባርነት ስርዓት እንድረጋገጥ የማ/ቤት የጥበቃ ደኅንነት አስተማማኝነትን ማረጋገጥ የሚያስችሉ የቋምና ተንቀሳቃሽ ጥበቃ ፤የፍተሻና የመረጃ ክትትል ስርዓት ለማጠናከር የዘርፉን አደረጃጀት የማሻሻል ፤ በኤለክትሮንክ የፍተሻ መሳርያ አቅርቦት እንድሟላ ፤ተከታታይነት ያላው የታራሚዎች ግቢና የማደሪያ ቤት ፈተሻ ፤የመረጃ ክትትል እና የታራሚዎች እንቅስቃሴ ቁጥጥር ክትትል ስርዓትን በማሻሻል የማ/ቤቱ ሠላምና ደኅንነታቸውን ተረጋግጦ ታራሚው ከስጋት ነፃ ሆኖ ለእርምት እና ህንፀት ስራ ዝግጁ እንድሆን የማድረግ ስራዎች እንድከናወኑ ተደረጓል፡፡

**በዘርፉ የነበሩ ውስንነቶች** ፡-ለዘርፉ የሚያስፈልግ የሎጀስትክ አቅርቦት ችግር፣ የሰው ኃይል እጥሬት እና ሀገራዊ የለውጥ እንቅስቃሰን መነሻ በማድረግ በተወሰኑ ታራሚዎች የተዛባ አመለካካት በማ/ቤቶች ላይ ጥቃት የማድረስና ሁከትና ብጥብጥ የማስነሳት ሙከራዎች መታየትና ከጥበቃ መካከል የስነ- ምግባር ችግሮች ያለባቸው አባላት የተከለከሉ ነገሮችን ወደ ማ/ቤት የማስገባት ሁኔታዎች መኖር በስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመኑ የታዩ ውስንነቶች ናቸው፡፡

## 1.1.9. ተቋማዊ የአሰራር ስርዓትን ከማሻሻል አንፃር የነበሩ አፈፃፀሞች፡-

ጠንካራ ተቋማዊ አሰራርና አደረጃጀት ስረዓት መኖር ለተቋም ተልዕኮ አፈጻፀም ውጤታማነት ከፍተኛ አስተዋፆ ያለው በመሆኑ ኮሚሽኑ ሀገራዊና ክልላዊ የሪፎርም እንቅስቃሴን መነሻ በማድረግ ተቋማዊ የአሰራር ማሻሻያ ስራዎችን ተግባራዊ ያድረግ ሲሆን

የአሰራርና የአፈፃፀም ክፍተቶችን ለማሻሻል የተቋሙ ማቋቋሚያ አዋጅ ፣ የአባላት መተዳደሪያ፣ የአባላት የማዕረግ ዕድጌት ፣ የዲስፕሊን አፈፃፀም መመሪያ እና የታራሚዎች አያያዝ ደንቦች ማሻሻያ ስራዎች በታራሚዎች አገልግሎት አሰጣጥ ላይ አሉታዊ ጫና ያስከተለው የማ/ቤት የፑል አሰራር ስርዓት ላይ የአሰራር ማሻሻያ በማድረግ የማ/ቤት የግዥና ፋይናንስ አስተዳደር ስራ ከፑል አሰራር ነፃ ሆኖ በተቋሙ እንድመራ የአሰራር እና የአደረጃጀት ማሻሻያ ስራ በታራሚዎች ማረም ማነፅ ተግበራ ሂደት ከማ/ቤቶች የሚመነጨውን ሀብት የሚመራበት የአስራር ስርዓት ለማሻሻል የማ/ቤቶችን የውስጥ ገቢ አሰባሰብ አጠቃቀም ስርዓት ግልፅነት ፣ ተጠያቂነት እና የጋራ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ በሚያስችል ሁኔታ መመሪያው ተሻሽሎ ስራ ላይ እንድውል በኮሚሽኑ የነበረው የመዋቅራዊ አደረጃጀት በታራሚ አያያዝና አገልግሎት አሰጣጥ እና የማረም ማነፅ ተግባር አፈፃፀም ያስከተለው የአሰርር ክፍተት ለማሻሻል የመዋቅርና

የአሰራር ማሻሻያ ጥናት ስራ ተግባራዊ በማድረግ በ1 ዋና የስራ ሂደት ስር የተጠቃለሉ የማ/ቤት ዋና ዋና የስራ ዘርፎች በኮሚሽን ደረጃ በ3 ዳይሬክቶሬት በዞን ማ/ቤቶች በ4 /ስራ ሂደት /ዳይሬክቶሬት አስተባባር እና በልዩ ልዩ ቡድን መሪ እንድደራጅ በማድረግ የኮሚሽኑ መዋቅራዊ አደረጃጀት ማሻሻያ ስራ ተግባራዊ በማድረግ ወደ ትግበራ ስራ ተገብቷል፡፡

**በዘርፍ የነበሩ ውስንነቶች**፡-የተካሄዱ የተቋማዊ የአሰራር ማሻሻያ ስራ በሚፈለግ ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ በኮሚሽኑ ያለው የሀብትና የሰው ኃይል መጠንና የአቅም ውስንነት የማሻሻያ ስራ ውጤታማነት ላይ ውስንነት እንድኖር አደረጎታል፡፡

## 1.1.10.ባለብዙ ዘርፍ ተግባራት ውጤታማነትን ማስፋት

በማ/ቤት የህግ ታራሚሴቶች ፣ ወጣቶች ፣ አካል ጉዳተኞች እና ከወላጆቻቻው ጋር በማ/ቤት የሚገኙ ህፃናት የማህበራዊ የኢኮኖሚያዊ እና የስነ- ልቦናዊ ጫና ተጋላጭነት በመቀነስ እንድታረሙ የተለያዩ የማህበራዊ አገልግሎት፣የገቢ ማስገኛ የስራ ዕድል አማራጭ ተጠቃሚነት ድጋፍ እንድያገኙ በማድረግ የታራሚዎች ፍላጎት መሰረት ያደረገ የቀለምት/ት የሙያ ስልጠናና የዕደ ጥበብ ስልጠና ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት በስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመን በመደበኛና መደበኛ ባልሆነ ተግባር ተኮር ት/ት ፣ በመደበኛ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና በአጫጭር ጊዜ ስልጠና በሳሙና ማምረት ፣ በልብስ ስፊት በሰንጻር ጥልፊ ስራ እና ልዩ ልዩ የዕደ ጥበብ ሙያ 345 ስልጠና አገልግሎት እንድያገኙ የተደረገ ሲሆን

ከወላጆቻቸው ጋር በማ/ቤት የሚገኙ ህፃናትን ከስነ-ልቦናዊ ጫና ተጋላጭ ለመጠበቅ በመተከል ዞን ማ/ቤት በአጋር አካላት ድጋፍና ከማ/ቤት ግቢ ወጭ የመዋለ ህፃናት ት/ቤት ግንባታ ስራ ተግባራዊ በማድረግ ህፃናቱ የመዝናኛና የት/ት አገልግሎት ተጠቃሚ በማድረግ በአሶሳ ዞን ማ/ቤትም በግል ት/ት ቤት ተቋማት ጋር ስምምነት በመፍጠር ት/ት እንድያገኙ የኮሚሽኑ አመራር፤አባላትና ሰራተኛ ከማ/ቤት ደረጃ ከሚከናወኑ ስራዎች በተጨማር በአሶሳ ከተማ ውስጥ ከሚገኙ ወላጅ አልባ ህፃናት መካከል 5 ህፃናት በቋምነት በመረከብ የት/ት ግብዓት የአልባሳት እና የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ት/ት እንድማሩ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል፡፡

የሴቶችን ተሳትፎና የውሳኔ ሰጭነትን ሚና ለማሻሻል በኮሚሽኑ እና በዞን ማ/ቤቶች ደረጃ 8ሴት አባላት በውሳኔ ሰጭ አመራርነት እና በቡድን መሪነት የስራ ክፍሎች የስራ ምደባና ስምሪት እንድያገኙ በማድረግ የተሳትፎን ማሻሻል ስራ ተግባራዊ ተደጓል፡፡

ሀገርቱን እየተከተለች ባለው የአረንጓደ ልማት ኢኮኖሚ ስራን በመደገፍ ረገድ ማ/ቤቶች የራሳቸውን አስተዋፆ ማበርከት እንድችሉ ታራሚዎችን በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ስራ ላይ በማሰማራት ስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመን 23,744 ሀገር በቀል እና የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ያላቸው ችግኝ ተከላ ስራ ለማከናውን ታቅዶ 20,902 የተለያዩ የችግኝ ተከላ ስራ ተከናውኗል፡፡

**በዘርፍ የነበሩ ውስንነቶች፡-** የሴቶች ፣ ወጣቶች ፣ አካል ጉዳተኞች እና ህፃናትን ከማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ተጋላጭነትን ለማላቀቅ የተሰጡ የት/ት ፣ ስልጠናና የገቢ ማስገኛ ስራ አማራጮች ለታራሚዎች ችግር ዘላቀታዊ በሆነ መልኩ ለመፍታት እንድያስገኝ ከማድረግ አንፃር የድጋፍ ክትትል ስርአት ውስንነቶች ታይቷል፡፡

## 1.1.11. የተቋም ገፅታ ግንባታ ስራን ከማሳደግ

በማ/ቤቶቻችን የሚከናወኑ የት/ትና ስልጠና ፤ የግብርና ልማት ስራ እና የዕደ ጥበብና የገቢ ማስገኛ የስራ እንቅስቃሰ በተለያዩ የመገናኛ ዜደ ለማህበረሰቡ ተደራሽ ማድረግ እንድያስችል በኮሚሽን ፣ በአሶሳ እና መተከል ዞን ማ/ቤቶች የመረጃ ማሰራጫ ፌስ ቡክ ገፅ በመክፈት የማ/ቤት የስራ እንቅስቃሰ በፌሰ ቡክ ፤ በክልሉ ኤፍ ኤም ሬዲዮ ጣቢያ ፤በቤጉ ቴሌቭዥን እና በብሮሽር እንድሰራጭ ኮሚሽኑ በሚያካሂዳቸው ዓመታዊ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ግምገማ እና በዓመታዊ የፍትህ ሳምንት ፕሮግራሞች የፍትህ ተቋማት አመራር እና የባለድርሻ አካላት የማ/ቤት የስራ እንቅስቃሰን በመስክ ጎብኝት እንድገነዘቡ በማድረግ ተቋማዊ ገፅታ ግንባታ ስራ ተግባራዊ ተደረጓል፡፡

**በዘረፉ ያለው ውስንነት፡-**የአጋርና ተባባር አካላት የጋራ መግባበት ማጠናከር ለማ/ቤቶች ተልዕኮ አፈፃፀም ወሳኝ ሚና ያለው ቢሆንም የእነዚህ አካላት የጋራ ቅንጅት ማጠናከር የሚያስችሉጠንካራ የግንኙነት አግባብ ፈጥሮ የመስራት ፤የመረጃ ጥራት ተደራሽነት ውስንነት በዘርፉ የታዩ ውስንነቶች ናቸው፡፡

## 1.1.12. የመፈፀም የማስፈፀም አቅም ግንባታን ከማሳደግ አንፃር የነበሩ አፈፃፀሞች

የማስፈፀም አቅም ውስንነትን ለማሻሻል የተቋሙ አመራር አባላት እና ሰራተኞች በሬጅም ጊዜ የት/ት ስልጠና ፕሮግራም በልዩ ልዩ የት/ት ዘርፎች በማስተር ፤በመጀመሪያ ዲግሪ ፤በፖሊስ ስራ አመራር ስልጠና 87 አመራር፤ አባላት እና ሰራተኞችን ተሳታፊ ለማድረግ ታቅዶ61 ተሳታፍ እንድሆኑ የተደረገ ሲሆን የፖሊስ አባላት የስነ- ምግባር ክፍተት ማሻሻያ ተሃድሶ ስልጠና በልዩ ልዩ የአጭር ጊዜ የስራ እና የክህሎት ማሻሻያ ስልጠና ዘርፎች 117 አመራር

፣ሰራተኞች እና አባላት ተሳታፊ በማድረግ በስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመኑ የት/ት ስልጠና ተደራሽነትን 59% ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን በኮሚሽኑ ያለውን የጥበቃ የሰው ኃይል እጥረት ችግር ለመሙላት 100 አድስ የፖሊስ አባላት ቅጠርና ስልጠና በመሰጠት በስትራቴጂክ ዕቅድ የሰው ኃይል መጠን ወደ 537 ማድረስ የተቻለ ሲሆን የስትራቴጂክ ግብ ተግባር አፈፃፀም 53% ተግባራዊ ተደረጓል፡፡

**በዘረፉ ያለው ውስንነት**፡- በተቋሙ ያለው የሰው ኃይል መጠን በማ/ቤት ከላው የታራሚ ቁጥርና የስራ ስፋት ጋር ተመጣጣኝ ባለመሆኑ በተቋሙ ስራ እና በፖሊስ አባላት ላይ ከፍተኛ የስራ ጫና ያስከተለ መሆኑ በአባላት ዘንድ የሚታየው የስነ- ምግባር ችግርና የአቅም ውስንነት በተቋም ተልዕኮ ስከት ላይ አሉታዊ ጫና ማስከተል መቻሉ በዘረፉ ያሉ ውስንነቶች ናቸው፡፡

### 1.1.13. ተቋማዊ አደረጃጀት ከማሻሻል

በመ/ቤቶች የሚታየውን የታራሚዎች ማደሪያ ቤት እና የውስጥ አደረጃጀት ችግሮችን ለመፍተት የማ/ቤት የመስፋፊያ ግንባታ ስራ በአሶሳ ዞን ማ/ቤት ለማካሄድ የግንባታ ዲዛይን ጥናት ስራ መሰረት ጫራታ ወጥቶ 6,191,465.45 /ስድስት ሚሊዮን አንድ መቶ ዘጠና አንድ ሽህ አራት መቶ ስልሳ አምስት ብር ከ45 ሳንቲም/ የግንባታ ስራ ውል ተገብቶ በግንባታ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡

በመተከል ዞን ማ/ቤት የት/ት ማዕከሉን ደረጃ ለማሻሻል 2 ክፍል ያለው የት/ት ማዕከል ግንባታ ስራ በማከናወን አገልግሎት ላይ እንድውል ተደረጓል፡፡

የማ/ቤት የልማት ማዕከላት ለማጠናከር በአሶሳ ዞን ማ/ቤት አድስ የልማት ማዕከል ለመክፈት በተደረገ ጥሬት 253 ሄክታር መሬት የያዘ የልማት ማዕከል በማስፈቀድ ለአገልግሎት ብቁ እንድሆን ተደርጓል፡፡

## 1.2. በስትራቲጂክ ዕቅድ ዘመኑ ኮሚሽኑ ካከናወናቸው ተግባራት መካከል የስኬት ምንጭ የሆኑ ስራዎች፡-

- ከሀገራዊና ክልላዊ የለውጥ እንቅስቃሰ መነሻ በማድረግ በኮሚሽኑ የለውጥ ስራን ተግባራዊ ለማድረገ የተካሄደ የዳሰሳ ጥናት ስራ እና ጥናቱን መሰረት በማድረግ የተካሄደ ማሻሻያ ስራ የዘመናት የማረሚያ በቶችን የአሰራር ፤የመዋቅር እና የአደረጃጀት ችግሮችን በጥልቀት በመለየት እና ችግሮችን ለመፍታት በተሰሩ ስራዎች የማ/ቤቱን ችግር መፍታት የቻሉ ውጤታማ የአሰራርና የአደረጃጀት ማሻሻያ ስራተግባራዊ መሆናቸው፡፡

- በማ/ቤት በተጀመሩ የውስጥ ገቢ አሰባሰብ ስራ የሚሰበሰበውን ገቢ በመጠቀም የማ/ቤት የውስጥ ችግሮችን በመፍታት ሂደት ለማ/ቤት ትልቅ አቅም መሆኑ እና ገቢውንም በመጠቀም የታራሚዎች ማደሪያ ቤት የማስፋፍያ፤የት/ት ማዕከላት ማስፋፍያ ፤የታራሚዎች ሽንት ቤት ፤ሚንስ ቤት፤ የዘመድ ግንኙነት ማዕከል ፤የአደራሽና የቢሮ ግንባታ ስራ ለታራሚዎች የህክምና ማመላለሻ መኪና ግዥ ፤የእርሻ ትራክቴር ግዥ ተግባራትን በማከናውን በራስ አቅም የውስጥ ችግሮችን የመፍታት ልምድ ማሳደግ የሚያስችሉ ተግባራቶች እንድከናወኑ ተደረጓል፡፡
- በአጋር ተቋማት ድጋፍና ትብብር የማ/ቤቶች አገልግሎት አሰጣት ችግር መፍታት የቻሉ ስትራቴጂካዊ ድጋፎች መደረጋቸው የአገልግሎት አሰጣጡን በማሻሻል ሂደት አበረታች ውጤት ማስገኜት መቻሉ ለስትራቴጂክ ውጤታማነቱ አስተዋፆ ማበርካት መቻሉ፡፡

## 1.3. በስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመን የነበሩ ጠንካራና ደካማጎኖች

### 1.3.1. ጠንካራ ጎን፡-

- ሀገራዊና ክልላዊ የሪፎርም አቅጣጫዎችን በመከተል ተቋማዊ የሪፎርም ስራዎችን ተግባራዊ ማድረግ መቻሉ
- ተቋሙ ያለውን ውስን ሀብትና የሰው ኃይሉን በማቀናጀት በስትራቴጂክ ዘመኑ የተቀመጡ ዕቅዶችን ተግባራዊ ማድረግ መቻሉ
- ማ/ቤት ያለውን ውስን የሰው ኃይል በመጠቀም በማ/ቤት ላይ የተጋረጡ ችግሮች ተቋሙን ለጥቃት ተጋላጭ ሳያደርግ ባለው የስው ኃይል ችግሩን መከላከል መቻሉ
- የውስጥ ገቢ አቅምን በመጠቀም ዘርፈ ብዙ የማ/ቤት የውስጥ ችግሮችን መፍታት መቻሉ

### 1.3.2. ደካማጎኖች፡-

- በየደረጃው የሚደረግ ተቋማዊ የድጋፍ ክትትል ስርዓት ለታችኛው መዋቅር አቅም በሚፈጠር መልኩ ተግባራዊ አለማድረግ
- የታራሚዎች የማረም ማነፅ ስራዎች ከአፈፃፀም ጥራትና ውጤታማነት አንፃር ያለበትን ደረጃ በማጥናት ያሉበትን ጉድሎቶችን የማስተካከል ልምድ አናሳ መሆን
- በአባላት ዘንድ ጎልቶ የወጡ የስነ- ምግባር ችግሮችን በዘላቂነት መፍታት የሚያስችል ስትራቴጂካዊ አቅጣጫ በማስቀመጥ እና ቁርጠኛ አቋም ይዞ ችግሩ መፍታት አለመቻል
- የተቋሙ መረጃ አያያዝና አጠቃቀም ስርዓት ደካማ መሆን

## 1.4.ለዘረፉ ስትራቴጂክ ትግበራ ስራ ወሳኝ የሆኑ ሰብዓዊና ቁሳዊ ሀብቶች

- ሀገራዊ የሪፎርም እንቅስቃሰ መሰረት በማድረግ ተቋማዊ አሰራርን ለማሻሻል የተሰሩ የመዋቅርና የአሰራርማሻሻያ ስራዎች ለማ/ቤቱ አገልግሎት አሰጣጥ እና ለማረም ማነፅ ስራ ውጤታማነት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥሩ መሆናቸው ለቀጣይ ስትራቴጂክ ትግበራ ስራ መልካም አጋጣም መሆናቸው
- በማ/ቤት ያለውን ሰፍውን የታራሚ ሰው ኃይል በልማት ስራ ስምርት ላይ የማልማት አቅማቸውን ማሳደግን ታሳቢ በማድረግ በማ/ቤቶች የልማት ማዕከል ለማደራጀት የተፈቀዱ የሰፋፍ የእርሻ መሬቶች እና ለሎች አማራጭ የስራ መስኮች መኖርበስትራቴጂክ ዘመኑ የስትራቴጂክ ትግበራ ስራ አማራጭ አቅም መሆናቸው
- የአጋር ፣የባለድርሻና ተባባሪ አካላት ድጋፍን ትብብር በስትራቴጂክ ዘመኑ የተቀመጡ ስትራቴጂካዊ አቅጣጫዎችን ለማሳካት የሚያስችሉ መሆናቸው
- በማ/ቤት የሚገኙ የህግ ታራሚዎች በማ/ቤት ቆይታቸው በተለያዩ ገቢ ማስገኛ ስራዕድልላይተሰማርቶ የመስራት ዝንባሌ ማደግ ለማረም ማነፅ ስራ ውጤታማነት ከፍተኛ አስተዋፆ ያለው መሆኑ

### 1.4. የማ/ቤቶች ኮሚሽን የተገልጋይ ፤ የባለድርሻ ፤ የአጋር እና ተባባሪ አካላት ፍላጎት ትንተና

#### 1.4.1. የተገልጋይ አካላት ፍላጎት ትንተና፡-

| ተ. ቁ | ተገልጋዮች | ተገልጋዮች ከተቋሙ የሚፈልጉት አገልግሎት | ተቋሙ ከተገልጋዮች የሚፈልገው ባህሪያት | የሚጠበቀው ተግባር ባይከናወን የሚያሳድረው ተጽዕኖ | የተጽእኖ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | **የህግ ታራሚዎች** | ◆ የምግብ አቅርቦት የመመገቢያና የማብሰያ ዕቃዎች አቅርቦት<br>◆ የመጠለያ የመኝታ የአልባሳት አጋልግሎት<br>◆ መዝናኛ፤<br>◆ የጽዳት፤ የህክምና፣<br>◆ ሠላምና ደህንነትን ያረጋገጠ ጥበቃ፤የሰብአዊ አያያዝ፤<br>◆ የፍትህ ነክ አገልግሎቶች /የቀጠሮ ክትትል፤አመክሮና ይቅርታ ፤ የዝውውር የእርቅ አገልግሎት/<br>◆ የገቢ ማስገኛ ሥራ ዕድል ተጠቃሚነት<br>◆ የምክርና የማህበራዊ አገልግሎት ድጋፍ<br>◆ የቤተሰብ ግንኙነት፣<br>◆ የመረጃ አገልግሎት፤<br>◆ የግል ንብረታቸውና ገንዘባቸው በአደራ እንዲቀመጥ<br>◆ የት//ትና ስልጠና ፤የስነ- ምግባር ማሻሻያና የንቃተ ህግ ት/ት<br>◆ ለሚያቀርቡ ጥያቄ ተገቢና ወቅታዊ ምላሽ መስጠት | ◆ ለደንብና መመሪያዎች ተገዥ ህግና ስርዓት ማክበር ለውስጥ አሰራር ስርዓት ተገዥ መሆን<br>◆ የታማኝነት ፤ የመታረም፤ የመጸጸትና መልካምስነ-ምግባር መላበስ<br>◆ በተቋሙ በሚዘጋጁ ልዩ ልዩ የት/ትና ስልጠና ፕሮግራሞች ተሳታፍ መሆን<br>◆ በተቋም ደረጃ ተግባራዊ በሚደረጉ የልማት ፕሮግራም ላይ ተሳታፍ መሆን<br>◆ ከሌሎች ታራሚዎች ጋር ተግባብቶ መኖር/ ጤናማ የእርስ በርስ ግንኙትን መፍጠር<br>◆ የግልና የአከባቢ ንፅህናን በአግባቡ መጠበቅ<br>◆ ባላቸው ዕውቀት ክህሎትና አቅም ተቋሙን የማገዝና የመደገፍ<br>◆ አቅማቸው በስራ ፈጠራና በኢኮኖሚ እንዲገነቡ ይፈልጋል፡፡<br>◆ ከአድማ ከስርዓት አልበኝነት አሰራር ራስን ነፃ ማድረግ | ◆ የእርስ በርስ ብጥብጥና ግጭት፣ ስርዓተአልበኝነት፣የህይወት መጥፋት ፣የአካል ጉድለት፣ የንብረት ውድመት፤የአደጋ ተጋላጭነት<br>◆ የእርምትና የመልካም ስነ- ምግባር ጉድለት<br>◆ መልካም አስተዳደር የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ክስተት መፈጠር | በጣም ከፍተኛ |
| 2 | **የታራሚ ቤተሰቦች** | ◆ መሠረታዊ ፍላጎታቸው በአግባቡ እንዲሚሉላቸው<br>◆ ቀልጣፋ የቤተሰብ ግንኙነት<br>◆ የታሰሩ ቤተሰቦቻቸው በአግባቡ እንዲያዙ፤<br>◆ ባህሪያቸው እንዲታረም፤<br>◆ ት/ትና የሙያ ስልጠና እንዲያገኙ<br>◆ የታራሚዎች የፍትህ ጉዳያቸው | ◆ ለማ/ቤቱ የአሰራር ስርዓት ተገዥ መሆን<br>◆ በእርምት ላይ ለሚገኙ ወገኖቻቸው መረጋጋት አቅም የሚፈጥሩ ምክሮችን መስጠት ለእርምት አወንታዊ ምላሽ እንድሰጡ ማድረግ<br>◆ በአሰራር ሂደት ውስጥ ቅረታ | ◆ በተቋሙ ላይ እምነት የማጣት<br>◆ የመልካም አሰተዳደር መጓደል፤ የተቋሙ ገፅታ ግንባታን ስም ይጎድፋል፤<br>◆ በታራሚዎች ላይ የሞራል ችግር ይፈጥራል<br>◆ በታራሚዎች ዘንድ ያለመረጋጋትንና | ◆ በጣም ከፍተኛ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | እንዲቀላጠፍ ይፈልጋሉ<br>◆ ሰብዓዊ መብታቸው እንዲከበርላቸው | የሚፈጥሩ ካሉ ወደ ግጭትና አለመግባበት ቢፍጠር በህጋዊ አሰራር ቅረታቸውን ማቅረብ<br>◆ በተቋም አሰራር ስርዓት መሻሻል ገንቢ ሀሳብና አስተያየት መስጠት<br>◆ ባጠቃላይ በማረምና ማነጽ ስራዎች ላይ አጋዥ እንዲሆኑ ይፈልጋለ | የመረበሽ ስሜት ያመጣል፣<br>◆ ተቋሙ ከህዝብ የተነጠለ ይሆናል<br>◆ የክልላዊ ገጽታ መበላሸት | |
| 3 | **የአስተዳደሩ ሰራተኞች** | ◆ ከአድእሎ ነፃ የሆነ ፍትሃዊ የምልመላ፣ የቅጥር፣ የምደባ የማዕረግ የደረጃ እድገትና የዝውውር አፈጻፀም እንዲኖር ይፈልጋሉ፣<br>◆ ግልፅና ፍትሃዊ የሥራ አመራርና የአስተዳደር ስርዓት እንዲኖር ይፈልጋሉ፣<br>◆ ከሥራው ጋር አግባብነት ያለው ተከታተይ ትምህርትና ስልጠና ማግኘት ይፈልጋሉ፣<br>◆ ምቹ የሥራ አካባቢ እንዲኖር ይፈልጋሉ፣<br>◆ በዕቅድ ዝግጅት፣ አፈፃፀም፣ ግምገማና ክትትል ሠራተኞች እንዲሳተፉ ይፈልጋሉ<br>◆ በመንግሥት የሚፈቀዱላቸውን ጥቅማ ጥቅሞች በወቅቱ እንዲሟሉላቸው ይፈልጋሉ<br>◆ ወቅታዊ የሆኑ መረጃዎችን የማግኘት ፍላጎት<br>◆ አቅም መገንባት የሚያስችል የት/ት ስልጠና እና ልዩ ልዩ ማትጊያ/የሞራል/ ስርዓት ተጠቃሚነት | ◆ በደንብና መመሪያ መሰረት ተግባሮቻቸውን እንዲፈጽሙ ይፈልጋል<br>◆ ከአመለካከት ከክራይ ሰብሳብነት ነፃ የሆነ ጥራት ያለው አገልግሎት በመስጠት ደንበኛን የሚያረካ ስራ እንዲከናወን ይፈልጋል<br>◆ ቅንጅታዊ አሰራርና ጤናማ የእርስበርስ የስራ ግንኙነት እንዲኖራቸው ይፈልጋል<br>◆ የሙያ ስነ- ምግባርን ያከበረና መልካም ስነ-ምግባር ተላብሶ መገኜት ይፈለጋል | ◆ ተቋሙያስቀመጠው ግብና ዓላማ በተፈለገው መጠን፣ ብቃትና ጥራት አይሣካም፣<br>◆ የተቋም ገጽታ መበላሸት<br>◆ የማረሚያ ቤቱ የታራሚ አገልግሎት በተፈለገው ጥራትና ፍጥነት አይፈጸምም፣ሥራውን ለማከናወን ፍላጎትና ተነሳሽነት ማጣት ያስከትላል፣<br>◆ ውጤታማ ሥራ አለመስራት፣ የባለቤትነት ስሜት አለመኖር<br>◆ የዕቅድ አፈፃፀም መጓተት፣<br>◆ የህዝብና የመንግስትን አሜነታን ማጣት<br>◆ የአስተዳደሩ ዓላማና የተገልጋዮች ፍላጐት አይሳካም፣ | ◆ በጣም ከፍተኛ |

1.4.2. የባለድርሻ አካላት ፍላጎት ትንተና

| ተ.ቁ | ባለድርሻ አካል | የባለድርሻ አካላት ፍላጎትና አገልግሎት | ተቋሙ ከባለድርሻ አካላት የሚፈልጋቸው ባህሪያት | ሊገጥም የሚችል ችግር | የተጽዕኖ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | **የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት** | ◆ በተጨባጭ መረጃ የተደገፈ ወቅታዊ ዕቅድና ሪፖርት እንዲቀርብ፣<br>◆ የህግ የበላይነትና የታራሚዎች ሰብዓዊ መብት በአግባቡ እንዲጠበቅ፣<br>◆ በጥናት የተመሰረተ፣ ወቅታዊና ጥራት ያለዉ የህግ ረቂቅ እንዲቀርብ፣<br>◆ ጥራት ያለው፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ እና ወጪ ቆጣቢ አገልግሎት እንዲሰጥ | ◆ ለተቋሙ ተልዕኮ አጋዥ የሆነ የህግ ማዕቀፍ እንዲፀድቅለት፣<br>◆ ለተቋም ዓለማ ማስፈፀሚያ የሚስፈልግ የበጀት ድጋፍ በበቂ ሁኔታ እንድቀርብ ይፈልጋል፣<br>◆ ለሚያቀርበዉ እቅድና ሪፖርት ወቅታዊ ግብረ መልስና ድጋፍ ይፈልጋል፣<br>◆ ለሚያቀርበዉ የድጋፍ ጥያቄ ፈጣን ምላሽ እንዲሰጥ | ◆ የተቋም ተልዕኮ ተፈፃምነት መቀነስ፤<br>◆ የመልካም አስተዳደር ችግሮች<br>◆ በተቋሙ አመራርና<br>◆ የተቋሙ ህልውና ማጣት | ◆ በጣም ከፍተኛ |
| 2 | **ፍርድ ቤቶች** | ◆ የፍርድ ውሳኔ እንዲፈፀምናመረጃ በአግባቡ እንዲያዝ፣<br>◆ ሰብአዊ መብት አያያዝ እንዲኖር፣<br>◆ የቀጠሮ እስረኞችናታራሚዎችበቀነቀጠ ሯቸውበአግብቡ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ፣<br>◆ የፍርድ ቤቶች ደንብ አንዲከበር፣<br>◆ የአመክሮና መፈቻ በጊዜው እንዲመጣ፣ | ◆ ውሳኔ ያላገኙ ታራሚዎች በአጭር ጊዜ ውሳኔ እንዲያገኙ ይፈልጋል ፣ የውሳኔ ግልባጭ እንዲደርሳቸው፡<br>◆ የይግባኝ ጥያቄ በወቅቱ ምላሽ እንዲያገኙ፡<br>◆ አጭርና ያልተንዛዛ ቀጠሮ<br>◆ ፍርድ ቤቶች ተደራሽና ለጥበቃና ደህንነት ምቹ እንዲሆኑ ይፈልጋል<br>◆ የማረሚያ ቤቱ ደንብና መመሪያዎች እንዲከበሩ ይፈልጋል<br>◆ እንደጸጥታ ተቋም ለታራሚዎች በችሎት ቅድሚያ እንዲሰጥ መፈለግ<br>◆ የተሟላ የቀጠሮ አስረኛና የታራሚ መረጃ፣ | ◆ የፍትህ መጓተት ያስከትላል<br>◆ ግንኙነትን ያሻክራል<br>◆ መልካም አስተዳደርመጓደል<br>◆ ፍርድ ቤቱ የእርምት እርምጃ ሊወስድ ይችላል<br>◆ የማረሚያ ቤቶችመጨናነቅን ያስከትላል<br>◆ የሰብዓዊ መብት ጥሰት | ◆ በጣም ከፍተኛ |
| 3 | **ሠላም ግንባታ ፀጥታ ቢሮ** | ◆ የታራሚውን እና የተቋሙን ሠላምና ደህንነት የሚያረጋግጥ አስተማማኝ የጥበቃ ደህንነት ስርዓት እንድኖር<br>◆ የወቅታዊነቱን የጠበቃ የመረጃ ተደራሽነት<br>◆ የተቋም የስራ አፈፃፀም ሪፖርት | ◆ ተቋማዊ ድጋፍና ዕገዛን<br>◆ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወቅታዊ ምላሽ .መስጠትን<br>◆ የመረጃ ልውውጥና በአሰራር የመደጋገፍ፣<br>◆ ለሚጠይቃቸው የትብብር ድጋፎች በጎ ምላሽ | ◆ የስራ ውጤታማነት ጥራት ማነስ<br>◆ የመልካም አስተዳደር ችግር መፈጠር | • **ከፍተኛ** |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 4 | **ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ** | ◆ የተሟላእና የተጣራ መረጃ ላይ የተመሰረተ ጥያቄ<br>◆ የታራሚዎች የባህር ለውጥን ላይ የተመሰረተ የይቅርታ ጥያቄ<br>◆ ጠንካራ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት | ◆ ተከታታይ ያለው የንቃተ ህግ እና የህግ ድጋፍ አገልግሎት<br>◆ ወቅቱን የጠበቀ የታራሚዎች የይቅርታ ጥያቄ ምላሽ<br>◆ ያልተንዛዛ ወቅቱን የጠበቀ የክስ አቀራረብ<br>◆ ተከታታይነት ያለው የታራሚዎች አያያዝና ሰብዓዊ መብት ጥበቃ ክትትል<br>◆ ቅረታን ያላስከተለ የታራሚዎች የይቅርታ አዋጅ ማሻሻያና ይቅርታ ተጠቃሚነት | ◆ ክትትልና ድጋፍ መጓደልን ያስከትላል<br>◆ ግንኙነትን ያሻክራል<br>◆ መልካም አስተዳደርና የሰብዓዊ መብት አያያዝ መጎደል ያስከትላል | በጣም ከፍተኛ |
| 5 | **ፖሊስ ተቋም** | ◆ ወቅታዊ የታራሚ ርክክብእንዲፈጸም፣<br>◆ የታራሚ መረጃ ልውውጥ እንዲኖር<br>◆ ታራሚው በጥንቃቄ እንዲጠበቅለት<br>◆ ተጨማሪ ምርመራ<br>◆ በጊዜ ቀጠሮ የገቡ ተጠርጣሪዎች በቀነ ቀጠሮቸው እንዲቀርቡ ይፈልጋሉ | ◆ ትብብርና አጋርነት ላይ የተመሰረተ መልካም ግንኙነት እንዲኖር<br>◆ ጣቢያ የታሰሩበት እንዲመጣ<br>◆ የተሟላ የቀጠሮ እስረኛና የታራሚመረጃ<br>◆ ወደ ማረ/ቤት እንዲገቡ ፍ/ቤቱ ሲወስን በዕለቱፖሊስእንዲያመጣው<br>◆ ቅንጅታዊ አሰራርና የጠንካራ የመረጃልውውጥ ስርዓት እንዲኖር | ◆ የቅንጅታዊ አሰራር ክፍተት የፍትህ ተደራሽነት መጓደል<br>◆ ጤናማ ያልሆነ ግንኙት እና መረጃ ልውውጥ ችግር መኖር<br>◆ የመልካም አስተዳደር አሰራር ችግር<br>◆ የተባባሪነት ስሜት አለመኖር | ◆ በጣም ከፍተኛ |
| 6 | **የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን** | ◆ ከሙስና የጸዳ አሰራርና ሙስናን የማይሸከም ተቋም<br>◆ ተከታታይነት ያለው የሃብት ምዝገባ<br>◆ በሙስና የተፈረደባቸን ታራሚዎች ባግባቡ ቅጣታቸው እንዲፈጸም ፣<br>◆ በተቋሙ ውስጥ በሙስና በሚጠረጠሩ ሰራተኞች አስፈላጊውን ጥቆማና መረጃ የመስጠት | ◆ ተከታታይ ያለው የግንዛቤ ማሻሻያ ስልጠና እንዲሰጥ፤<br>◆ ተቋማዊ ዕገዛና ትብብር | ◆ የተቋሙ ስም ይጎድፋል<br>◆ የክራይ ሰብሳብነት እና ሙስና በበላይነት ይነግሳል | ◆ መለስተኛ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 6 | **የገ/ኢ/ልማት** | ◆ የተፈቀደ በጀት በአግባቡ ስራ ላይ እንድውል<br>◆ ወቅቱን የጠበቀ ጥራቱን የበጀት ሪፖርት<br>◆ የፕሮግራም በጀት እቅድ፣ የስራ መርሃ ግብር ሪፖርት በወቅቱ እንዲቀርብለት<br>◆ የፋ/ንብ/አስዳደር ደንብና መመሪያ ተከትሎ መስራት፣ | ◆ ስራን ማዕከል አድረጎ የቀረበው የበጀት ጥያቄ ምላሽ ምላሽ ማግኜት<br>◆ ወቅታዊ የሆነ የስልጠናና የሙያ ድጋፍ እንዲደረግለት፣<br>◆ ወቅቱን የጠበቀ የአፈፃፀም ግብረ መልስ<br>◆ ሙያዊ ድጋፍና እገዛ<br>◆ የበጀትና የሎጀስትክ አቅርቦት ድጋፍ እንዲደረግለት፣ | ◆ የስራ መጓተት፣ የበጀት ቅነሳ ሊያጋጥም ይችላል፣<br>◆ የበጀት ምደባን ያጓትታል፣<br>◆ ግንኙነትን ያሻክራል | በጣም ከፍተኛ |
| 7 | **የፐብሊክ ሰርቪስ ኮሚሽን** | ◆ የተሻለ የአገልግሎት አሰጣጥ<br>◆ አግባብነት ያለው የምዘናና የክትትል ስርዓት እንዲኖር<br>◆ የስልጠና ፍላጎት እንዲቀርብ<br>◆ የሠው ሀይል አስተዳደር ደንቦችናመመሪያእንዲከበሩ<br>◆ የመረጃ ልውውጥ፣ | ◆ ሊያሰራ የሚችልና ወጥ የሆነ የሰው ኃይል አስተዳደር መመሪያ.<br>◆ ግልጽ የማወዳደሪያ መስፈርት<br>◆ የሰው ሃይል ልማትን ማጠናከር<br>◆ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ግልጽና ፈጣን ምላሽ ማግኘት<br>◆ ብቃት ያለው የሰው ኃይል ቅጥርና ምደባ | ◆ ፍትሃዊነትና ግልፅነት የጎደለ የአሰራር ስርዓት<br>◆ የመልካም አስተዳደር እጦት<br>◆ ግልጽ የሆነ ግንኙነት አለመኖር<br>◆ የሰው ሀይል አያያዝ ችግር | ከፍተኛ |
| 8 | **ትምህርትና ስልጠና ተቋማት** | ◆ የመማር ማስተማር ሂደት ስታንዳርድ እንዲከበርለት<br>◆ መማርና መሰልጠን የሚፈልጉ የህግ ታራሚዎችመረጃና የስልጠና ፍላጎት<br>◆ የትምህርት ካሌንደሩን የጠበቀ የመማር ማስተማር ሂደት ፤<br>◆ ታራሚ ተማሪዎች እንዲማሩ ቅስቀሳ እንዲደረግ፣ | ◆ ለማረም ማነጽ አጋዥ የሆኑ ብቁ መምህራን እንዲመደቡ፣<br>◆ የት/ት ደረጃ የማሻሻል ፍላጎት<br>◆ የት/ት ግብዓት አቅርቦት/ እንድሟላ<br>◆ የሙያ ብቃት ያላቸው የመምህራን ምደባ<br>◆ ተከታታይነት ያለው የሱፐርቭዥን ስራ<br>◆ የተሟላ የመጽሐፍ ስርጭት፣<br>◆ የተሟላ የቤተ ሙከራ ዕቃዎችና<br>◆ የቤተ መፅሐፍት አገልግሎት፤<br>◆ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ ትምህርትእንዲሰጥ | ◆ የመማር ማስተማሩ ተግባር ይስተጓጎላል፣<br>◆ የማረም ማነጽ ስራዉ ሙሉ አይሆንም:<br>◆ የት/ትና ስልጠና ጥራት መጓደል<br>◆ የማረም ማነፅ ስራ የትግበራ ጥራት ማነስ | ◆ ከፍተኛ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 9 | **የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት** | ◆ በማረ/ቤት ያሉ ታራሚዎች የቆይታ ጊዜቸውን ጨርሰው ሲወጡ ዘመናዊ የግብርና እውቀት ይዘው እንዲወጡ<br>◆ ታራሚዎች ከእርምት በኃላ በግብርና ልማት ስራ ላይ ተሰማርቶ አምራች ኃይል እንድሆኑ<br>◆ የአካባቢና የተፈጥሮ ጥበቃስራ ተሳታፍ መሆንን | ◆ የስልጠና ፣የሙያ፣የግብዓት አቅርቦት ድጋፍ<br>◆ የስልጠና ካሪኩለም የአፈጻጸም ሪፖርት<br>◆ ትብብርነት እና አጋርነትን | ◆ የስራ ጥራት መጓድል<br>◆ ድጋፍ ይቀንሳል | መለስተኛ ተጽዕኖ ያመጣል |
| 10 | **ጤና ጥበቃ ተቋም** | ◆ ጤንነቱ በአግባቡ የተጠበቀ ተገልጋይ<br>◆ ከወረርሽን ተጋላጭነት ነፃ የሆነ ማህበረሰብ | ◆ የህክምና መሳሪያና የመድሃኒትድጋፍ<br>◆ የበሽታ መከላከል ት/ት ድጋፍ<br>◆ የክትትል ድጋፍ ስራ<br>◆ የስልጠና ድጋፍ<br>◆ የባለሙያ ድጋፍ<br>◆ የወረርሽን<br>◆ አጋርነት የተቀናጀ የጋራ ትብብር | ◆ የበሽታ ስርጭት ይስፋፋል<br>◆ የዘጎት የበሽታ ተጋላጭነት መስፋፋት | በጣም ከፍተኛ |
| 12 | የሴቶች ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር | ◆ ሴቶችና ወጣቶች ወደ አመራር ቦታ እንዲመጡ<br>◆ እቅዶችና መመሪያዎች ሲወጡ የህፃናትና የሴቶችን ተዋፆኦ ያገናዘበ እንዲሆን<br>◆ ሴቶች ታራሚዎች በአግባቡ እንዲያዙ<br>◆ የሥርዓተ ፆታ እኩልነት እንዲሰርጽ | ◆ ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እንዲሰጥ<br>◆ ከእናቶቻቸው ጋር ወደ ማረ/ቤቶች የገቡ ከ18 ወራት በታች ያሉ ህጻናት ድጋፍ እንዲያገኙእናለአሳዳጊእንዲሰጡ<br>◆ በማ/ቤት ያሉ ሴቶች ህፃናት ደጋፍና እገዛ ማግኘት | ◆ የሴቶች የእኩልነት መብትና ተሳትፎ አይረጋገጥም<br>◆ ለህጻናት መጥፎ አመለካከት ይኖራቸዋል<br>◆ ተቋማዊ የአፈጻጸም ምዘናን ደረጃን ዝቅ ያደርጋል | **ከፍተኛ** |
| 13 | መንግሳታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (NGO) | ◆ የተሰጡ ድጋፍና እርዳታው በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል<br>◆ ደረጃውን የጠበቀ ፕሮጀክት የአፈጻጸም ሪፖርት | ◆ ግንኙነቱ ከፖለቲካና ከሃይማኖት ተጽእኖ የጸዳ<br>◆ ችግር ፈቺ ድጋፍ<br>◆ የሚሰጠው ድጋፍ ከሙስና በጸዳ መልኩ እዲፈጸም፡ | ◆ የድጋፍ አገልግሎቱ ሊቋረጥ ይችላል<br>◆ ግንኙነት ይሻክራል<br>◆ የተቋምገጽታ ያጎድፋል | መካከለኛ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 14 | ፌደራል ማ/ቤቶች | ◆ ወቅቱን የጠበቀ የታራሚዎች መረጃና ስታስቲክስ<br>◆ ወቅቱን የጠበቀ የደንብ ልብስ በጀት ፊሰስ እንድደረግ<br>◆ ወቅቱን የጠበቀ የመረጃ ልውውጥ<br>◆ በሪፌራል የተላኩ ታራሚዎችን ህክምና እንደጨረሱ በወቅቱ እንዲወስዱ፤የተሻሉ ተሞክሮዎች | ◆ የታራሚዎች መረጃና ስታስቲክስ<br>◆ የሎጅስቲክ አቅርቦት ድጋፍ<br>◆ የተሻሉ ተሞክሮዎች<br>◆ ስልጠናና የሙያ ድጋፍ እንዲደረ<br>◆ ጥራቱን የጠበቀ የደንብ ልብስና ትጥቅ ግዥ | ◆ ግንኙነት ይሻክራል<br>◆ ወጥ አሰራርአይኖርም<br>◆ በመረጃ ጥራትና በርስ በርስ ግንኙነት ተጽእኖ ያመጣል | ከፍተኛ |
| 15 | የሚዲያ ተቋማት | ◆ ግልፅ ጥራትና ወቅቱን የጠበቀና የተሟላ መረጃ | ◆ የተቋሙን ገፅታን ልያጎለብት የሚችል መረጃ ለማህበረሰቡ ተደራሽ እንድሆን<br>◆ ጤናማ የስራ ግንኙነትመኖር<br>◆ ፍትሃዊ የአየር ስዓት ሽፋን እንዲኖር<br>◆ የሙያ ድጋፍና እገዛ | ◆ የመረጃ ተደራሽነት ተፅዕኖ የተቋሙ ገጽታ ግንባታ ማጉደፍ | ◆ ከፍተኛ |
| 16 | ጥቃቅንና አነስ ተኛሥራዎች ማስፋፊያኤጀን ሲ | ◆ በማረ/ቤት የተደራጁ ታራሚዎች መረጃ ዝርዝር መረጃ | ◆ በማረ/ቤቶች ታራሚዎች ተደራጅተው ወደ ሥራ እን ዲሠማሩና የስልጠናና የግብዓት የሙያ ድጋፍ | ◆ የዕውቀት ሽግግር አለመኖር | ◆ መካከለኛ |
| 17 | ዩኒቨርስቲዎች ና ኮሌጆች | ◆ ጥናት ለማድረግ ምቹ ሁኔታ፤<br>◆ ለሚሰጡ የትምህርት እድሎች በት/ሚ/ር መስፈርት መሰረት ምልመላ<br>◆ በአግባቡ የተለየ ተቋማዊ ፍላጎትና ጥያቄ | ◆ ነጻ የትምህርት፤ የሙያ ድጋፍ፤ አጫጭር የባለሙያ ስልጠናና ጥናት<br>◆ አቅም ያለውና ተወዳዳሪ የሰው ሀይል እንዲኖር<br>◆ የማህበረሰብ ድጋፍ አገልግሎት<br>◆ ጥራት ያለው ጥናትና ምርምር ስራ እንድካሄድ<br>◆ ተቋማዊ ችግር መፍታት የሚችል የፐሮጀክት ቀርፃ ስራ | ◆ የተባባሪነት እና የጋራ ተግባቦት ችግር | ◆ መጠኘኛ |
| 18 | ሙያና ቴክኒክ ኤጀንሲና ኮሌጆች | ◆ ሙያና ቴክኒክ ስልጠናዎች ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ይፈልጋል | ◆ የቴክኒክና የሙያ ድጋፍ<br>◆ ለታራሚዎች የዕውቀት ሽግግር የሚፈጥር ስልጠና<br>◆ የስልጠና ቁሳቁስ ድጋፍ<br>◆ የሙያና ቴክኒክ ደረጃን ያሟሉ ማሰልጠኛዎች እንዲኖሩ የማገዝ<br>◆ የስልጠና ካሪኩለም | ◆ የታራሚዎች የመሰልጠን ፍላጎት ማጣት<br>◆ የሥራ እድል ያሳጣል<br>◆ በታራሚዎች ዘንድ ተስፋ የመቁረጥ ስሜት እንድፈጠር | ከፍተኛ |

1.4.3. የተባባሪ አካላት ትንተና

| ተ/ቁ | ተባባሪዎች | ከአስተዳደሩ ጋር የሚኖረው የትብብር ዘርፍ/መስክ/ የሚመለከታቸው ሁኔታዎች | የሚያስገኘው ጠቀሜታ |
|---|---|---|---|
| 1 | መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፤ ፕርዝን ፎሎ ሽፕ ኢትዮያ አለም አቀፍ የቀይ መስቀል ማህበር (ICRC)፣ ከሌሎች የሰብአዊ መብት ጥበቃና መሰል ተቋማት፣ | ◆ ለሥልጠናና ትምህርት፣ ለታራሚዎች የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያዎች የገንዘብና ቁሣቁስ እገዛ ማግኘት፣<br>◆ በታራሚ አያያዝ ዙሪያ ግብአቶች በማቅረብ፣ ስልጠናው የአለም አቀፍ ልምዶችን ያገናዘብ የታራሚ አያያዝን ስርዓት እንድፈጠር ማድረግ<br>◆ ወቅታዊ ጉብኝት በማድረግና በስታንዳርዱ መሠረት እንዲሰራ አስተያየት በመስጠት ማረ/ ቤቱን ማገዝ፣<br>◆ የአስተዳደሩን ራዕይ ተልዕኮና እሴቶች ለማሳካት ልዩ ልዩ እገዛና ድጋፍ ሲያበረክቱ ገንቢ አስተያየቶቻቸውን መቀበልና የአስተዳደሩን ተልዕኮ ማስፈጸም፣ | ◆ አስተዳደሩ በሚያከናውናቸው የማሠልጠንና አገልግሎት የማሻሻል ተግባር ላይ በከፍተኛ ደረጃ ተሳታፍ መሆናቸው የስራ ውጤታማነትን ያስገኛል<br>◆ አስተዳደሩ አለም አቀፍ ልምድን ያጐለበተ፣ የታራሚ አያያዝ ስታንዳርዳይዜሽን መሠረት እንዲያከናወንና ሙያዊ ድጋና እገዛ ይሰጣሉ<br>◆ አስተዳደሩ ለዓላማው መሳካት አጋዥ ከሚሆኑ ተቋማት ጋር ተቋማዊ ትስስር በመፍጠር የታራሚው የሰብአዊ መብቶች እንዲከበሩ ማድረግና የተቋሙንና የአገሪቱን መልካም ገጽታ መገንባት፣ |
| 2 | የተለያዩ የክልል ሴክተር መ/ቤቶች፣መብራት ሃይል፣ውሃ ልማት ፣ቴሌኮሙኒኬሽን፣ከተማ ልማት ፤ባንክ፣የበጎ አድራጉት ማህበራት | ◆ ከማረምና ተሃድሶ ተግባራት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት በትብብር ማከናወን፣<br>◆ የማረ/ቤቱን የፕሮጀክት ሥራዎች ክትትል ስራ በማከናውን ማከናወን፣ | ◆ አስተዳደሩ ከተለያዩ ሴክተርና ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣እንዲሁም ከክልል ቢሮዎች ጋር የተቀናጀ የሥራ ትብብር እንዲፈጠር ያደርጋል፣ |
| 3 | የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ፣የክልል ፖሊስ ማሰልጠኛ ተቋም | ◆ መኮንኖችንና ሌሎች ባለሙያዎችን በማሰልጠን የቁሳቁስ፣ የባለሙያ፣ የመረጃ ልውውጥና የቤተመጽሐፍት አገልግሎት መስጠት፣ | ◆ በአስተዳደሩ የትምህርት ስልጠናና የምርምር ተግባራትን በማገዝ የሙያና የመረጃ ልውውጥ ድጋፍ ያደርጋል፣ |
| 4 | የክልል የሥራ አመራር ኢንስቲትዩት፣ | ◆ ለከፍተኛ፣ ለመካከለኛ ለድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች የአጫጭር ጊዜ ስልጠና መስጠት፣ | ◆ የአስተዳደሩን የሰው ሃብት ልማት እና የአቅም ግንባታ ተግባራት ማገዝ፣ |
| 5 | የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጆች፣ ሆስፒታሎች፣ | አስተዳደሩ በሚፈልጋቸውና በተመረጡ አጫጭርና የረዥም ጊዜ የስልጠና ሂደቶች ላይ የቴክኒክና የምክር አገልግሎት መስጠት፣<br>የሰው ሃብት ልማትን በረዥም ጊዜ ሥልጠና፣ ዘርፉን በሚመለከት የምርምር ሥራዎች፣የህክምና አገልግሎት፣የቴክኒክናሙያዊእገዛማድረግ፣ | ◆ በየደረጃው የሰለጠነ የሰው ኃይል፣ የቴክኒክና የምክር አገልግሎት ያስገኛል፣<br>◆ በከፍተኛ ደረጃ በሰለጠነ የሰው ኃይል በተከናወኑ የምርምር ሥራዎች ተጠቃሚ መሆን፣ |
| 6 | ◆ የሬዲዮ፣ የቴሌቪዥንና የኘሬስ ድርጅቶች፤ | ◆ የአስተዳደሩን የሥራ እንቅስቃሴ የሚገልጽ ወቅታዊ የማረሚያ ቤትና ተዛማጅ ጉዳዮችን ለሕብረተሰቡ በማሳወቅና በማረምና ማነጽ ተግባራት ላይ ሕዝብን ለማሳተፍ ግንዛቤ መፍጠር፣ | ◆ የማረሚያ ቤቱን ዓላማና ተግባር በማስተዋወቅ የሕብረተሰቡን ግንዛቤ ማስፋትና ወደ ኮሚዩኒቲ ሰርቪስ ለማሸጋገር ቅድመ ዝግጅት መፍጠር፣ |

## 1.5. የተቋሙ ጥንካሬ ፣ ድክመት ፣ መልካም አጋጣሚና ስጋቶች ትንተና፤

### 1.5.1. የጥንካሬና ድክመት መግለጫዎች፡-

| ተ ቁ | መለኪያ | ጥንካሬ | ድክመት |
|---|---|---|---|
| 1 | የስትራቴጂክ አመራር ብቃት | ◆ የ2ኛ ዙር የአምስት ዓመት (2008-2012) ስትራቴጂያዊ ዕቅድ በማውጣት እና ከስትራቲጂክ ዕቅድ መነሻ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ የተግበባር አፈፃፀም ዕቅድ ተዘጋጀት መተግበሩ፣<br>◆ ተቋሙ የነበረበትን ነባራዊ ሁኔታ በመረዳትና የአመራር፣ አደረጃጀትና አሰራር ችግሮች በጥናት ለይቶ መፌታት የተተደረገ ጥረት መኖሩ፣<br>◆ የተቋሙ የተልእኮ አፈጻፀም በስትራቴጂያዊ ቅኝት ግምገማ ማካሄድ መጀመሩ<br>◆ ሰብአዊ መብት አያያዜ ጉዳዮች ትኩረት ተሰጥቶ መሥራት መጀመሩ፣<br>◆ የተቋሙ የተልእኮና ዕቅድ አፈፃፀም ከመንግስት የለውጥ አጀንዳ ጋር ከማስተሳሰር ጥረት መደረጉ<br>◆ ፈፃሚውንና መካከለኛ አመራሩን በስልጠናና ትምህርት የማብቃት ጥረት መደረጉ<br>◆ የሴት አመራር ሺፋን የማሳደግ ጥሬቶች መጀመራቸው<br>◆ ለተቋሙ በመንግስት በኩል የተሰጠውን ትኩረት አቅጣጫኝ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከተለየዩ አካላት ጋር ግንኙነት በመፍጠር የተቋሙ ልዩ ልዩ ችግሮች ለመፍታት ከፍተኛ ጥረት ጅምር መደረጉ፣<br>◆ ተቋሙ የነበረበትን ነባራዊ ሁኔታ የሪፎርም ስራዎች አተገባበር በጥናት ላይ ተመሰርተው እንድሰራ በማድረግ የአመራር፣አደረጃጀትና አሰራር ችግሮች ለመፍታት የተደረገ ጥረት ውጤት ማስመዝገብ መጀመሩ፣ | ◆ የአምስት ዓመቱ (2008-2012)የእትእ (ስትራቴጂክ) እቅድ በታቀደው ልክ እንዲተገበር የተሟላ አመራር በመስጠት ፣ዕቅዱ በጥራት እንድተገበር ያለማድረግ<br>◆ አመራሩ የተረጋጋና ቀጣይነት ያለው የአመራር ሚና የሚጫወት ስትራቴጂክ አመራርን ሆኖ ስራን በበላይነት የመምራት ውስንነት መኖር<br>◆ አመራሩ በደራሽ ስራዎች በመጠመድ ስትራተጅያዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥቶ ያለመስራት፣<br>◆ የተጀመሩ የሪፎረም ስራዎች የታሰበው ውጤት እንድያስገኝ በቁርጠኝነት የመስራት ክፍተት መኖር<br>◆ ጥራት ባለው መረጃ ላይ የተመሰረተ የክትትልና ድጋፍ አለመተግበር፣<br>◆ በጸደቀው መዋቅር ላይ ወጥነት ያለው ምደባ ሰጦ ወደ ስራ የማስገባት ክፍተት መኖር<br>◆ የመዋቅሩን ክፍተት በየጊዜው እየተገመገመ ክፍተቶቹ ተለይቶ የማስተካከያ እረምጃ የመወሰድ ክፍተት መኖር |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 2 | **አሰራርና የአመራር ስልት** | ◆ ሀገራዊና ክልላዊ የለወጥ ስራ እንቅስቃሰዎች በተቋም ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ የሚደረግ ጥረት አበረታች መሆኑ / የተቋማዊ ስትራተጂክ ዕቅድ በሚዛናዊ ውጤት ተኮር ምዘና ስርዓት ተዘጋጀቱ<br>◆ በየደረጃው ያለው አመራር የጋራ አመራር የአሳታፊነትና የቅንጅት አሰራርን በመከተል የየበጀት ዓመቱን ዕቅድ ለማሳካት የሚያደረገው ጥረት መድረጉ ፣<br>◆ ከሰራተኞች /አባላት እና ታራሚዎች የሚነሱ ግልጽ የቅሬታ አቀራረብ እና አፈታት አሰራር በማዘጋጀት ተገቢው ምላሽ መስጠት መቻሉ ፣<br>◆ የሰራተኞች የመብት ጥበቃና አያያዝ እየተሻሻለ መምጣቱ ፣<br>◆ የአሰራር ስርዓት ማነቆ ሆኖ የቆየ የማ/ቤት ቤት የፑል አሰራር ችግር መፍታት የሚያስችል አሰራር እንድፈጠር መደረጉ<br>◆ ከፍትህ አካላት፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ፤ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር ቅንጅታዊ አሰራሮችን በመፍጠር የተባበባሪነት እና የበጎ አሰራሮችን የማሳደግ በጎ ጅማሮ መኖሩ | ◆ የተዘረጉ የውጥ መሳሪያዎችን በአግባቡና ቀጣይነት ባለው አግባብ ተግባራዊ ያለማድረግ<br>◆ ወጥ የሆነ የማትጊያና የሽልማት ሥርዓት አለመኖር፣<br>◆ የክትትል ድጋፍና ግምገማ ስርዓቱ በጥራትና በውጤት ላይ ያተኮረ አለመሆን፣<br>◆ የሕብረተሰቡን ተሳትፎና እርካታ ደረጃ የሚለካበት ቋሚና የተሟላ የመረጃ ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣<br>◆ በጀት አጠቃቀም የተጠናከረ ቁጥጥርእና ክትትል ፣<br>◆ ከሰራተኞች /አባላት እና ታራሚዎች የሚቀርቡ ቅሬታዎች በእቅድ ተይዞ አለመሰራቱ፣የመልካም አስተዳደር ችግርን በዘላቂነት መፍታት የሚያስችል አሰራር አለመኖር<br>◆ ከሌሎች የፍትህ አካላት አገልግሎት አሰጣጥ ጋር የተያያዙ በውሳኔ ግልባጭ በወቅቱ አለመምጣት፣የፖሊስ ጣቢያ የቆይታ፣ በይግባኝ ቀጠሮ እና የውሳኔ አሰጣጥ መዘግየት፣ በቅጣት ገንዘብ ማስፈጸም፣ የዝውውር ጉዳዮች በአፈጻፀም የሚታዩ ችግሮች፣<br>◆ ከአጋርአካላት ጋር በትብብር ከመስራት አንጻር አሟጦ አለመጠቀም ፣ |
| 3 | **የጥበቃና ደህንነት ተግባራት** | ◆ በሃገር ደረጃ የተፈጠረውን አለመረጋጋትና የመልካም አስተዳደር ችግርን መንሰኤ አድረጎ በማ/ቤቶቻችን የተፈጠሩ ግርግር ተከትሎ የተለያዩ የታራሚ ሁከቶችን ምንም ዓይነት ተፅዕኖ ሳያስከትል መቆጣጠር መቻሉ፤<br>◆ የጥበቃና ደህንነት ተግባራት የዜጎችን ሰብዓዊ መብት ለማክበር እና ለማስከበር በሚያስችሉ ሁኔታ ተግባራዊ መደረጋቸው<br>◆ የማረሚያ ቤቶች ለጥበቃና ደህንነት ለማስተዳደርና ለማረም ማነጽ አገልግሎት ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ ሁኔታ አደረጃጀቱ እነንድስተካከል መደረጉ | ◆ የጥበቃና ደህንነት ስራውን በሎጅስትክ አቅርቦት እና በቴክኖሎጂ አሰራር የተደገፈ አለመሆን<br>◆ ከስራው ስፋት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የሰው ኃይል አቅርቦት አለመኖር<br>◆ በተግባር አፈፃፀም በአባላት ዘንድ ጎልቶ የወጣ የስነ- ምግባር ችግር መኖር የተከለከሉ ነገሮችን ወደ ማ/ቤት የማስገባት ፤ለታራሚዎች ማምለጥ እና መሰል ችግሮች መንሰኤ መሆኑ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 4 | ማረም ማነፅና ተሃድሶና ልማት | ◆ በተሃድሶና ልማት ታራሚዎችን ከማረጋጋት ፣ከማረምና ማነፅ ፣ወደ ትምህርትናስልጠና ከማሳተፍና በማህበራት አደራጅቶ ወደ ስራ ከማስገባት አኳያ ለውጦች መምጣታቸው፣<br>◆ በማረምና ማነፅ ስራ የውጤታማነት ከአጋርና ተባበባር አካላት ጋር የተጀመሩ የጋራ ቅንጅት አበረታች መሆናቸው<br>◆ ታራሚዎችን በግብርና ልማት ለማሰልጠንና ታራሚዎችን በግብርና ልማት ስራ ስምርት ላይ በማሳተፍ ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ የግብርና ልማት ስራዎች ለማ/ቤቱ የውስጥ ገቢ አቅምን በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፆ ማበረከታቸው<br>◆ ታራሚዎች ተከታታይነት ያለው የምክር አገልግሎት፤የስነ-ምግባር ማሻሻያ ት/ት አገልግሎት እየተሰጣቸው መሆኑ | ◆ በማህበር ለተደራጁ ታራሚዎች የመስሪያ ቦታ የገበያ እና የጥሬ እቃ አቅርቦት ችግር<br>◆ መሰልጠንና መማር በስራ መሰማራት የሚችለውን የታራሚ አቅም በመለየት አገልግሎቱን ተደራሽ አለማድረግ፤<br>◆ በተለያዩ ሙያ መስክ የሰለጠኑ ታራሚዎች በሰለጠኑበት ሙያ መስክ ወደ ስራ ማስገባት የሚስችል ስርዓት ዘርጎቶ ታራሚውን ወደ ስራ አለማስገባት<br>◆ ለማረም ማነፅና ተሃድሶ አገልግሎት መስጫ የሚውል የተደራጀ የስልጠና ማዕከል አለመኖር<br>◆ ከአጋር አካላት ጋር በትብብር ለመስራት ያለውን አቅም አሟጦ አለመጠቀም ክፍተት መኖር |
| 5 | የመሰረታዊ ፍላጎትና የአገልግሎት አሰጣጥ | ◆ ለታራሚዎች ስለሚሰጡ አገልግሎቶች /ምግብ አልባሳትና መጠለያ፣ የህክምናና የሳኒቴሽን የማህበራዊ አገልግሎት ድጋፍች አሳታፊነት ፍትሃዊነት ወቅታዊነትና ጥራት በጠበቀ መልኩ ተደራሽ ለማድረግ የማሻሻል ጥናት መደረጉ፤<br>◆ የቅድመ በሽታ መከላከልና የህክምና አገልግሎት ከፍተኛ መሻሻል መታየቱ፣<br>◆ በታራሚዎች መሰረታዊ ፍላጎት አቅርቦት ተደራሽነት ላይ ጫና የፈጠረ የፑል አሰራር ችግር እንድፈታ መደረጉ | ◆ የመሰረታዊ ፍላጎት አቅርቦት ጥራት ተደራሽነት በጠበቀ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ ሀገራዊ የገበያ አለመረጋገት አሉታዊ ጫና ማስከተል መቻሉ ለማድረገ<br>◆ የተቋሙ አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል የተሰሩ ስራዎችና የታራሚው / ህብረተሰቡ ፍላጎት ጋር በበቂ ጥናት የተመሰረተና የተመጣጠነ አለመሆኑ<br>◆ በተቋሙ የሚሰጡ አገልግሎቶች የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ ያልወጣላቸው መሆኑ ፣<br>◆ የህክምና አግልሎት ተደራሽነትን ለማረጋገጥ የግብዓት አቅርቦት አለመሟላት፣ የሪፌራል አሰራር ስርዓቱ ክፍተት ያለው መሆን፣ |
| 6 | የታራሚዎች ፍትህ አስተዳደር ስርዓት | ◆ ሀገራዊ የለውጥ እንቅስቃሰ መሰረት በማድረግ በማ/ቤት ለሚገኙ ታራሚዎች ይቅርታ እንድደረግ መደረጉ<br>◆ ታራሚዎች ለእርም በሚሰጡት አዎንታዊ ምላሽ ተመዝኖ የአመክሮ ተጠቃም እንድሆኑ መደረጉ<br>◆ ከታራሚዎች የሚቀርቡ የዝውውር፤የእርቅ ጥያቄዎች ወቅታዊ ምላሽ እንያገኙ መሆኑ<br>◆ የመደበኛና ጊዜ ቀጠሮ ታሳርዎች የቀጠሮ ክትትል ስርዓት እየተሻሻለ መምጣቱ | ◆ በሀገር ደረጃ ወጥ የይቅርታ አዋጅ አለመኖር<br>◆ ከማ/ቤቶች የሚቀሩቡ የታራሚዎች አመክሮ ጥያቄ በፍ/ቤቶች በኩል በወቅታዊና ፈጣን ምላሽ አለማግኜት<br>◆ የታራሚዎች የዝውውር ፤የእርቅ ምላሽ በተቋማትና በግለሰቦች በጎ ፍቃድ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ በታራሚዎች ፍላጎት መጠን ተፈፃም አለመሆን<br>◆ የቀጠሮ መዘገየት ችግሮች ሙሉ በሙሉ አለመቀረፍ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 7 | **የስትራቴጂክ አፈፃፀም ክትትል ግምገማ ድጋፍ** | ◆ ከተቋም ስትራቴጂክ ዕቅድ መነሻ ዓመታዊ የአፈፃፀም ዕቅድ ዝግጅት ትግበራ ፤የአፈፃፀም ሪፖርትዝግጅት ስራ በወቅቱ እንድካሄድ<br>◆ የተቋሙን ፕሮግራም መሰረት በማድረግ የየዓመቱ የበጀት ፍላጎት ዕቅድ በማቅርብ በጀት የማስፈቀድ የተፈቀደውን በጀት የመምራትና አፈጻጸሙን የመከታተል ስራ መሰራቱ፣<br>◆ የዕቅድ አፈፃፀም ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የመስክ ክትትልና ድጋፍ ስራዎች በማከናወናወን ያሉ ክፍተቶች ለማስተካከል ጥረት መደረጉ፡ | ◆ የዕቅድ ዝግጅት በአግባቡ በተሰበሰበ፣ በተደራጀና በተተነተነመረጃ ላይ የተመሰረተ ያለመሆን፣<br>◆ በዕቅድ የተያዙ ስራዎች በትክክል እንዲተገበሩ የሚደረገዉ የድጋፍ፣ ክትትልና የቁጥጥር ስራዉ በቂ ያለመሆን፣<br>◆ የሪፖርት ዝግጅት ጥራት ውንንነት መኖር<br>◆ የመስክና ክትትልና ድጋፍ ስራዎች ችግር ፈቺ አለመሆኑ፤<br>◆ የተጠያቂነት አሰራር ላይ ክፍተት መኖር፣ |
| 8 | **የፋይናንስ አሰራር አፈፃፀም** | ◆ የዓመቱ ለስራ ማስኬጃ ፣ለደመወዝና ለካፒታል ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚመደበው በጀት እያደገ መምጣቱ ፣ | ◆ የፋይንስ አስተዳደር ስርዓቱን በአግብቡ ለመከታተተል ወቅቱን የጠበቃ የበጀት ሪፖርት ስርዓት አለመኖር<br>◆ ግዢዎች በወቅቱ አለማከናወን ፣የጥራትና የዋጋ መጋነን መስተዋሉ፣<br>◆ የካፒታል ፕሮጀክቶች አፈፃፀም መዘገየት (የጫራታ ሂደት፤ የኮንትራክተሮች ስራ መጓተት)፤<br>◆ የበጀት እጥረት፣<br>◆ በጀትን በተገቢው የመጠቀምና የማስተዳደር አቅም ውስንነት መኖር<br>◆ ከረጂ ድረጅት የሚገኝ የሀብት ምንጭ አለመኖር |
| 9 | **የሰው ሀብት ስራ አመራር** | ◆ የአስተዳደሩ የሰው ኃይል የማረሚያ ፖሊስ አባላትና ሲቪል ሰራተኞች ሁሉም የተቋሙ ስራዎች የሚተገብርና ተልዕኮ የመፈፀም ፍላጎት መኖር<br>◆ ተቋማዊ የሪፎርም ስራን ተከትሎ አዳዲስ አመራሮችን ወደ ሃላፊነት ማውጣት መቻሉ<br>◆ የማረም ማነጽ የታራሚዎች ሰብዓዊ መብት ጥበቃ፣ የስነ-ምግባር ዙርያ የሚታዩ ክፍተቶችና ሌሎች የአቅምና የማስፈጸም ጉድለቶች ማረምና ማስተካከል የሚያስችል ስልጠናዎች መሰጠታቸው ሉ፣ | ◆ የተደራጀ የሰው ኃይል ልማት አለመኖር ፣<br>◆ በሰራተኛው/ማረ/ፖሊሱየአገልጋይነት መንፈስ ማነስእና የስነምግባር መጓደል፤<br>◆ የስነ ምግባር ግንባታ ስራ ዝቅተኛ መሆን፤ |

1.5.2. የመልካም አጋጣሚና ሥጋት መግለጫዎች

| ተቁ | መለኪያ | መልካም አጋጣሚ | ስጋቶች |
|---|---|---|---|
| 1 | ፖለቲካዊ ሁኔታዎች | ◆ አገሪቱ በከፍተኛ የለውጥ ሂደት ውስጥ በመሆኗ አላሰራ ያሉ አሰራሮችን ለማሻሻል ምቹ ሁኔታዎች ስለመኖራቸው<br>◆ የፖለቲካ ምህዳሩ እየሰፋ በመምጣቱ የዜጎች ሁሉአቀፍ ተሳትፎ ማደግ ፣<br>◆ የፍትህ አካላት በጋራ ጉዳዮች በጋራለመንቀሳቀስ /የመደጋገፍ/ በዓብይ፣በጥምርናበቴክኒክኮሚቴዎች በጋራ የሚሰሩበት አግባብ መኖር<br>◆ ያልተማከለ አስተዳደር መኖሩ፣ የፌዴራል ስርዓቱ ለክልሎችና የፍትህ ተቋማት ነጻነት<br>◆ የፍትህ ተቋማት (ፍ/ቤቶች፣ ፖሊስ፣ ዓ/ህግ ማረ/ቶች)ከፖለቲካ ነፃና ገለልተኛ እንዲሆኑ መደረጉ፣<br>◆ ከአገሪቱ ሁኔታ አኳያ በክልሉ አንፃራዊ ሰላም መኖሩ ፣<br>◆ በተለያዩ ምክንያቶች የሚቀሰቀሱ ግጭቶች፤ አለመረጋጋት ;<br>◆ ህገ ወጥ እንቅስቃሴዎች ፖለቲካዊ መፍትሄ በመስጠት በዘለቄታዊ ለመፍታት የሚያስችል አቅምያለመሆኑ፣ | ◆ የተቋማዊ ሪፎርም ሂደቶች በተፈለገው ፍጥነትና ጥራት አስኪዶ ውጤት ለማስመዝገብ የሚደረገው ጥረት (በሪሶርስና በሌሎች ውጫዊ ሁኔታዎች) መቀዛቀዝ የሚታይበት መሆኑ፣<br>◆ የተፈጠረውን የፖለቲካ ምህዳር አላግባብ በመጠቀም ሀገራዊ አንድነትን የሚሸረሽሩ አስተሰሰቦች መኖር ለወንጀለኞች ቁጥር መጨመር መንስኤ መሆን<br>◆ ህብረተሰቡ በማረሚያ ቤቶች ላይ ያላቸው አመለካከት ስልጣን ላለው ፓርቲ ፖሊሲዎች ስትራቴጂዎችን ማስፈጸሚያ የማየት አዝማሚያ መኖሩ፣<br>◆ በተፈለገው ደረጃ በጋራ ጉዳዮች የመደጋገፍና ችግሮችን ለመፍታት ትኩረት አለመስጠት ሊታይ ይችላል፤<br>◆ ወጥ የሆነ የፍትህ ተቋማት አሰራር ባለመኖሩ ወጥ የታረሚዎች አያያዝ አለመኖር የታራሚዎች የይቅርታ ተጠቃምነት የዝውውር ጥያቄ ሊበዛ እርካታም ሊቀንስ ይችላል።<br>◆ ከሁኔታዎች መለዋወጥ የመንግስትና ሌሎች አካላት በማረሚየ ቤቶች ላይ ጣልቃ ገብነት ሊከሰት ይችላል፤<br>◆ የሚከሰቱ ግጭቶች በሀገራዊና ክልላዊ ሠላምና ደህንነት ላይ ስጋት የሚደቅን መሆኑ<br>◆ በህገ-ወጥ እንቅስቃሴዎች መከሰታቸው፣ችግሩን በሃይል ለመፍታት በሚደረግ ሂደት አዳዲስ ጥያቄዎች በማስነሳት ወደ ግጭት የሚያመሩ ሁኔታዎች መኖር |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 2 | ኢኮኖሚያ ዊ ጉዳዮች | ◆ በሀገሪቱ እየተመዘገበ ያለው ተከታታይ የኢኮኖሚ ዕድገት ለዜጎች የስራ እድል በመፍጠር ከፍተኛ ድርሻ እያሳየ መሆኑ፣<br>◆ ለማረ/ቤቶች ከመንግስት የሚመደበው በጀት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱ፣<br>◆ ከተለያዩ ተቋማት ጋር ትስስር በመፍጠር ተጠቃሚነትን ለማስፋት ምቹ ሁኔታ መኖሩ፣ | ◆ የግብዓት፣ የምርትና አገልግሎት ዋጋ የዋጋ ንረት /ግሽበት ከፍተኛ በመሆኑ በበጀት አጠቃቀም ላይ የሚያስከትለው ተፅዕኖ ከፍተኛ መሆኑ፣<br>◆ በየአካባቢው በሚፈጠሩ ግጭቶች አምራች ሃይሉ ተረጋግቶ ማምረት አለመቻል፣ የስራ አጥ ቁጥር መብዛት ወጣቱም ወደ አድማና ብጥበጥ ሊያመራ ይችሉ፡፡<br>◆ ከታራሚዎች የምግብ አቅርቦት ጋር ተያይዞ የገበያ ዋጋ ንረት ሊያጋትም ይችላል፡፡ |
| 3 | ማህበራዊ ጉዳዮች | ◆ በህገ መንግሥቱ ሁሉም እምነቶች፣ አመለካከቶችና እሴቶች እኩል እውቅና የተሰጣቸው፣በነጻነት የሚከበሩ በመሆኑ ከሃይማኖትና ዕምነት ጋር የተያያዙ ግጭቶች ለማስወገድ ህ/ሰቡ በጋራ የመመከት ባህል ያደገ መሆኑ፤<br>◆ ሕብረተሰቡን ያሳተፈ የእርምት ስርአት ለመዘርጋት ምቹ ሁኔታ ያለ መሆኑ፣<br>◆ ህብረተሰቡ ህግና ሥርዓት አክባሪ መሆኑ፣ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቶች መኖራቸው ለሚፈጠሩ ግጭቶች ህግን ከማስከበር ጎን ለጎን በእርቅ ለመፍታት መቻሉ ፣<br>◆ የብዘሃን መገናኛ መስፋፋት እና ለተቋም ገጽታግንባታን ለማረም ማነጽ ስራ አጋዥ እየሆኑ መምጣታቸው | ◆ የተከሰቱ የአክራሪነትና ጽንፈኝነት አዝማሚያዎች በሚያሳድሩት ጫና በአንዳንድ አካባቢዎችና የእምነት ተከታዮች የሚታየው አፍራሽ እንቅስቃሴ የዜጐችን መቻቻልና አብሮነት በመሸርሸር ለወንጀለኞች መጠቀሚያ ሊሆን ይችላል፡፡<br>◆ ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ፣ አደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚነት፣ጎጂ የሆኑ የውጭ ባህሎች እምነቶችና አመለካከቶች ወደ ሀገርውስጥ ማስገባትና ማስፋፋት፣<br>◆ በአለምና በሀገር ደረጃ የተከሰተ ወረርሽኝ በሽታ ወደ ማረሚያ ቤት ሊገባ ይችላል፡፡<br>◆ በጊዜው እየተከሰቱ ያሉ ሀገራዊ አንድነትን የሚሸረሽሩ አስተሰሰቦችና ተግባራት አብሮነተን በመሸርሸር የህብረተሰቡን እሴቶች ለማስረጽና ወደነበረበት ለመመለስ አስቸጋሪ መሆን፣<br>◆ የብዘሃን መገናኛ መስፋፋት ህዝቦች እርስ በርስ ግጭት መስፋፋት በህብረተሰቡ ከሚነሱ ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊና ሌሎች ጥያቄዎች አመካኝነት እየጋለ ከሚበርደው የአገራችን ወቅታዊ ሁኔታ አኳያ (የፀረ ሠላም ኃይሎችና ህገ-ወጦች መበራከት ጋር ተያይዞ) የዜጐችን መቻቻልና አብሮነት በመሸርሸር ለወንጀለኞች መጠቀሚያ መሆን፣ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ዜጎች ከቀያቸው መፈናቀልና መሰደድ መንስዓ መሆን ይችላል፤ |
| 4 | ቴክኖሎጂ ያዊ ጉዳዮች | ◆ አገሪቱ በሁሉም ዘርፎች የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መስፋፋትና ዘመናዊ አሰራር እያደገ መምጣቱ ፣ስራዎች በቴክኖሎጂ ለመደገፍ ምቹ ሁኔታ መኖሩ፤<br>◆ በኢን ፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መረጃን ለመለዋወጥ፣ አቅምን ለመገንባት ከፍተኛ ድርሻ መወጣት መቻላቸው፣ | ◆ ከቴክኖሎጂው መራቀቅና እድገት ጋር የወንጀል አይነቶች ውስብስብነትና መበራከት ፣ለማረምና ለማነጽ የተለየ አደረጃጀትና ዘመናዊ አሠራር ስለሚጠይቅ ለዚህ የተዘጋጀ ተቋም አለመኖር፣<br>◆ በቴክኖሎጂ ታግዘው የሚሰጡ አገልግሎች አለመኖር |
| 5 | ሕጋዊ ሁኔታዎች | ◆ የታራሚዎች አያያዝ ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌ ያለው መሆኑ<br>◆ ኮሚሽኑ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፍነት መፈፀም የሚያስችል አዋጆች፣ደንቦች፤መመሪያና የአሰራር መመሪያ ያለው መሆኑ | ◆ በተቋሙ የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያና የአሰራር ማኑዋል በሁሉም ዘንድ የጠራ ግንዛቤ የማስያዝ ክፍተት መኖር |

## 1.6. አስቻይና ፈታኝ ሁኔታዎች፣

### 1.6.1. አስቻይ ሁኔታ፡-

| | አስቻይ ሁኔታዎች፣ | አስቻይ ሁኔታዎችን የመጠቀሚያ ስልት፣ |
|---|---|---|
| 1 | ◆ የሚያስራ ሕገ መንግሥትና ገልፅ የሆኑ ሀገራዊ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች መኖራቸው፣ | ◆ የታራሚዎችን ሰብዓዊ መብት ማስክበርና ማክበር የሚያስችል ሕገ መንግሥቱንና ሕገ መንግሥታዊ ስርዓቱን፣<br>◆ ሕገ መንግሥቱን ተከትለው የወጡ ህጎችና የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ከተቋሙ ተግባርና ሃላፊነት ጋር አጣጥሞ በመተግበር፣ |
| 2 | ◆ በሪፎርም ሂደት አሰራሮችን ለማሻሻል፣ አቅም ለመገንባትና ምቹ ሁኔታዎች ስለመኖራቸው | ◆ የአመራሩንና የፈፃሚውን አቅም በመገንባት፣ |
| 3 | ◆ የፍትህ ሥርዓት ግንባታ እና መልካም አስተዳደር የመገንባት የመንግስት የትኩረት አቅጣጫ መሆኑና | ◆ የፍትሕ ስርዓት ማሻሻያና ሌሎች ፕሮግራሞችን ተግባራዊ በማድረግለማረም ማነጽ ስራ መጠቀም፣<br>◆ ለተቋሙ ተልዕኮ ተግባራዊነት ከፍትሕ አካላት ጋር ተቀናጅቶ በመስራት፣<br>◆ ማስፈፀሚያ ሕጎችና ደንቦችን የአሰራር ስርዓት በማዘጋጀትና በማፀደቅ ስራ ላይ ማዋል ግንዛቤን በማስፋት፣<br>◆ ለሚነሱ የአባላትና የታራሚዎች ቅሬታዎችና አቤቱታዎች በአጭር ጊዜ ውሳኔ በመስጠት፣<br>◆ ከለሎች የፍትህ ተቋማት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ፈጥሮ መስራት<br>◆ የፈፃሚውን የአገልጋይነት ስሜትና ስነ-ምግባር እንዲሻሻል በማድረግ፣<br>◆ ከፌዴራል ና ክልል ማ/ቤቶች የጋራ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ተከታታይነት ያለው መድረክ በመፍጠር መሥራት፡<br>◆ ከዩኒቨርሲቲዎችና ከሌሎች አካላት የተጀመሩ የቅንጅት ስራዎችን አጠናክሮ በመቀጠል፣ |
| 4 | ◆ የማስፈፀም አቅም መሻሻል ማሳየቱ፣ | ◆ የተቋሙን ራዕይና ተልእኮ የሚያሳኩ ተከታታይነት ያላቸው የአጭርና የረዥም ጊዜስልጠናዎችን በመስጠት፣<br>◆ ተቋሙን በሰልጠነና ብቃት ባለው የሰው ሃይል በማሟላት፣<br>◆ በየደረጃው ያለው አመራር የማስፈፀም አቅሙን በተለያዩ የዓቅም ግንባታ ተግባራት በማጎልበት፣<br>◆ የሰራተኛው አፈጻፀም ውጤታማነት በመለካትና የማትጊያ ስርዓት በመዘርጋት፣<br>◆ አመራርና ሰራተኛውን አተካክቶና አሂዙሮ በመስራት ፣ |
| 4 | ◆ በጀትና ዕቅድን ያስተሳሰረ የኘሮግራም ዝግጅትስርዓት ሥርዓት መዘርጋቱ፤ | ◆ ዕቅድን መሰረት ያደረገ ውጤትን ከበጀት ጋር እንዲተሳሰር በማድረግ አፈፃፀምን በውጤት በመለካት፣<br>◆ የተቋሙን የውስጥ ገቢ በማሳደግ ለተቋሙ ጥቅም እንዲውል በማድረግ<br>◆ በዕቅድ የተመራ የፋይናንስ አጠቃቀም በማስፈን፣ |

### 1.6.2. ፈታኝ ሁኔታዎች፡-

| ተ.ቁ | ፈታኝ ሁኔታዎች፣ | የመፍትሄ እርምጃ ፣ |
|---|---|---|
| 1 | ◆ ከስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ይልቅ በደራሽ ጉዳዮች ላይ ማተኮር | ◆ ሥራን በዕቀድ በመምራት፣ በደራሽ ጉዳዮች ላይ ከማተኮር ለስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ትኩረት ሰጥቶ በመስራት፣ |
| 2 | ◆ የክትትል ድጋፍና ግምገማ አሠራር በጥራትና በውጤት ላይ ያተኮረ አለመሆንና ሥራን መሠረት ያደረገ የግምገማ ባህል ያለማዳበር፣ | ◆ አፈፃፀምን ከውጤትና ከጥራት አንፃር በመገምገም፣<br>◆ የግምገማ ውጤትን መሠረት በማድረግ ቀጣይ የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ፣<br>◆ መልካም ተሞክሮዎችና ልምዶችን በመቀመርና በማስፋት፣<br>◆ ግምገማው ወቅቱን የጠበቀ እና በመርህ የተመሠረተ እንዲሆን በማድረግ፣ |
| 3 | ◆ የተቋሙን ቀጣይ አቅጣጫ የሚያመላክት የተደራጀ የሰው ኃይል ልማት አለመኖር፣<br>◆ በአባላት ላይ ከፍተኛ የስራ ጫና መኖር | ◆ የተቋሙ የሰው ኃይል ልማት መሪ ዕቅድ በማዘጋጀት፣ የማረሚያ ፖሊስ ስታንዳርድ ማዘጋጀት፣<br>◆ ባለሙያን ለማቆየት የሚያስችል ምቹ ሁኔታ በመፍጠር፣<br>◆ ዕውቀትና ክህሎትን መሠረት ያደረገ የሰው ኃይል ምደባ በማደረግ፣ |
| 4 | ◆ የተቋሙ ተልዕኮ ለማሳካት የተመደበው የፖሊስ ሃይልና የዕውቀትና የክህሎት እና የአቅም ውስንነት ያለበት መሆኑ ፣ | ◆ የዓቅም መገንቢያ ተቋሙን ማደራጀት፣አጫጭር፣መካከለኛና የረጂም ጊዜ ስልጠናዎች በመስጠት፣<br>◆ የመሥሪያ ቤቱን ራዕይና ተልእኮ ሊያሳኩ የሚችሉ ባለሙያዎችን በጥራትና በብዛት ማዘጋጀት ፣ |
| 5 | ◆ የአባላት የስነ- ምግባር ክፍተት መኖር | ◆ ለስነ- ምግባር መስፋፋት መንስኤ የሆኑ ችግሮችን በጥናት መለየት ችግሩን መፍታት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት<br>◆ የስነ- ምግባር ግንባታ ስልጠና መስጠት<br>◆ የአባላት አያያዝ ስርዓት ማሻሻል<br>◆ ልዩልዩ ማትጊያ ግብዓቶችና ጥቅማ ጥቅሞች እንዲከበሩ በማድረግ፣ |
| 6 | ◆ የተቋሙ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደራጀ አለመሆን ፣ | ◆ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት በመዘርጋት ጥቅም ላይ በማዋል፣<br>◆ በሁሉም ስራ ክፍሎች ባለሙያዎችን በማሟላትና ዓቅም በመገንባት፣ |
| 7 | ◆ የአገልግሎት አሰጣጥ መሻሻል የሚፈለገው ደረጃ ላይ አለመድረስ ፣ | ◆ የአገልግሎት አሰጣት ስታንዳርድ በማዘጋጀት በስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎት በመስጠት፣<br>◆ አገልግሎት አሰጣጡን በቴክኖሎጂ እንዲታገዝ በማድረግ፣<br>◆ የፈፃሚው የአገልጋይነትና የባለቤትነት ስሜት በማጎልበት፣<br>◆ ቅሬታዎችን ተቀብሎ በመመርመር የመፍትሔ እርምጃዎችን በመውሰድ፣ |
| 8 | ◆ ያለው ቅንጅታዊ አሰራር የሚፈለገውን ውጤት ማስገኜትበሚያስችል ደረጃ አለ መሆን | ◆ ለቅንጅታዊ አሰራር መጠናከር ክፍተት የሆኑ ጉዳዮችን ለይቶ በመፍታት አሰራሩን ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲመራ ማስቻል |
| 9 | ◆ የግዥ ስርኣቱ በዕቅድና በፕሮግራም ያለመምራት | ◆ የግዥ ስርዓቱ በዕቅድና በፕሮግራም እንድመራ የግዥ ስርዓት ቁጥጥር ስርዓት ማጠናከር<br>◆ የመንግስት የግዥ ስርኣትን እና ተጠያቂነትን በማጠናከር በተጠያቂዎች ላይ ህጋዊ እርምጃ መውሰድ ፣ |

# 2. ክፍል-ሁለት

## 2.1. የኮሚሽኑ ራዕይ ፣ ተልዕኮ ፣ እሴት እና ስልጣንና ተግባር

### 2.1.1. የኮሚሽኑ ራዕይ፡-

2017 ዓ.ም የህግ የበላይነት እና የታራሚዎች ሰብአዊ መብት የተከበረበት ፣ የታረመና የታነፀ ፣ አምራችና ህግ አክባሪ ዜጋ የሚፈራበት ሞድል ተቋም መሆን፡፡

### 2.1.2. ተልዕኮ፡-

በፍርድ ቤት ትዕዛዝና ዉሳኔ ወደ ማረፊያና ማረሚያ ቤት የሚላኩ የቀጠሮ እስረኞችና ታራሚዎችን በመቀበል የተጠናከረ የጥበቃ ደህንነት እና የሰብዓዊ አያያዝና አስተዳደር፣ የመሠረታዊ ፍላጐት አቅርቦት፣ የማረም ማነፅ ተሃድሶ ልማት አገልግሎት በመስጠት ታራሚዎች በአግባቡ ታርሞና ታንፆ አምራችና ህግ አክባሪ ዜጋ ሆኖ እንዲወ ማድረግ

### 2.1.3. እሴቶች፡-

- የሕግ የበላይነት ማክበር ማስከበር ፣
- ሰብአዊ መብት ማክበር ማስከበር፣
- ፍትሃዊነት፣
- ግልጽነትና ተጠያቂነት፣
- አሳታፊነት
- ኪራይ ሰብሳቢነትንና ሙስናን መጠየፍ፣
- በታማኝነትና በቅንነት ማገልገል፣
- ማረም ማነጽ ተኮር አገልግሎት
- ለለውጥ ዝግጁነት ፣
- አርአያነት፣

## 2.2. የኮሚሽኑ ስልጣንና ተግባር

1. በክልል ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙትን ማረሚያ ቤቶች በበላይነት ይመራል ፣ያስተዳድራል፣ ስራቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ አፈጻጸማቸውን ይገመግማል
2. በየደረጃው ያሉትን የማረሚያ ቤቶች ሠራተኛ ምልመላ፣ቅጥር፣ ምደባ፣ የደረጃ ዕድገት ዱስፒልንና ዝውውርን በተመልከተ የሚቀርቡትን የውሳኔ ሃሳቦች ተቀብሉ ያፀድቃል
3. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ታራሚዎችን በቀልም ትምህርት፣በሙያ ስሌጠና እና የማህበራዊና የካውንስልንግ አገልግሎት በመስጠት ታራሚዎች ሰላማዊና አምራች ዜጋ እንዱሆኑ ያደርጋሌ፡፡ ለዚሁም የሚያስፍልጉትን የስሌጠና ማዕከላት ያቋቁማል ፣ ያደራጃል፤ ያስተዳድራል፤
4. በፋዴራልም ሆነ በክልሉ ፍርድ ቤቶች በሚሰጥ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ኮሚሽኑ ወደ ሚያስተዳድራቸው ማረሚያ ቤቶች የሚላኩ ታራሚዎች በሰብአዊ አኳኋን መያዛቸውን፣ መጠበቃቸውንና፣ መታረማ ቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
5. ፍርድኛ ታራሚዎችንና በጥበቃ ሥር የሚገኙ ሰዎች ከተላላፊ በሽታዎች መጠበቃቸውንና በእርማትም ሆነ በጥበቃ ላይ እያሉ ሲታመሙ ነፃ ህክምና፣ ምግብና መጠለያ እንዱያገኙ ያድርጋል
6. ዝርዝሩ በድንብ የሚወሰን ሆኖ ማናቸውም ታራሚ በማረሚያ ቤት ቆይታው በሚፈጽመው ጥፋት አስተዳደራዊ እርምጃዎች በየደረጃው እንዱወሰደ ያደርጋል የቅጣት ውሳኔዎችን ያፀዴቃል፣ያሻሽላል ይሽራል፤
7. ዝርዝሩ በድንብ የሚወሰን ሆኖ ታራሚዎች በእርማት ወቅት በሚያሳዩት አወንታዊ የባህሪይ ልውጥ ሳቢያ በህጉ መሠረት በአመክሮ የመልቀቅ ጥያቄ ለማረሚያ ቤቱ ሲያቀርቡ ይከታተላ፣ይቆጣጠራል የቅሬታም ሆነ የእስራት ቅናሽ ውሳኔዎችን ይፍፅማል፤
8. የክልሉን ማረሚያ ቤቶች በሚመልከት ከልሎች ክልሉችና ከፌዳራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ጋር የስራ ግንኙነቶችን ያድርጋሌ፤
9. የንብረት ባልቤት ይሆናል ፣ ውል ይዋዋላል፣ ይከሳል ይከሰሳል፤
10. ልሎች ከስራ ባህሪው ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 2.3. የክልል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን የስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮችና ዋና ዋና ግቦች

### 2.3.1. ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች

የኮሚሽኑ ጥንካሬና መልካም አጋጣሚዎች እንዲሁም ስትራቴጂውን በመተግበር ሂደት ሊኖሩ የሚችሉ ጉድለቶችንና ስጋቶችን በመተንተን፣ የተገልጋዮችን ፍላጐት መነሻ በማድረግ ሁሉንም ፈጻሚ አካላት በውጤት ዙሪያ ሊያሰባስቡ የሚችሉና ራዕዩን ወደ ተጨባጭ ተግባራት ሊቀይሩ የሚያስችሉ ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች በአራት ነጥቦች ተለይተዋል፡፡ የተመረጡት ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች፡-

2.3.1.1. ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮችና ውጤቶች

| ተ/ቁ | ስትራቴጂያዎ የትኩረት መስኮች | ስትራቴጂያዎ የትኩረት መስክ ዉጤት |
|---|---|---|
| 1 | ◆ የተጠናከረ የጥበቃና ደህንነት ፍትህ አስተዳደር | ◆ ደህንነቱ የተጠበቀና የህግ የበላይነት ያረጋገጠ ታራሚ |
| 2 | ◆ የላቀ የተሃድሶና ልማት አገልግሎት | ◆ የታረመ፣ የታነፀ፣ በክህሎት ፣ በአሰተሳሰብ እና በአመለካከት ለወጥ ያመጣ ታረሚ |
| 3 | ◆ የላቀ የመሠረታዊ ፍላጐት አቅርቦት አገልግሎት | ◆ መሠረታዊ ፍላጐቱ የተሟላለት የህግ ታራሚ |
| 4 | ◆ የተደራጅ ተቋማዊ ግንባታ | ◆ የተጠናከር አደረጃጀትና የመፈፀም ብቃት ያለው የሰው ኃይል |

2.3.1.2. ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች መግለጫ

| ተ.ቁ | ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስክ | ስትራቴጂያዊ ውጤት | ወሰን /ይዘት/ |
|---|---|---|---|
| 1 | የላቀ የመሠረታዊ ፍላጐት አቅርቦት አገልግሎት | መሠረታዊ ፍላጐቱ የተሟላለት የህግ ታራሚ | ◆ ፍርደኛ ታራሚና የቀጠሮ ታሳርዎች የመጠለያ የምግብ ፣የወሃና የመጠለያ የመኝታ የአልባሳት አቅርቦት በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት መስጠቱን፤<br>◆ በማረሚያ ቤት የግል፣ የጋራና የአካባቢን ጤና በመጠበቅ ሊከሰቱ የሚችሉ ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን መከላከል የሚያስችል የተሸታ መከላከል ት/ትና የፈውስ ህክምና አገልግሎት |
| 2 | የተጠናከረ የጥበቃና ደህንነት ፍትህ አስተዳደር | ደህንነቱ የተጠበቀና የህግ የበላይነት ያረጋገጠ ታራሚ | ◆ ታረሚዎች ከውስጥና ከውጭ ባላጋራዎቻቸው ጥቃት እንዳይደርስባቸው አስተማማኝ ጥበቃ በማድረግ ደህንነታቸውንመጠበቅ<br>◆ ፍርደኞችንና የቀጠሮ እስረኞችን በመቀበል በወንጀል አይነት፣ በእድሜ፣ በፆታ መደልደልና ታራሚዎችን በፍርድ ልክ መለየትን፣<br>◆ እንደየፍርድ ደረጃቸው ስምሪቱንና እጀባውን ማከናወንን፣<br>◆ ታራሚ ደህንነትና ሰብአዊ መብቱን አክብሮ ጥበቃውን ማጠናከርን፣<br>◆ የታራሚ መረጃ አጠናቅሮ በፍርድ ቤት ትእዛዝ፣ በይቅርታ፣በአመክሮና እስራታቸውን ጨርሰው የሚፈቱ ታራሚዎች በወቅቱ እንዲፈቱ ማድረግን ያካትታል። |
| 3 | የላቀ የተሃድሶና ልማት አገልግሎት | የታረመ፣ የታነፀ፣ በክህሎት ፣ በአሰተሳሰብ እና በአመለካከት ለዉጥ ያመጣ ታረሚ | ◆ ለቀጠሮ እስረኞች /ለታራሚዎች የማህበራዊ፣ የምክክር ፣የስፖርትና መዝናኛ አገልግሎትን መስጠትን፣<br>◆ የታራሚዎች የት/ት እና የስልጠና ተሳታፍነታ በዘላቂ በማሻሻል የክህሎት እና የእውቅት ባለቤትነትን ማረጋገጥን<br>◆ ለታራሚዎች የንቃተ ህግና የሥነ ምግባር ትምህርት፣ የቀለም ትምህርት፣ የቴክኒክ ሙያ ስልጠና በመስጠት የታራሚዎችን እውቀትና ክህሎት በማሳደግ የሙያ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግን፣ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | ◆ ታራሚዎችን በማደራጀት፣በልማት ሥራዎች በማሳተፍና ገቢ እንዲያገኙ በማድረግ የእርምት ሥራውን በማሳለጥ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግን ያጠቃልላል፡፡ |
| 4 | የተደራጅ ተቋማዊ ግንባታ | የተጠናከር አሰራርና አደረጃጀት ስርዓትና የመፈፀም ብቃት ያለው የሰው ኃይል | ◆ የተቋሙ‑ንየሰውኃይልመጠን ማሳደግ የመፈፀምና የማስፈፀምአቅም ብቃትማሻሻል<br>◆ አዳዲስ የማ/ቤት ግንባታና ነባር የታራሚ ማደሪያ ቤት ደረጃውን በጠበቅ እንዲገነቡ እና ለአገልግሎት መዋላቸውን የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓትን በማሻሻል የተገልጋዩን ተጠቃምነትን ማረጋገጥን<br>◆ የአዋጅ ፣ደንቦች ፣መመሪያዎችና የአሰራር ማኑዋሎችን ማሻሻልን<br>◆ መዋቅራዊ አሰራርና አደረጃጀትን ለማሻሻል የድጋፍ ክትትል ስርዓትን ማጠናከርን<br>◆ የአግልግሎት መስጫ ማዕከላት አደረጃጀትን በማሻሻል<br>◆ የታራሚ መኖሪያ ቤቶችና የአስተዳደር ቢሮዎች ማስፋፊያ ግንባታ፣የሴንቴሪ ጥገናና እድሳት በተያዘለት ደረጃ መሠረት ማከናወንን ያካትታል፡፡ |

## 2.4. ስትራቴጂያዊ ግቦች

### 2.4.1. ለሁሉም ተቋማዊ ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች የተጠቃለሉ ግቦች በእያንዳንዱ እይታ እንደሚከተለው ተካተዋል

| ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች | | | |
|---|---|---|---|
| 1.የጥበቃና ደህንነት ፍትህ አስተዳደር | 2. የተሃድሶ ልማት ማረም ማነፅ አገልግሎት | 3. የመሠረታዊ ፍላጐት አቅርቦት አገልግሎት | 4.ተቋማዊ ግንባታ |
| **የተቋሙን ሰላም፣ ደህንነት እና የህግ በላይነትን ማረጋገጥ**<br>◆ የቋም ጥበቃ የእጀባ ፣ የመረጃ ክትትልና የታራሚዎች እንቅስቃሰ ክትትል<br>◆ የታራሚ የእርስ በርስ ግንኙነት የበተሰብ ግንኑነት ጤናማነትን ማረጋገጥ<br>◆ የታራሚዎችን ሰብአዊ መብት አያያዝ ማሻሻል፣<br>◆ ወደ ማረ/ቤቶች እንዳይገቡና እንዳይወጡ የተከለከሉ ነገሮች ቁጥጥርና ክትትል ማሳደግ<br>◆ የታራሚዎች የቀጠሮ አቀራረብ እና የፍርድ አፈፃፀም ክትትል | **የህግ ታራሚዎችን የማረምና የማነጽ አገልገሎት አሰጣጥን ማሳደግ ፣**<br>◆ የትምህርትና ስልጠና አገልግሎቶችን በስታንድርድ መሠረት በጥራት መስጠትን ማሳደግ፣<br>◆ የንቃተ ህግ የግንዛቤ ማሻሻያ ት/ት ፤የምክር አገልግሎት አሰጣት ጥራት ተደራሽነትን ማጠናከር<br>◆ የግብርና ልማት ስራ ስምርት<br>◆ የገቢ ማስገኛ ስራ ዕድል አገልግሎቶችን<br>◆ የታራሚዎችን በግብርናና በሙያ ልማት ስራዎች በግልም ሆነ በማህበራት በመደራጀት የመስራት ደረጃን ማሳደግ።<br>◆ የታረሚዎች የባህሪ ለውጥ ግምገማና ምዘና በማድረግ ያለውን ለውጥ | **የመሰረታዊ ፍላጎቶች አቅርቦትና አገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል ፣**<br>◆ የህግ ታራሚዎች ምግብ፣ የዉሃና የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ማሻሻል<br>◆ የአቅርቦት ተደራሽነት መጠን ጥራት ተደራሽነትን ማሻሻል<br>◆ የታራሚዎች የህክምና አገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ<br>◆ የታራሚዎችን የቅድሜ በሽታ መከላከል ት/ት በመሰጠት የግቢ ምቾት በማሻሻል የበሽታ ተገላጭነትን መቀነሰ<br>◆ የስፖርት መዝናኛ ክበባትአደረጃጀቶችን መፍጠር | **የተቋሙን መሰረተ ልማት ማሳደግ፣**<br>◆ የአገልግሎት መሰጫ ማዕከላት ተደራሽነትን ማሻሻል፣<br>◆ የታራሚዎች ነባርና አዳዲስ መኖሪያ ቤቶች፣ ፤የአስተዳደር ቢሮዎች እና የተለያዩ አገልግሎት መስጫ ተቋማትግንባታና፣ጥገናና እድሳት ስራዎችአፈፃፀም ማሳደግ<br>◆ የነባርና አዳዲስ ተቋማት የውስጥ ፋሲሊቲዎችን በስታንዳርድ መሠረት ማሟላት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ማጠናከር፣<br>◆ የታራሚዎች የፍትህ አስተዳዳር አግልግሎት በስታንድርድ መሰረት በጥራት ተፈፃሚ ማድረግ ፣<br>◆ የታራሚዎች የይግባኝ፤ አመክሮና ይቅርታ አሰጣጥ ጥራትና ግልጽኝነትን ማሻሻል፣<br>◆ የማህበራዊ አገልግሎት ተደራሽነትን/የእርቅ የዝውውር የማህበበራዊ ጉዳይ ማስፈፀ ስርዓትን ማሻሻል<br>◆ ታራሚዎች ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳደሩበት ስርዓትን ማጠናከር | መለካት፣<br>◆ የታራሚዎች የገቢና የቁጠባ ባህል አቅም ማሳደግ<br>◆ በማረሚያ ቤትም ሆነ ከፍቺ በኋላ ማህበራዊ መሰረቶቻቸውን የሚያጠናክሩ የስነ-ልቦና አቅም ማሳደግ | ◆ የታራሚዎች የቤተሰብ ግንኙነት ፣ከጠበቆቻቸው እና የሀይማኖት አባቶቻቸው የሚያገኙትን አገልግሎት አሰጣጥ ሰርዓትን ማሻሻል | ◆ የተፈጥሮ ሃብትን የማይጐዱ አማራጭ የሀይል ምንጮች ስራ ላይ ማዋልን፣<br>◆ የተቋማዊ የስው ኃይል ብቃት በአቅም ግንባታ ስራ ማጠንክርና፡፡የሰው ኃይል የማሟላት<br>◆ የትምህርትና የሙያ ስልጠና መስጫ ማዕከላትን ደረጃ ማሳደግና አዳዲስ ማዕከላትን ማቋቋም፣<br>◆ ICT ቴክኖሎጅን ማበልፀግ<br>◆ የለውጥ መሳሪያዎች ትግበራን ተፍፃሚ ማድረግ |

## 2.4.2. ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች ለማሳካት የተጣሉ ግቦች


- **የአቅርቦት ተደራሽነትን በማሻሻል የተገለጋይ እረካታ ማሳደግ**
  - ✓ የምግብ አቅረቦትና ጥራት ተደራሽነትን ማረጋገጥ
  - ✓ የበሽታ መከላከለ እና የፍውሰ ህክምና አገልግሎት ተደራሽ ማድረግ
  - ✓ የአልባሳትና የመኝታ አቅርቦትና ተደራሽነትን ማስፋት
- **አሰራር ስርዓትን ማሻሻል**
  - ✓ የተቋም አዋጅ፣ድንብ ፣መመሪያና የአሰራር ማንዋሎችን ማሻሻል
  - ✓ ስትራቴጅ ዝግጅት ፣ተግበራ፣ክትትልና ድጋፍ ተፈፃሚነትን ማሻሻል
  - ✓ የጥናትና የምርምር ተግበራ ማካሄድ
  - ✓ የአገልግሎት አሰጣጥ ዝግጅት እና ተግበራ ማካሄድ
- **የመሠረት ልማት አቅረቦት ተደራሽነትን ማሳደግ**
  - ✓ የነባር አገልግሎት መሰጫ ማዕከላት ማስፋፊያ ማካሄድ (የታራሚ ማደሪያ ቤት፣የህክምና ማዕከላት፣የውሃ አቅርቦት ፣የት/ት ቤት ማስፋፊያና ደረጃ ማሻሻያ ወዘተ)
  - ✓ የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጅ ዝርጋታ ስራ ተግባራዊ ማድረግ
  - ✓ አዳዲስ የሙያ ስልጠና ማዕከላት ማድራጀት
  - ✓ ቅርንጫፍ የማረሚያ ቤት ማዕከላት አደረጃጀት መፍጠር
  - ✓ የአገልግሎት መሰጫ ማዕከላት እደሳት እና ጥገና ማካሄድ
- **የተገባቦትና የገፅታ ግንባታ ማሳደግ**
- **የተሃደሶ ልማት ማረም ማነፅ ውጤታማነትን ማሳድግ**
  - ✓ የምክር እና የሰነ ልቦና ድጋፍ አገልግሎት ተደራሽ ማድረግ
  - ✓ የንቃት ህግ እና የሰነ ምግባር ማሻሻያ ትምህርት ተደራሽነትን ማሰፋት
  - ✓ የቀለም ትምህርት እና የሙያ ሰልጠና ጥራት ተደራሽ ማድረግ
  - ✓ የታራሚዎችን የሰራ ዕድል ፍጠራ ክህሎት ማሳድግ
  - ✓ የግብርና ልማት ስራ በማሰፍት የታራሚ ተጠቃሚነት እና ምርታማነትን ማሳደግ
- **የተቋም ስላም እና ደህንነት አሰተማመኝነት ማረጋገጥ**
  - ✓ የቋሚና ተንቀሳቃሽ ጥበቃ ስራን ውጤታማ ማድርግ
  - ✓ የመረጃ ክትትል ሰርዓትን ማጠናከር
  - ✓ የፍተሸ ቁጥጥር አሰራር በማጠናከር የአደጋ ተገላጭነትን መቀነሰ
  - ✓ የጥበቃ ደህንነት ሎጀሰቲክ አቅርቦት ማሟላት
- **የአገልግሎት ተደራሽነትን ማሳድግ**
  - ✓ የፍትህ አገልግሎት ተደራሽ ማድረግ (የቀጠሮ፣ይገባኝ፣አመክሮና ይቅረታ)
  - ✓ የማህበራዊ አገልግሎት አሰጣጥ ሰርዓትን ማሻሻል (እረቅ፣ዝውውር፣ዘመድ ግንኙንትና ጉዳይ ማሰፈፀም)
  - ✓ የቅሬታ ማሰተናገዥ አሰራር መዘርጋት
  - ✓ የለውጥ ተግበራ ሰርዓቶችን ተፈፃሚ ማድረግ

| | | |
|---|---|---|
| | ✓ የባለደርሻ እና የአጋር አካላትን ተብብርና እገዛን ማጠናከር<br>✓ የመረጃ ሰርጨት ግለፀኝነትንና ተደራሽነትን ማስፈን<br>✓ የስፖርትና የመዝናኛ አገልግሎት ተደራሽነትን ማስፋት<br>✓ የተገለጋይ ማህበርሰብ የጋራ ምክክር ሰርዓት ማጠናከር<br>✓ የተቋም እሴት ግንባታ ማሳደግ (የመሰክ ጉብኝት፣የባለድረሻ አካላት ወይይት፣የአፈፃፀም ግምገማ ወዘተ)<br>◆ **የስው ሀብት ልማት ማሳደግ**<br>✓ የስው ሀይል ቀጠር (አዲሰ ስው ሀይል ቀጠርና ሰልጠና)<br>✓ የአቅም ግንባታ ስልጠና (የአጫጭር፣የመካከለኛና የረጀም ዚጌ)<br>✓ የሠራተኛ ሰነ ምግባር ግንባታ ማሳደግ<br>✓ የማቲጊያ ሰርዓት ማሻሻል<br>◆ **የቴክኖሎጂ አቅም በማሳድግ የመረጃ አሰተዳደር ሰርዓትን ማሻሻል**<br>✓ የዳታ ቤዝ መረጃ ትሰሰር ሰርዓት መዘርጋት<br>✓ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት ክህሎት ማሳደግ | ◆ **የዘርፍ ብዙ ጉዳዩችን አካቶ መሰራትን ማሳደግ**<br>✓ ልዩ ድጋፍ እና እገዛ ለሚሹ ተገለጋይ ማህበርሰብ ተቋማዊ አጋረነትን ማጠናከር (ሴት የህግ ታራሚዎች፣ህፃናት፣ የአእምሮ ሁሙማን፣ወጣት ጥፋተኞች፣የአካል ጉዳተኞች፣የHIV ሁሙማን እና አዛውንቶች )<br>✓ የሴቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማሳደግ<br>✓ የአካባቢና የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ አፈፃፀም ማጠናከር<br>◆ **የሀብት አሰተዳደር ስርዓትን ማሻሻል**<br>✓ የበጀት አጠቃቀም ሰርዓትን ማሻሻል<br>✓ የገቢ አሰባሰብ ሰርዓትን በማጠናከር የውሰጥ ገቢን ማሳደግ<br>✓ የኦዲት እና የእንሰፐክሽን ሰርዓት መዘርጋት<br>✓ የንብርት አሰተዳደር ሰርዓት መዘርጋት |

## 2.5. የተጠቃለሉ የስትራቴጂካዊ ግቦች

| እይታ | ስታራቴጂያዊ ግብ |
|---|---|
| ተገላጋይ | 1. የአቅርቦት ተደራሽነትን በማሻሻል የተገለጋይ እረካታ ማሳደግ<br>2. የአገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ |
| ፋይናነስ | 3. የሀብት አስተዳደር ሰርዓትን ማሻሻል |
| የውስጥ አሰራር | 4. አሰራር ሰርዓትን ማሻሻል<br>5. የተቋም ሰላም እና ደህንነት አስተማማኝነትን ማረጋገጥ<br>6. የተሃደሶ ልማት ማረም ማነፅ ውጤታማነትን ማሳደግ<br>7. የምርታማነትና የታራሚ ተጠቃሚነትን ዕድጌት ማሻሻል<br>8. የአገልግሎትመሰጫ ማዕከላት አደረጃጀትንማስፋት<br>9. የዘርፍ ብዙ ጉዳዩችን አካቶ መሰራትን ማሳደግ |
| መማማርና ዕደግት | 10.የተገባቦትና የገፅታ ግንባታ ማሳደግ<br>11.የሰው ሀብት ልማት ማሳደግ<br>12.የቴክኖሎጂ አቅም በማሳደግ የመረጃ አስተዳደር ሰርዓትን ማሻሻል |

## 2.5.1. የተጠቃለል የስትራቴጀክ ግቦች ማፕ



## 2.5.2. የግቦች መግለጫ

| እይታ | ግቦች | የግቦች ወሰን | የግቦች መለኪያ |
|---|---|---|---|
| ተገልጋይ | ◆ የአቅርቦት ተደራሽነትን በማሻሻል የተገልጋይ እርካታን ማሳደግ | ◆ ተቋሙ ባስቀመጠው የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድና ዜጎች ቻርተር ስምምነት መሰረት ለተገልጋዩች አገልግሎት በመስጠት እርካታን እንዲያድግ ማድረግ፣<br>◆ ተገልጋዩች የሚያነሷቸውን የምግብ አቅርቦትና ጥራት ችግር ፣ የውሃ እጥረት በአገባቡ በማጠን አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት የታራሚዎችን ችግሮችን መፍታት<br>◆ የበሽታ መከላከል እና የፍውሰ ህክምና አገልግሎት ተደራሽ በማድረግ ለታራሚዎች የመኝታ አቅረቦት በማምቻቸት የእረካታ መጠን ማሳደግ<br>◆ ተገልጋዮች ስለመርካታቸው እርካታ የሚለካበትን የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የእርካታ ዳሰሳ ጥናቶች በማካሄድ የእርካታ ደረጃን መለካት ፣ | ◆ ያደገ የተገልጋዮች እርካታ |
| | ◆ የአገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ | ◆ የጊዜ ቀጠሮ፣ይግባኝ፣አመክሮ፣ይቅረታ እና እጀባ ለሚያስፈልጋቸው ታራሚዎች አገልግሎት መስጠት<br>◆ የታራሚዎች የፍቺ ትዕዛዞችን ተቀብሎ ማስተናገድ፣<br>◆ የታራሚዎች የማህበራዊ አገልግሎት ጥያቄዎች እረቅ፣ዝውውርና ጉዳይ ማስፈፀም የመሳሰሉትን ነገሮችን ማስተናገድ<br>◆ የቅረታ ማስተናገዣ አሰራር በመዘረጋት ታራሚው የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ማድረግ | ◆ ያደገ የአገልግሎት ተደራሽነት |
| ፋይናንስ | ◆ የሀብት አስተዳደር ስርዓትን ማሻሻል | ◆ የተመደበውን በጀት በአግባቡ በእቅድ መሰረት ስራ ላይ ማዋል፣<br>◆ ደንብና መመሪያን የጠበቀ የፋይናንስ አሰራር እንዲኖር ማድረግ፡<br>◆ በዕቅድ የሚመራ የግዥ አሰራር በመዘርጋት ጥራቱንና ጊዜውን የጠበቀ ግዥ መፈፀም፣<br>◆ የንብረት ፍታሃዊ ስርጭት፣ አጠቃቀም ፣ አስተዳደር እንዲኖር እና ብክነት እንዲቀንስ ማድረግን፣ | ◆ ዉጤታማ የበጀት አጠቃቀም<br>◆ ፍትሃዊ የንብረት ስርጭት<br>◆ ያደገ የሀብት መጠን<br>◆ ጥራቱን የጠበቀ ግዥ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ◆ የወሰጥ ገቢ አቅም ለማሳደግ የሀብት ምንጮችን ማስፋትን፣<br>◆ ከግብርና፣ ከኢንዱስትሪና በስልጠና ሂደት ከሚመረቱ ምርቶች ሽያጭ የሚገኘውን ገቢ ማሳደግና ውጤታማ ማድረግን ያካትታል፣ | ◆ የቀነሰ የሃብት ብክነት ያደገ የውስጥ ገቢ |
| **የውሰጥ አሰራር** | **የዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን አካቶ መስራትን ማሳደግ** | ◆ ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ተገልጋዮች ታሳቢ በማድረግ አካታችነትን አሟልቶ ማቀድና መተግበር፣<br>◆ በተቋሙ ሴት ሰራተኞችና ታራሚዎች፣ አካል ጉዳተኞች፣የወጣቶች ጥፋተኞች እና የሕፃናት መብቶችና ነፃነቶች በማክበር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግን፤<br>◆ የተቋሙ ሴት ሰራተኞችን የትምህርት ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ<br>◆ ከወላጆቻቸውጋር በማረሚያ ቤት ለሚገኙ ህጻናትና አጸደ-ህጻናትና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታ መፈጠር<br>◆ ከኤችአይቪ ቫይረስ ጋር የሚኖሩ አባላት፣ሰራተኞችና ታራሚዎች በሕጉ የተረጋገጡላቸውን መብቶችተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ፣<br>◆ ለአእምሮ ህሙማንና ለአረጋውያን እንዲሁም ወላጅ አልባና ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የአባላት ልጆችን፣የማህበርሰብ ክፍሎችንመደገፍን<br>◆ ነባር ችግኖችን በመከባከብ እና አዳዲስ የተለያዩ አገር በቀልና ሌሎችንም የችግኝ አይነቶችን እንዲተከሉ በማድረግ ለአከባቢ ጥበቃ እንክብካቤ አስተዋፆ ማደረግን | ◆ ያደገ የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች አካታችነትና ትግበራ፣<br>◆ የተከበሩ የሴቶች፣የአካል ጉዳተኞች፣የወጣቶችና የሕፃናት መብቶችና ነፃነቶች፤<br>◆ ያደገ የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ |
| | **አሰራር ስርዓትን ማሻሻል** | ◆ የተቋም አዋጅ፣ድንብ መመሪያና የአሰራር ማንዋሎችን ማሻሻያ በማድረግ ለተገልጋዩ ማህበረሰብ ገልፅ ማደረግን<br>◆ በእቅድ ዝግጅትና ተግበራ የክትትልና የሙያዊ ድጋፍ ስራዎችን በማካሄድ ተፈፃሚነቱን መረጋገጥን<br>◆ ተቋማዊ ችግሮችን የሚፈቱ የጥናትና የምርምር ስራዎችን ተግባራዊ ማድረግን | ◆ የተሸሻል አሰራር መመሪያ<br>◆ ያደገ የክትትልና የድጋፍ ስራ<br>◆ ያደገ ጥናትና ምርምር |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | **የአገልግሎት መሰቻ ማዕከላት አደረጃጀት ማስፋት** | ◆ የታራሚ ማደሪያ ቤት፣የህክምና መስጫ መአከላት፣ የውሃ አቅረቦት እና ት/ት ቤት ማስፋፊያ ግንባታ በማካሄድ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥን<br>◆ የታራሚዎን የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ማዕከላት በማደራጀት የእውቅት ክህሎት ተጠቃሚ ማድረግን<br>◆ አዲስ የማ/ቤት ቅረንጫፍ ማዕከላት አደረጃጀት በመፈጠር የተጨናነቀውን የማ/ቤት ቦታ ጥበትን ማስተነፍስ<br>◆ ለታራሚ አገልግሎት መሰጪያነት የሚዉሉ ማዕከላት እና ለጥበቃ ደህንነት የሚያገለግሉ የጥበቃ ሴንቴሪዎችን እደሳትና ጥገና ስራ ማካሄደን<br>◆ ክልል አቀፍ የልማት ማዕከል በማደረጃትየማ/ቤት የገቢ አቅም ማሳደግ | ◆ የተሸሻል የአገልግሎት መሰጫ ማዕከል<br>◆ የተደራጅ የሙያ ማዕከል |
| | **የተሃደሶ ልማት ማረም ማነፅ ውጤታማነትን ማሳደግ** | ◆ የምክር እና የሰነ-ልቦና ድጋፍ አገልግሎትን ተደራሽ ማድረግን<br>◆ የህግ ታራሚዎችን የንቃት ህግ ት/ት እና የሰነ-ምግባር ማሻሻያ ት/ት ተደራሽነትን ማስፋትን<br>◆ ታራሚዎች መደበኛ እና የጎልማሶች ተግባር ተኮር ት/ት ተጠቃሚ ማድረግን<br>◆ የሙያ ሰልጠና ጥራት ተደራሽነትን<br>◆ ለታራሚዎች የስራ ዕድል ክህሎት ማሳደግን<br>◆ በግብርና ልማት ስራ በማስፋት የታራሚ ተጠቃሚነትን ማሳደግን | ◆ ያደገ የምክርና ሰነ-ልቦና ድጋፍ<br>◆ ያደገ የቀለመና ሙያ ክህሎት ሰልጠና<br>◆ የደገ ተጠቃሚነት<br>◆ ያደገ የስራ ዕድል |
| | **የምርታማነትና የታራሚ ተጠቃሚነትን ዕድጌት ማሻሻል** | ◆ በግብርና ልማት ስራ በማስፋት የምርታማነት ዕድጌትን ማረጋገጥ /የሰብል ልማት የበጋ መስኖ ልማት ስራ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ስራ/<br>◆ የእንስሳት ሀብት ልማት ስራዎችን ማከናውን<br>◆ በግብርና ልማት ስራ ስምርት የታራሚውን የግንዛቤ በማሳደግ የልማታዊ አስተሳሰብ እንድፈጥሩ ማድረግ | ◆ የተቋሙንና ታራሚ ተጠቃሚነትን ማሳደግን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የተቋም ሰላም እና ደህንነት አሰተማማኝነት ማረጋገጥ | ◆ የመረጃ ክትትል ሰርዓትን ማጠናከርን<br>◆ የሎጀስቲክ አቅርቦት ማሟላትን<br>◆ ተንቀሳቃሽ ጥበቃ ስራን ውጤታም መድረግን<br>◆ የበር ፍተሻ ስራ በማጠናክር እና የቁጥጥርና የክትትል ሰርዓትን በማጠናከር የአደጋ ተገላጭነትን መቀነስን | ◆ የተጠናከር የመረጃ ክትትል<br>◆ የተሟላ የሎጀስቲክ አቅርቦት<br>◆ የቀነሰ የአደጋ ተገላጭነት |
| መማማር ና ዕደግት | የተገባቦትና የገፅታ ግንባታ ማሳደግ | ◆ የባለድርሻና እና የአጋር አካላትን ተብብርና እገዛን ማጠናከረርን<br>◆ የኮምንኬሽን ስርዓቶችን በመዘርጋትና የውስጥና የውጭ መረጃዎችን በማሰባሰብ ለተቋሙ ሰራተኞች፣ተገልጋዮችና ለህብረተሰቡ መረጃ መስጠት፣<br>◆ ለማረም ማነጽና ለተቋም ገጽታ ግንባታ የሚረዱ የተለያዩ የሁኔት ፈጠራና የመድረክ ዝግጅቶች ማከናወንን፣<br>◆ ስፖርት ክለቡን በማጠናከር በክልልና በሀገር ውስጥ ስፖርታዊ ውድድሮች ላይበመሳተፍና ውጤታማ በማድረግ የተቋሙንና የክልሉን ገጽታ መገንባትን፣<br>◆ የመሰክ ጉብኝት፣ የባለድርሻ አካት የጋራ ውይይት፣የአፈፃፀም ግምገማ መድረክ እና የተገልጋይ ማህበርሰብ ጋር ውይይት በማካሄድ የተቋም እሴት ግንባታ ማሳደግን ያካትታል | ◆ የተገነባ የተቋም መልካም ገጽታ<br>◆ ያደገ ስፖርታዊ ውድድር<br>◆ ያደገ የተገልጋይ ማህበርሰብ ጋር ውይይት |
| | የሰው ሀብት ልማት ማሳደግ | ◆ የሰው ሃይል ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት በማድረግ በምልመላ፣ በቅጥር፣ በምደባ እና በዝውውር ማሟላትን፣<br>◆ በዕቅድና ጥናት ላይ የተመሠረተ የረጅም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ስልጠናዎችን መስጠትን፣<br>◆ የሴት ሰራተኞች ተሳትፎና የአመራር ደረጃ እንዲሻሻል ማድረግን፣<br>◆ የሰራተኛውን በቡድን የመስራት ባህል እንዲያድግ በማድረግ ለተቋሙ ተልዕኮ ማሳኪያነት መጠቀምን፣ | ◆ የተሟላ የሰው ሃይል<br>◆ የመፈጸም አቅሙ ያደገ የሰው ሃይል<br>◆ ያደገ የሴት ሰራተኞች አመራር ብቃትና ደረጃ<br>◆ ያደገ በቡድን የመስራት ባህል |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ◆ የሠራተኛው ሥነ-ምግባር እንዲሻሻል በትኩረት መስራትን፣<br>◆ የሠራተኛው የስራ ሞራልና ፍላጎት እንዲፈጠሩ የእርስ በእርስ የተፎካካሪነት ስሜት እንዲኖራቸው የማቲጊያ ሰርዓት ማሻሻልን ያካትታል | ◆ መልካም ስነ-ምግባር ያላቸው ሰራተኞች<br>◆ ተግባራዊ የሆነ ማቲጊያ |
| | **የቴክኖሎጂ አቅም በማሳደግ የመረጃ አሰተዳደር ሰርዓትን ማሻሻል** | ◆ የዳታ ቤዝ አሰራርን አጠቃቀም ባህልን ለማሻሻል የሚያስችል የቴክኖሎጂ ፕሮግራም መተግበር፣<br>◆ የተቋሙን ስራዎች በኮምፒተር ቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን ማድረግን፣<br>◆ የቴክኖሎጂ አቅርቦት ሽፋን ተደራሽ ማድረግ፣<br>◆ የኢንተርኔት ዝርጋታ እንዲጠናከር ማድረግና<br>◆ በቴክኖሎጅ በአጠቃቀም ስርአቱ ላይ የክህሎት ስልጠና መስጠት<br>◆ የመረጃ መሰብሰብያ ፎርማቶችን በማዘጋጀት መረጃዎችን መሰብሰብና ማደራጀት<br>◆ የመረጃና የዳታ ልውውጥ ስርአት አውቶሜት ማድረግ፣<br>◆ የቴክኖሎጂ አይነቶችን መለየት፣ መቅረፅ፣ ማስረፅ፣ መተግበርና ማስተዳደር<br>◆ ሶፍት ዌሮችን ማልማትና መጠቀምን ያካትታል፣ | ◆ ያደገ ተቋማዊ የቴክኖሎጂ አቅም<br>◆ ያደገ ቴክኖሎጂን የመጠቀም አቅም<br>◆ የተሻሻል የቴክኖሎጂ አሰተዳደር |

## 2.6. የስትራቴጂያዊ ግቦች፣ ዓላማና ማስፈፀሚያ ስልት

| የስትራቴጅክ ግብ | የስትራቴጅክ ግብ አላማ | የስትራቴጅክ ግቡን ማስፈፀሚያ ስልት |
|---|---|---|
| **ግብ.1** **የአቅርቦት ተደራሽነትን በማሻሻል የተገልጋይ እርካታን ማሳደግ፣** | በሚሰጡ አገልግሎቶች ‹ የተገልጋዮ አርካታን በማረጋገጥ የአገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል፤ | ▪ የታራሚዎች የምግብ በጀት በየጊዜው ከሚከሰተው የዋጋ ግሽበት ጋር የሚጣጣም ጥናት በማጥናትና ማሻሻያ በማድረግ ፣ ጥራቱን የጠበቀ የምግብ አቅርቦት የታራሚዎች የመኝታ አልባሳት<br>▪ አቅርቦት እንድሟላ ማድረግ<br>▪ ለቀጠሮ አስረኞችና ታራሚዎችን ምግብ ፣ የቀን ፤ የሌሊትና የስራ አልባሳት ፣ የመኖሪያ ቤት አቅርቦትና አገልግሎቶች ፣ የማህበራዊ ፣ የምክክርና የማረም ማነጽ ፣ የትምህርትና ስልጠና አገልግሎቶች የተገልጋይ እርካታ ማስገኘታቸውን ይረጋገጣል፡፡<br>▪ የታራሚጠያቂዎች (ቤተሰብ ፣ የሃይማኖት ፤አባት ፤ ጠበቃ) ካለምንም ስጋት በማስተናገድ ፣ ጥራትና ተደራሽነቱን ማረጋገጥ፡<br>▪ የቅድመ በሽታ መከላከል መርህን መሠረት ያደረገ የግል፣የጋራና የአካባቢ ጤናን በመጠበቅ ሊከሰቱ የሚችሉትን ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን መከላከልና መቆጣጠር ፣ የበሽታ መከላከል እና የፈውስ አገልግሎት ሽፋን ማሳደግ<br>▪ ከኮቪድ 19 ወረርሽኝ መከሰት ጋር ተያይዞ በታራሚዎችና በአባላት ሊከሰቱ የሚችሉ የጤናና ማህበራዊ ቀውሶች በየጊዜው እየተከታተሉ የመፍታት ስራዎቸ ይከናወናሉ፡፡<br>▪ በታራሚ ሰብዓዊ መብት አያያዝ የሚደርገው የክትትልና ድጋፍ በማጠናከር የታራሚው መብት አለመጣሱንና በአግባቡ መከበሩን የማረጋገጥ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡<br>▪ በተቋማዊ የደሰሳ ጥናት ስራ በማ/ቤት የሚከናወኑ የአገልግሎት አሰጣት ፤የማረም ማነፅ ተግባራት አፈፃፀም ጥራት ተደራሽነትን የመፈተሽና የማረጋገጥ ስራዎችን ተግባራዊ በማድረግ<br>▪ የተገልጋይ እርካታ የሚለካበትን የአሰራር ስርዓት መዘርጋትን ያካትታል፡፡ |
| **ግብ.2** **የአገልግሎት** | ኮሚሽኑ በሚሰጠው አገልግሎት | ▪ የተቋሙ የዜጎች ቻርተር ሰነድ ከዜጎች /ተገልጋዮች ፍላጎት ጋር በማጣጣም ማስተካከያ በማድረግ ውጤታማ፣ቀልጣፋ፣ተደራሽነትያለውና፣ተገማች አገልግሎት መስጠት የሚያስችል አስራሮችን ተግባራዊ እንድሆኑ ማድረግ |

| | | |
|---|---|---|
| **ተደራሽነትን ማስፋት** | ጥራትና ቅልጥፍናን በማሳደግ ተደራሽ እንዲሆን በማድረግ እርካታን ማረጋገጥነው፣ | ▪ የፍትህ ደራሽነትን ለማረጋገጥ የቀጠሮ ታሳርዎች ጉዳያቸውን መከታተል ይችሉ ዘንድ የቪዲዮ ችሎቶችን በማስፋፋት ታራሚዎች ባሉበት ቦታ ሆነው የተከሰሰሱበትን ወንጀል የይግባኝ ክርክር በቪዲዩ ችሎት እንዲከታተሉ ከባለድርሻ አካላት በቅንጅት በመስራት የተገልጋዮች እርካታ ማሳደግ<br>▪ የወንጀል ተጠርጣሪዎች፣ የተከሳሾችና የህግ ታራሚዎች ህገ -መንግስታዊ መብታቸውና ሰብዓዊ ክብራቸውን በተሟላ መልኩ መከበሩን ማረጋገጥ የሚስችሉ ተግባራትን መፈፀም<br>▪ የቅሬታ ማስተናገጃ ስራ ክፍሎች በማጠናከር የቅረታ አፈታት ስርዓት በመዘርጋት የመልካም አስተዳደር ችግሮችን መፈታቱን የማረጋገጥ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡<br>▪ የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ መሰረት ተገልጋዩ ታራሚ አገልግሎት በመስጠት እንዲሁም ተገልጋዩች የሚያነሷቸውን ቅሬታዎች በአግባቡ በመቀበል አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት እርካታቸውን ማረጋገጥ ነው<br>▪ የታራሚ የቤተሰቦች የግንኙነት ስርዓት ፤የዝውውር ፤የእርቅ ስምምነት የማህበራዊ አገልግሎት ጥያቄዎችን በፍትሃዊ ተደራሽ ማድረግ<br>▪ ኮሚሽኑ ተልዕኮውን በሕግ አግባብ በመፈፀም፣መረጃዎችን እንደአስፈላጊነቱ ግልጽ በማድረግና ለተገልጋዩ በመስጠት የግልጽነት መርህን በተሟላ መልኩ ይዘረጋል፤<br>▪ የታራሚዎች የእርቅ ጉዳዮች በአግባቡ ተፈፃሚ በማድረግ በማረሚያ ቤትም ሆነ ከፍቺ በኋላ ከማህበረሰቡ ጋር መኖር የሚያስችላቸው የስነ-ልቦና ለውጥ እንዲያመጡ በማድረግ ለመልሶ ማቀላቀል ምቹ ሁኔታን እንድፈጠርላቸው ማድረግ<br>▪ የታራሚዎችን የባህሪ መለወጥ ተከታታይ በሆነ ምዘና ላይ የተመሰረተ መረጃዎችን በማደራጀት፣<br>▪ ግልጽና ፍትሃዊ አሰራር በመዘርጋት የአመክሮና የይቅርታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ታራሚዎችን<br>▪ ከታራሚዎችና ከታራሚቤተሰቦች (የህዝብ ክንፍ) ቋሚ የውይይት መድረኮች ማዘጋጀት፣<br>▪ የታራሚዎች የፍትህ አስተዳደር ጥያቄዎች የታራሚዎች የፍቺ ትዕዛዞችን የማስተናገድ አቅምና ግልጽነት ማሻሻል፣<br>▪ ታራሚዎች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር አቅም ማሳደግ እንድችሉ የታራሚዎች የኮሚቴ አደረጃጀት ግልፅነትና በታራሚዎች ነፃ ፍቃድ እንድደራጁ ማድረግ |

| | | |
|---|---|---|
| ግብ.3 የሀብት አስተዳደርና አጠቃቀም ስርዓት ማሻሻል | የፕሮግራም በጀት መርህን በመተግበር ፍትሃዊ የፋይናንስ ፣የንብረት ድልድልና አጠቃቀም በመዘርጋት የተጠናከረ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ማስፈን ነው፡ | ▪ ደንብና መመሪያን የጠበቀ የፋይናንስ አሰራር የፋይናንስ የክፍያ ስርአትን በመከተል የበጀት አስተዳደር መምራት ፡፡<br>▪ የተቋሙን ፍላጎት ያማከለና በዕቅድ የሚመራ፣ጥራቱን የጠበቀ የግዥ አሰራር ይዘረጋል፡፡<br>▪ ፍታሃዊ የሆነ የንብረት ስርጭት፣አጠቃቀም፣እንዲኖርና ብክነት እንዲቀንስ ማድረግን፣<br>▪ ኮሚሽኑ የውስጥ ገቢው ለማረም ማነጽና ተሃድሶ ልማት ማስፋፊያ ለማዋል እንድያስችል የሃብት ምንጮችን የማስፋት ስራዎች ላይ ትኩረት ተሰጦ እንድሰራ ማድረግ ፡፡<br>▪ በገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ስርዓት ላይ ተገቢ ክትትል በማድረግ ገቢውን በአግባቡ መምራት<br>▪ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቱን አፈጻፀም የኦዲት እንስፐክሽን ስራ ተፈጻሚነት በማድረግ አሰራሩእንዲሻሻል ማድረግ<br>▪ ውጤታማና ወጪ ቆጣቢ የሀብት አስተዳደር ሥርዓት በመዘርጋት ከተቋሙ የሚያመነጨውን የውስጥ ገቢ በማሳደግ ገቢውን ለተሃድሶ ልማት ማረም ማነፅ ተግባራት ላይ ማዋል<br>▪ ከተለያዩ አጋርና ተባባር ድርጅቶች የሚሰጡ ድጋፎች ለታለመለት ተግባር እንዲውል በማድረግ የታራሚውን ተጠቃሚነት ለማሻሻል ይሰራል፡፡ |
| ግብ.4 ተቋማዊ አሰራር ስርዓትን ማሻሻል | ኮሚሽኑ በሚሰጠው አገልግሎት ጥራትና ቅልጥፍናን በማሳደግ ፣የግልጽነትና የተጠያቂነት የአሰራር ባህልን በማዳበር የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባራትን | ▪ በመሰረታዊ ስራሂደት /BPR/ ስታንዳርዶች አተገባበር ላይ የሚታየውን የአደረጃጀትና የአሰራር ክፍተት በመፈተሽና በማጥራት አስፈላጊ ማሻሻያዎችን ማድረግ፣<br>▪ በመሰረታዊ ስራ ሂደት ለውጡ /BPR/ እና የውጤት ተኮር ስርዓት ትግበራን /BSC/ ዕቅድ ዝግጅቱንና የአፈጻጸም ምዘናውን በተሟላ ሁኔታ መተግበር፣<br>▪ በስትራቴጂክ ዝግጅት ስረፀት ትግባራ የዕቅድ አፈፃፀም ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የመስክና ድጋፍ ክትትል የሱፐርቪዥን ስራዎች በማከናወናወን የዕቅድ ተፈፃሚነትን እንድረጋገጥ ማድረግ ፡<br>▪ የተቋማዊ አዋጅ ፣ደንብ፣፣የመመሪያዎች፣የስታንዳርዶችና አሰራሮች ክለሳ፣ዝግጅት፣ የተፈፀምነትና ደረጃ ክትትል ስራ ተግባራዊ ማድረግ<br>▪ የማረሚያ ፖሊስ መተዳደሪያና የታራሚዎች መተዳደሪያ ደንቦችን ልዩ ልዩ መመሪያዎች እና የግልጽነትና የተጠያቂነት ስርዓትን ማስፈን የሚያስችሉ የስነ-ምግባር እሴቶችን በመቅረጽ ተግባራዊ ማድረግ ፡፡<br>▪ በማረሚያ ቤቶች አሰራር፣በታራሚዎችን አያያዝና አስተዳደር በማረም ማነፅ ስራ ዘርፎች ዙሪያ ጥናትና ምርምር ስራ ተግባራዊ ማድረግ |

| | | |
|---|---|---|
| | በመዋጋት የመልካም አስተዳደር ስርአት ግንባታን ማረጋገጥ፣ | ▪ ለአገልግሎት አሰጣት ማነቆ ሆኖ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት የተጀመሩትን የሪፎርም ስራዎች አጠናክሮ በማስቀጠል<br>▪ በአገር አቀፍ ደረጃ ለታራሚዎች አያያዝ ፣ የማረም ማነፅ ተግባራት የተዘጋጁ አሰራርን ስታንዳርዶችና ተግባራዊ ማድረግ<br>▪ በተቋም ደረጃ የወጡ ደንቦች መመሪያዎች በአግባቡ ተግባራዊ እንድሆኑ ማድረግ<br>▪ በአሰራር ሂደት በሚፈጠሩ የአሰራርና አፈፃፀምግድፈት ሁሉም ዘንድ እኩል ደረጃ ተፈፃምነት እንድኖር ማድረግ<br>▪ ለስነ- ምግባር ለኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር ተጋላጭ በሆኑት ሰራተኞችና የስራ ክፍሎች በመለየት የሚሰተዋሉባቸውን ክፍተቶች እንድስተካከል የግልጽነትና ተጠያቂነት አሰራር እንዲሰፍን ይደረጋል፡፡<br>▪ ከሁኔታዎች ተለዋዋጭነት ጋር የሚጣጣሙ አዳዲስ አሰራሮችን በመቅፈጽና በማሻሻል የተገልጋዮች እርካታ ማሳደግ የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናውን<br>▪ የፌደራልና የክልል ማረ/ቤቶችን የጋራ የምክክር ጉባኤ በክልል ደረጃ በማዘጋጀት በፌደራልና በክልሎች በተለያየ ደረጃ በሚገኙ የማረሚያ ተቋማት የአደረጃጀትና የአሰራር ምርጥና ተሞክሮዎች መቀመር እና ከተቋማቱ ጋር መካከልና ጠንካራ ግንኙነት እንዲፈጠር ይደረጋል<br>▪ የማረሚያ ፖሊስ የምልመላ ፣ የቅጥር ፣ የስልጠና ፣ የደረጃና የሀላፊነት ዕድገት ፤የመደበኛ ፖሊስ ስልጠና የማዕረግ ሽግግር ስልጠናና የረጅም ጊዜ የሙያ ማሻሻያ ስልጠና ከፈደራልና ክልል ማ/ቤቶች ጋር ውጥነት ባለው አግባብ ተግባራዊ እንድሆን ማድረግ |
| **ግብ.5 የማ/ቤቶችን ሠላምና ደህንነት አስተማማኝነት ን ማረጋገጥ** | የጥበቃ ደህንነትና የፍትህ አስተዳደር ስራዎችን በመስራት፣የቅጣት ውሳኔዎችን ማስፈፀም፣ሰብአዊ መብቶች በማክበር | ▪ የጥበቃ፣ደህንነትና አስተዳደር ስራዎችን አስተማማኝ ለማድረግ የሚያስፈልጉ የዘመናዊ ቴክኖሎጅ መሳሪያዎችና ግብአቶችን በማሟላት<br>▪ ጠንካራ የመረጃ የክትትል ቁጥጥር ስርዓት በማጠናከር የማ/ቤት ሠላምና ደህንነት እንድረጋገጥ ማድረግ<br>▪ የፖሊስ አባላትን የስነ- ምግባር ጉድለቶችንና የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም በስልጠና በማጎልበት፣የአገልግሎቱን ውጤታማነት የማሳደግ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡<br>▪ የህግ በበላይነትንና ሰብአዊ መብቶችን ጠበቃ ማረጋገጥ የሚያስችል የጥበቃና ደህንነት ስራውን በአስተማማኝ ደረጃ ላይ በማድረስ ታራሚዎች በሠላማዊ ሁኔታ ውሳኔያቸውን እንዲፈጽሙ ማድረግ |

| | | |
|---|---|---|
| | የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ ነው፡፡ | ▪ ልዩ ልዩ ትጥቆች እና ልዩ ልዩ የጥበቃ በማሟላት አገልግሎቶቹን የማሳደግ ስራዎች ይከናወናሉ፤፡<br>▪ የማረሚያ ፖሊስ አልባሳትና ትጥቅ ላይ የሚታየውን የጥራት ክፍተት በማጥናት የጥበቃ አገልግሎት ጥራትና ተገቢነትን የማረጋገጥ ሥራ ይሰራል፡፡<br>▪ ታራሚዎች ከማናቸውም የሁከትና ብጥበጥ እንድሁም ከስርዓት አልበኝነት አካሄድ ነፃ ሆኖ ህግና ስርዓቱን እንድያከብሩ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የማ/ቤቱ ሠላም እንድረጋገጥ ይደረጋል |
| **ግብ-6 የህግ ታራሚዎችን የማረምና የማነጽ ውጤታማነትን ማሳደግ፣** | ታራሚዎችን በማረምና በማነፅ የባህሪ ለውጥና የእውቀትና የክህሎት ለውጥ በማምጣት አምራች ዜጋ እንዲሆኑ ማስቻል ነው፡፡ | ▪ ለህግ ታራሚዎች የማህበራዊና የሥነ-ልቦና አገልግሎት የሥነ ዜጋና የሥነ ምግባር ትምህርት እና ስፖርትና መዝናኛ አገልግሎት በመስጠት ለእርምት ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡<br>▪ የህግ ታራሚዎች በመደበኛ ትምህርት የተቀናጀ ተግባር ተኮር ጎልማሶች መሠረተ ትምህርት በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተጠቃሚ ማድረግ፣<br>▪ በምክር አገልግሎት ድጋፍ ፣የንቃተ ህግና የታራሚዎች ስነ-ምግባር ማሻሻያ ግንዛቤ ማሳደጊያ ት/ት በማጠናከር የታራሚውን የባህር ለውጥ ስራን ውጤታማ ማድረግ<br>▪ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በቅንጅትና በትብብር በመስራት የታራሚውን የንቃተ ህግ ደረጃ በደረጃ በማሻሻል ህግና ስርአት የሚያከብርና ህግ አክባር እንድፈጠር በንቃት የሚሳተፍና የሚደግፍ ስርዓት አንድፈጥሩ ማድረግ<br>▪ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የሰለጠኑ የህግ ታራሚዎች በስራ ማህበራት በማቋቋምና በማደራጀት የህግ ታራሚዎች ከትርፍ ክፍፍልና ቁጠባ ተጠቃሚ ማድረግ፣<br>▪ በተለያየ ሙያ ሰልጥነው በልማትና በምርት ስራ መሳተፍያ ለባቸው ሁሉም ታራሚዎች እንዲሳተፉ በማድረግ ገቢያቸው እንዲያድግ ይደረጋል፡፡<br>▪ ታራሚዎች አነስተኛ ኢንዱስትሪ ልማት ስራ በማስፋፋት ወደ ስራ በማስገባት ሰልጣኞችን ማሰልጠንና ምርት ስራ ታራሚውን በማሳተፍ ተጠቃሚ ማድረግ፣<br>▪ በሀገር ደረጃ የወጣ የታራሚ ማረም መነፅ ተሃድሶና ልማት አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ፣መመሪያዎችና ማንዋሎችን ማዘጋጀት በሁሉም ማ/ቤቶች ተግባራዊ እንድሆኑ ማድረግ<br>▪ ማ/ቤቶቻችን በትምህርትና ስልጠና ስርዓትን ባለቤትና በኂላፊነት መምራት በሚችሉበት ደረጃ ላይ እንድደረስ ማድረግ<br>▪ በሁሉም ማረሚያ ማእከላት የትምህርትና ስልጠና ተቋማት በመንግስት ስታንዳርድ መሠረተ ልማት በመገንባትና |

| | | |
|---|---|---|
| | | በማሟላት በተገቢው ጥራትና አግባብነት መሰረት የተሀድሶ ልማት አገልግሎት መስጠታቸው ይረጋገጣል፡፡<br>▪ የትምህርት ፣ የምርትና የልማት ተቋማትን ደረጃ ማሳደግና አዳዲስ የስልጠናና የምርት ተቋማት በማቋቋም መማርና መሰልጠን የሚገባቸው ሁሉም ታራሚዎች እንዲማሩና እንዲሰለጥኑ ይደረጋል፡፡<br>▪ በሁሉም ማዕከላት የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋት ታራሚዎችን በኢንዱስትሪ ልማት በማሰልጠን ወደ ሥራ በማሰማራት የታራሚዎችና የተቋሙን ገቢ እንዲያድግ ይደረጋል፣<br>▪ በየደረጃው የተጠናከረ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት በመዘርጋት በታራሚ ማነፅ ዘርፍ ያሉ ክፍተቶችን በማስተካከል የማረምና ማነጽ ስራዎች አፈፃፀም ጥራትና ውጤታማነትን ማሳደግ ፡፡<br>▪ የደጋጋሚ ወንጀለኛነት አመለካካት ያላቸው ታራሚዎች ለመቀነስ የሚያስችል የአሰራ ስርዓት በመዘርጋት ደጋጋሚነት ማስቀረት የሚያስችሉ ተግባራትን መፈፀሚ፡፡ |
| **ግብ.7 ምርታማነትና የታራሚ ተጠቃሚነትን ማሻሻል** | በግብርና ልማት ስልጠናና የስራ ስምርት ለምርታማነት የሚያበቃ አቅሙ ያሳደገ ታራሚ መፍጠር | ▪ የተሻሉ ተሞክሮዎችን በማስፋትና በማሳደግ የተሀድሶ ልማት አገልግሎትና ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡<br>▪ በማረ/ማዕከላት የግብርና እና የኢንዱስትሪ ልማት(ማምረቻ ማእከላት) በማስፋፋት፣ የህግ በታራሚዎች ልማት ተሳትፎ ተቋማዊ ገቢ ማሳደግ<br>▪ አዲስ የማረሚያ ግብርና ልማት ተቋም በማቋቋም እና በማስፋፋት የህግ ታራሚዎች ግብርና ልማት በእንስሳት ሀብት ልማት ስራ በማስፋት የታራሚዎችንና የተቋሙን ገቢ እንዲያድግ እና የማ/ቤቶች ማዕከላት ለአከባቢው ገበሬዎች የሰርቶማሳያ ማዕከላት ማድረግ<br>▪ የህግ ታራሚዎች በልማት ስራዎች በማሳተፍ የዕውቀት የሙያ ክህሎት ባለቤት ሆነው የልማቱም ተጠቃሚ እንድሆኑ ማድረግ<br>▪ የማ/ቤት የግብርና ልማት ስራ በዘመናዊ ማካናይዜሽን በማስደገፍ የምርታማነት ዕድጌት እንድረጋገጥ<br>▪ የአከባቢ ገበያ የማረጋጋ አቅም እንድፈጠር የበጋ መስኖ ልማት ስራ በማጠናከከር ለማ/ቤቱና ለአከባቢው ማህበረሰብ ተደራሽ ማድረግ<br>▪ ታራሚዎች በእንስሳት እርባታ ፤በማድለብ ፤በንብ ማነብ ተግባራት ፤በዓሳ ሀብት ልማት ስራ በማሰማራት የእንስሳት ሀብት ልማት ማሳደግ |

| | | |
|---|---|---|
| ግብ.8 የአገልግሎት መስጫ መሰረተ ልማት አደረጃጀት ማስፋት | በሁሉም ማረሚያ ማዕከላት የአስተዳደር ህንጻ፤የታራሚ የመኖሪያ፤የአገልግሎትመስጫና የስልጠና ተቋማትን በማሻሻል አገልግሎትን ማሳደግ፣ | ▪ በሁሉም ማረሚያ ቤቶች የተገነቡና እየተገነቡ ያሉ በቀጣይ የሚገነቡ ነባር ማ/ቤቶች የታራሚዎች መኖሪያ ቤቶች፣ የአገልግሎት መስጫ ተቋማት የህግ ታራሚዎችን አኗኗር በማሻሻል ሰብአዊ መብት በሚያስከበር ስራ መልኩ የፍሳሽ ማስወገጃ ፤የምግብ ማብሰያ ፤የመመገቢ አደራሽ ፤ህክምና ማዕከላት እና ለሎች የውስጥ ፋሲሊቲዎችን በማሟላት እንድካሄድ ማድረግ<br>▪ የት/ትና ስልጠና ማዕከላት በአሰራር በአደረጃጀት በማሻሻል የት/ትና ስልጠና ተደራሽነትን ማስፋት<br>▪ አዳድስ የቅርጫፍ ማ/ቤት ግንባታ ፤የውጣቶች ህፃናት ማቆ ማእከላት ግንባታ ፤የፖሊስ አባላትመኖሪያካምፕ ግንባታ ስራ በመጀመሪያው 5 ዓመት የስትራቴጂክ ዘመን ዲዛይኖች ስራና የግንባታ ስራ እንድካሄድ ማድረግ ፡፡<br>▪ ድርጅታዊ አቅምን ማሳደግ የሚያስችሉ ሎጅስትክ አቅርቦት እንድሟላ ማድረግ /ተሽከርካሪ፣ የልዩ ልዩ ስልጠና ማቴሪል አቅርቦት |
| ግብ.9 የዘርፈብዙጉዳዮችንአካቶመስራትንማሳደግ፣ | በሁሉም ማረሚያ ማዕከላት የአስተዳደር ህንጻ ፤የታራሚ የመኖሪያ፤ የአገልግሎት መስጫና የስልጠና ተቋማትን በማሻሻል አገልግሎትን ማሳደግ፣ | ▪ ሁሉም የስራ ክፍሎች ስርዓተ ጾታን፣ከኤች አይ ቪ ቫይረስ ጋር የሚኖሩ አባላት፣ሰራተኞችና ታራሚዎችን፣ ለአእምሮ ህሙማንና ለአረጋውያን እንዲሁም ወላጅ አልባና ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የአባላት ልጆችን መደገፍ<br>▪ የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ጉዳዮች በትኩረት መስራት<br>▪ የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን አካታችነትን አሟልቶ የሚታቀድና የሚተገበር ይሆናል፡፡<br>▪ የአቅም ውሱንነት ያለባቸውን ሴቶች በትምህርትና ስልጠና በማብቃት ወደ አመራርነት እንዲመጡ በማድረግ ባሉባቸው የኃላፊነት ቦታዎች ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ይሰራል፡፡<br>▪ በተለያዩመቃቅሮች ላይ የሴቶችን ተሳትፎከፍ ማድረግ ፡፡<br>▪ የማረሚያ ቤት አገልግሎቶች ለአካል ጉዳተኞች ፣ ለአእምሮ ህሙማንና ለአረጋውያን ምቹና ተደራሽ እንዲሆኑ ትኩረት በመስጠት ይከናወናል፡፡<br>▪ የሴቶችና ህጻናት ህገ- መንግስታዊ መብቶችን ነፃነቶችና በሁሉም ማረሚያ ቤቶች እንዲከበሩ የተለየ ድጋፍና ክብካቤ ይደረጋል፡፡<br>▪ ለነፍሰጡር፣ለመጫትና ለህመምተኞች የተለዬ ቦታ ይዘጋጅላቸዋል፡፡<br>▪ ከወላጆቻቸው ጋር በማረሚያ ቤት ለሚኖሩ ህፃናት ትምህርት፣መጫወቻና የጽዳት መጠበቂያ ቁሳቁሶችን በቋሚነት |

| | | |
|---|---|---|
| | | እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡<br>▪ ለኤች አይ ቪ ህመምተኞች ተጨማሪ ምግብ ፣መድሐኒት፣የግል ንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁስ እንዲሟሉላቸው እና የሥነ ልቦና ምክር አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ አስፈላጊ የሆኑ ድጋፎች ይደረግላቸዋል፡፡<br>▪ በአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ስራ የተቋሙ አመራር አባላት እና የህግ ታራሚዎች ጉልህ ተሳትፎና ከፍተኛ ድርሻ እንዲኖራቸው በማድረግ አካባቢንና የተፈጥሮ ሃብትን የማይጎዳ የማገዶ አጠቃቀም አማራጭ የሀይል ምንጮች ይስፋፋሉ፡፡ |
| **ግብ.10 የተግባቦትና የገፅታ ግንባታን ማሳደግ፣** | የፌዴራልና የክልል ማረሚያ ቤቶችን ራእይ፣ተልእኮና ግብ ለህብረተሰቡና ለባለድርሻ በማስተዋወቅ በማረም ማነጽ ተግባር ተሳታፊ እንዲሆኑ ማስቻል ነው፡፡ | ▪ የኮሙንኬሽን ስርዓቶችን በመዘርጋትና የውስጥና የውጭ መረጃዎችን በማሰባሰብ ለተቋሙ ሰራተኞች፣ተገልጋዮችና ለህብረተሰቡ መረጃ መስጠት፣መረጃዎችን በማህበራዊ ድረ-ገጾች ላይ በመጫንና ወቅታዊ ጉዳዮችን ለህብረተሰቡ ተደራሽ የማድረግ ስራ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡<br>▪ ተቋሙ ከኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች የአየር ሰዓት ሽፋን ተጠቃሚ በማድረግ መረጃውን ለማህበረሰቡ ተደራሽ ማድረግ<br>▪ በዕቅድ ዝግጅትና በአፈፃፀም ግምገማ ፣በመልካም አስተዳደርና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ከሰራተኞች፣ ከፍትህ አካላት፣መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ከአካባቢው ህብረተሰብ ጋር መልካም ግንኙነትና የጋራ መድረኮች መፍጠር፤<br>▪ የተለያዩ የኮሙዮኒኬሽን ስራዎችን በመጠቀም የማረ/ቤቶች ዓላማና ተልዕኮ የመንግሥትና ሌሎች ተቋማትና ሕብረተሰቡ በአግባቡ እንዲገነዘቡ በማድረግ በማረም ማነጽ ስራዎች ላይ ተሳትፎ በማሳደግ የህብረሰብ አቀፍ የእርምት ሂደትን ለማጎልበት የህዝብ ንቅናቄን መፍጠር፣<br>▪ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር መልካም ግንኙነትና ትብብር በመፍጠር በተቋማዊ አቅም ግንባታ፣በማረም ማነጽ እና በጸጥታ ጉዳዮች ላይ በዕቅድ መስራት፣ከህዝብ ክንፍ ጋር ቋሚ የውይይት መድረኮች በማዘጋጀት ተሳታፊ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡<br>▪ ማረ/ቤቶችን ለሁሉም መረጃ ጠያቂ ክፍት በማድረግ ተቋሙ በሁሉም ዘርፎች የሚሰጣቸው አገልግሎቶች ህብረተሰቡ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረውና መረጃው ተደራሽ በማድረግ የህዝብና የመንግስት አመኔታን እንዲያድግ ማድረግ<br>▪ መጽሔት፣ጋዜጣ፣ብሮሽር፣በራሪወረቀቶች፣ካሌንደር፣አጀንዳና ፖስተር በማዘጋጀት መረጃዎች እንዲተላለፉ ይደረጋል፡፡<br>▪ ለማረም ማነጽናለ ተቋም ገጽታ ግንባታ ስራ አጋዥነት እንድውል በታራሚዎች የተመረቱ የዕደ ጥበብ ስራዎችና |

| | | |
|---|---|---|
| | | የፈጠራ ስራዎችን በአከባቢው በሚዘጋጁ የባዛርና ኢግብሽንመድረክ ማቅረብ<br>▪ ኪነ ጥበባዊ መዝናኛ እንቅስቃሴዎችን በማከናወን፣ታራሚዎች በሙዚቃ መሳሪያና በድምጽ ይሰለጥናሉ፡፡ በሙዚቃ የሰለጠኑ ታራሚዎች ልዩ ልዩ የፈጠራና ኮፒ ስራዎችን በማዘጋጀት ሌሎች ታራሚዎችን እያዝናኑ ያስተምራሉ፡፡ታራሚውዎችና አባላት ትምህርታዊ ፕሮግራሞች እና የመዝናኛ አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡<br>▪ ስፖርት ክለቡን በማጠናከር ስፖርታዊ ውድድሮች ላይ በመሳተፍና ውጤታማ በማድረግ የተቋሙንና የአገርን ገጽታ ግንባታ ይከናወናል፡፡ |
| **ግብ 11 የሰውሀይልልማ ትንማሳደግ፣** | ▪ በአመለካከቱ፣ በዕውቀቱና በክህሎቱ ብቁና የተሟላ ስብዕና የተላበሰ፣ የኮሚሽኑ ተልእኮ በብቃት የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ያለው የሰው ኃይል መፍጠር ነው፡፡ | ▪ በስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመኑ ከላይኛው እስከ ታችኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ ለሚገኙ አስፈጻሚ አካላት የተለያዩ የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡<br>▪ የሰው ሃይል ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት በማድረግ በምልመላ፣በቅጥር፣በምደባ እና በዝውውር ለማሟላት የሚታዩትን ክፍተቶች በመለየት የተቋሙን ተልእኮ ሊያሳኩ የሚችሉ የሰው ኃይል ማሟላት<br>▪ የአቅም ግንባታ ስራዎች ይከናወናሉ የማረሚያ ፖሊስ እና የሲቪል ሠራተኞችን ማሟላት፣የሴት ሰራተኞች ተሳትፎና የአመራር ደረጃ እንዲሻሻል ማድረግ፣<br>▪ የትምህርት መስኮች በአጭር ጊዜ ሥልጠና መደበኛ የማረሚያ ፖሊስ ስልጠናና ከዲፕሎማ በላይ ባሉ የትምህርት እርከኖች በማሰልጠን የመካከለኛና የበታች አመራሮችን አቅም መገንባት ፡፡<br>▪ በተቋሙ በየደረጃው ያለው የሰው ሀይል በአመለካከቱ፣ በዕውቀቱና በክህሎቱ ለማብቃት በህገ- መንግስት ፣በተቋሙ ልዩ ልዩ ህግጋት እና በአሰራር ስርዓት የግንዛቤ ማሻሻያ ስልጠና በመስጠት ግንዛቤያቸውን በማስፋት ተቋማዊ ለውጥን በብቃት መምራት በሚያስችል ደረጃ ላይ ማድረስ<br>▪ የሰው ኃይል መብትና ጥቅማ ጥቅም በአግባቡ እንድከበር ማድረግ<br>▪ የስራ ብቃት ማረጋገጫ፣የፈጻሚና የቡድን ማበረታቻ እንዲሁም የተቋማት ማወዳደሪያ ስርዓቶችን ተግባራዊ በማድረግ የሰራተኛ የስራ ሞራል ግንባታ ስራ ተግባራዊ እንድሆኑ ይደረጋል ፡፡<br>▪ የአሰራር ፍትሃዊነትና ግልፀኝነት ስርዓት በማስፈን የሠራተኛውን እርካታ ማሳደግ |

| | | |
|---|---|---|
| **ግብ.12 የቴክኖሎጂ ተጠቃምነት አቅምን በማሳደግ የመረጃ አስተዳደር ስርዓት ማሻሻል** | የኮሚሽኑ የቴክኖሎጂ አቅምን በማሳደግ የመረጃ አያያዝና አደረጃጀት በማሻሻል የአሠራርን ቀልጣፋና ተደራሽ ማድረግ ነው፡፡ | ▪ አገልግሎቶችን በኢንፎርሜሽን ኮሙዮኒኬሽን ቴክኖሎጂ የተደገፉ ማድረግ ስራዎች ተጠናክረው ይተገበራል<br>▪ ዕውቀትና ልምድ ያላቸውን ሙያተኞችን በመሟላት በማረሚያ ቤቶች የሲሲ ቲቪ ካሜራና የፍተሻ መሳሪያዎች የጣትና አሻራ መሳሪያዎች እንዲሟሉ ይደረጋል፡፡<br>▪ ማ/ቤቶችን የሬዲዮ መገናኛና ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆን ይደረጋል፡፡<br>▪ የኮሚሽኑ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣በማደራጀትና በመተንተን የሚያሰራጭ ማዕከላዊ መረጃ ቋት<br>▪ ዳታ ቤዝ መረጃ ስርዓት በማደራጀት ኮሚሽኑ ከዞን ማረሚያ ቤቶች ጋር እንዲሁም አንድ የሥራ ሂደት ከሌላው የስራ ሂደት ጋር የሚደረጋቸውን የመረጃ ልውውጦች ዘመናዊ ቴክኖሎጂን መሰረት ያደረገ እንዲሆን ይደረጋል፡፡<br>▪ በሁሉም ማዕከላት የመረጃ ማዕከላትን በማደራጀትና ዘመናዊ የመረጃ አያያዝና ስርጭት ሥርዓት በመዘርጋት ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግን ያካትታል፡፡<br>▪ ሙያተኞችንና አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎችን በማሟላት የተቋሙ አጠቃላ ይመረጃዎች፣ ታራሚዎችና ሰራተኞች መረጃ በዳታ ቤዝ እንዲያዝ ይሠራል፡፡<br>▪ የተቋሙ መረጃዎች በአግባቡ በማደራጀት ዘመናዊ አሰራርን አጠቃቀም ባህልን ለማሻሻል የሚያስችል የቴክኖሎጂ ፕሮግራም የሚተግበር ይሆናል፡፡<br>▪ የታራሚዎችና የማረሚያ ቤት ልዩ ልዩ የስታቲስቲክስ መረጃዎች በማደራጀት ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡ |
| | | ▪ የአይ ቲ ሙያተኞች ተገቢውን ስልጠና እንዲያገኙ በማድረግ የጥገና ስራ ሙሉ ለሙሉ በተቋሙ ሙያተኞች እንዲከናወን በማድረግ ዘመናዊ አሰራርን አጠቃቀም ባህልን ለማሻሻል የሚያስችል የቴክኖሎጂ ፕሮግራም የሚተግበር ይሆናል፡ |

## 2.7. ግቦች መለኪያዎችና ተደራሽ ኢላማዎች፡-

| እይታ | የእይታ ክብደት | የስትራቴጂክ ግቦች | የግብ ክብደት | የግቦች መለኪያዎች | የመለኪያ ክብደት | 2012 ተደራሽ | የ5 ዓመት ኢላማ | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተገልጋይ | 20% | የአቅርቦት ተደራሽነትን በማሻሻል የተገልጋይ እርካታን ማሳደግ፣ | 10% | የተካሄደ የታራሚዎች የአቅርቦት ማሻሻያ ጥናት ብዛት በቁጥር | 3 | 3 | 1 | - | - | 1 | - | - |
| | | | | የተሟላ የአቅርቦት መጠን ጥራት ተደራሽነት ዕድጌት በመቶኛ | 4 | 60% | 20% | 62% | 65% | 69% | 74% | 80% |
| | | | | የተካሄደ የእረካታ ማረጋገጫ ደሰሳ ጥናት ብዛት በቁጥር | 3 | 1 | 5 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| | | የአገልግሎት አሰጣጥ ተደራሽነትን ማስፋት | 10% | የማህበራዊ አገልግሎት ምላሽ አሰጣጥ ተደራሽነት ዕድጌት በመቶኛ | 2 | 68% | 16% | 71% | 74% | 77% | 80% | 84% |
| | | | | ስታንዳርድን መሰረት ለተገልጋዩ የተሰጠ አገልግሎቶች ዕድጌት በመቶኛ | 2 | - | 20% | 50% | 55% | 60% | 65% | 70% |
| | | | | ከተገልጋዩ ማህበረሰብ ጋር የተካሄዱ የምክክር መድረክ ብዛት | 2 | - | 20 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 |
| | | | | የታራሚዎች ፍትህ አስተዳደር ተደራሽነትን ዕድጌት በመቶኛ | 2 | 68.5% | 15.5 % | 71% | 74% | 77% | 80% | 84% |
| | | | | የቅረታ ምላሽ አሰጣጥ ዕድግት በመቶኛ | 2 | - | 25% | 50% | 55% | 62% | 68% | 75% |
| ፋይናንስ | 10% | የሀብት አስተዳደርና አጠቃቀም ስርዓት ማሻሻል | 10% | የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነት ዕድጌት በመቶኛ | 4 | 90% | 10% | 92% | 94% | 96% | 98% | 100% |
| | | | | የተሰበሰበ የውስጥ ገቢ ዕድጌት ምጣኔ በሚሊዮን | 4 | 14,496, 906 | 248411 80 | 3,450 000 | 4,140, 000 | 4,968, 000 | 5,713,2 00 | 6,570, 180 |
| | | | | የኦዲትና እንስፔክሽን ትግበራ ብዛት በቁጥር | 2 | 1 | 5 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 |

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ውስጥ አሰራር | 50% | የአሰራር ስርዓትን ማሻሻል | 8% | የማሻሻያና ክላሳ የተደረገ አድስ የወጡ አዋጅ ፤ደንብ ፤መመሪያና የአሰራር ማኑዋል ብዛት በቁጥር | 2 | 7 | 9 | 3 | 3 | | - | 3 |
| | | | | የስትራቴጂክ ዝግጅት የግንዛቤ ፈጠራ የአፈፃፀም ድጋፍ ፤ክትትል ተፈፃምነት ዕድጌት በቁጥር | 2 | 19 | 25 | 6 | 4 | 5 | 4 | 6 |
| | | | | በጥናትና ምርምር ላይ ተመስርቶ የተካሄደ ማሻሻያ ስራ ብዛት | 1 | 1 | 1 | - | - | 1 | - | - |
| | | | | ስታንዳርድ ወጦለት ስራ ላይ የዋለ የአገልግልት ብዛት | 1 | - | 4 | 2 | - | - | - | 2 |
| | | | | ተሞክሮ የተቀመረባቸው የስራ ዘርፎች ብዛት | 1 | 1 | 100 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 |
| | | | | የድንቦች፣መመሪያዎች ተፈፃሚነት ዕድግት በመቶኛ | 1 | - | 20% | 60% | 65% | 70% | 75% | 80% |
| | | የማ/ቤቶችን ሠላምና ደኅንነት አስተማማኝነትን ማረጋገጥ | 10% | የቋምና ተንቀሳቃሽ የጥበቃ ደህንነት ስራ ውጤታማነት ዕድጌት | 3 | 75% | 25% | 80% | 85% | 90% | 90% | 100% |
| | | | | የጥበቃ ደህንነት የሎጀስትክ አቅርቦት ተደራሽነት ዕድጌት | 3 | 63% | 37% | 78% | 83% | 88% | 93% | 100% |
| | | | | በመረጃ ክትትል በቁጥጥርና ፈተሻ ጥራት የቀነሰ የአደጋ ተጋላጭነት | 2 | 2 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| | | | | የተሻሻለ ዘመናዊ የጥበቃ ደህንነት የቴክኖሎጅ አቅርቦት የተሟላላቸው ማ/ቤቶች ብዛት | 2 | 4 | 2 | - | 1 | - | 1 | - |
| | | የተሃድሶ ልማትና ማረም ማነፅ ውጤታማነትን ማሳደግ | 10% | የምክር ፤ የስነ-ምግባር ማሻሻያ ድጋፍ አገልግሎት ተደራሽነት በቁጥር | 3 | 25,747 | 138,139 | 25,000 | 26,250 | 27,562 | 28,940 | 30,387 |
| | | | | የት/ት የሙያ ክህሎት ስልጠና ተሳታነት ታራሚ ብዛት ቁጥር | 3 | 8,177 | 4852 | 933 | 951 | 970 | 989 | 1009 |
| | | | | በሰለጠኑበት ሙያ የገቢ ማስገኛ ስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ታራሚዎች ብዛት | 2 | 1209 | 1002 | 165 | 181 | 199 | 218 | 239 |
| | | | | የማረም ማነፀ ተግባራት አፈፃፀም ጥራት | 2 | - | 20% | 50% | 55% | 60% | 65% | 70% |

| | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕድገት በመቶኛ | | | | | | | | |
| | | **የምርታማነትና የታራሚ ተጠቃሚነትን ዕድገት ማሻሻል** | 9% | በግብርና ልማት ስራ ስምርት ተሳትፎ የዳበረ ዕውቀትና በክህሎት ታራሚ ቁጥር | 3 | 40,258 | 67332 | 12,185 | 12,795 | 13,434 | 14,106 | 14,812 |
| | | | | በግብርና ልማት ስራ የለማ የመሬት ሽፋንና የምርት ምጣኔ ዕድገት በጥምርታ | 3 | 234.5 ሄክ/4,64 4ኩ.ታ | 1127 ሄክ/ 24794 ኩ.ታ | 97 ሄክ/ 2134ኩ.ታ | 175 ሄክ/ 3850ኩ.ታ | 230 ሄክ/ 5060 ኩ.ታ | 280ሄክ/ 6160 ኩ.ታ | 345 ሄክ/ 7590ኩ.ታ |
| | | | | የእንስሳት ሀብት ልማት ዕድገት መጠን በቁጥር | 3 | 1,314 | 2482 | 406 | 447 | 492 | 541 | 596 |
| | | **የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት አደረጃጀትን ማስፋት** | 8% | የደረጃ ዕድጌት የአደረጃጀትና የአሰራር ማሻሻያ የተደረጉ የት/ት የስልጠና ማዕከላት ብዛት በቁጥር | 2 | 2 | 3 | - | 1 | - | 1 | 1 |
| | | | | የማስፋፍያ ግንባታና ዕድሳት የተደረገ ነባር ማ/ቤቶች ብዛት | 2 | 1 | 1 | 1 | - | - | - | - |
| | | | | የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት ተሟልቶላቸው አድስ የተከፈቱ የቅርንጫፍ የማ/ቤት ብዛት | 1 | - | 1 | - | - | - | 1 | - |
| | | | | የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጅ ዝርጋታ የተደረገባቸው ማ/ቤት ብዛት | 1 | - | 2 | - | 1 | - | - | 1 |
| | | | | በክልልና በዞን ደረጃ የሚመራ የተደራጀ የልማት ማዕከል ብዛት | 2 | 3 | 1 | - | 1 | - | - | - |
| | | **የዘርፍ ብዙ ጉዳዮችና አካቶ መስራትን ማሳደግ** | 5% | ልዩ ድጋፍና እገዛ የሚሹ አካላት የተጠቃሚነት ዕድጌት | 1 | 63% | 17% | 66% | 69% | 72% | 76% | 80% |
| | | | | የሴቶች የተሳትፎ ተጠቃሚነት ደረጃ ዕድጌት | 1 | 66% | 5.7% | 67.7% | 68.7% | 69.7% | 70.7% | 71.7% |
| | | | | በማ/ቤቶች የተደራጀ የህፃናት ማቆያ ማዕከላት ብዛት | 1 | 1 | 1 | - | 1 | - | - | - |
| | | | | በአከባቢና ተፈጥሮ ሀብት ልማት የተተከለ ችግኝ ብዛት በቁጥር | 1 | 20,902 | 100,000 | 20,000 | 20,000 | 20,000 | 20,000 | 20,000 |

| | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የኤች አይቭ ኤዲስ የመከላከል ግንዛቤ ፈጠራ ት/ትና ድጋፍ እገዛ ተደራሽነት በቁጥር | 1 | - | 18,000 | 1200 | 2400 | 3600 | 4800 | 6000 |
| መማማርና ዕድገት | 20% | የሰው ሀብት ልማትን ማሳደግ | 10% | በቅጥርና ስልጠና ሙሌት ያደገ የሰው ኃይል በመቶኛ | 1 | 526 | 761 | 75 | 315 | 63 | 248 | 60 |
| | | | | በት/ትና ስልጠና የማስፈፀም ብቃቱ ያደገ የሰው ኃይል መጠን | 2 | 429 | 681 | 122 | 130 | 136 | 143 | 150 |
| | | | | በተሃድሶ ስልጠና የሙያ ስኑ ምግባሩን ያዳበረ የፖሊስ ኃይል በቁጥር | 2 | 138 | 428 | 75 | 80 | 85 | 90 | 98 |
| | | | | በስራ አፈፃፀም ውጤታማት የማቲጊያ ስርዓት ተጠቃሚ የሆነ የስራ ክፍልና የሰው ሀይል መጠን | 1 | 22 | 365 | 65 | 69 | 73 | 77 | 81 |
| | | | | ያደገ የሴቶች የአመራርነትና የውሳኔ ሰጭነት ተሳትፎ ዕድገት በቁጥር | 2 | 24 | 20 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 |
| | | | | በአሰራር ፍታዊነትና ግልፅኝነት የሠራተኛው እረካታ እድግት በመቶኛ | 2 | - | 20% | 60% | 65% | 70% | 75% | 80% |
| | | የተገባቦትና የገፅታ ግንባታ ማሳደግ | 6% | ግልፅኝነት የተሞላበት የመረጃ ሰርጭት ብዛት በቁጥር | 1 | 49 | 100 | 10 | 10 | 10 | 10 | 10 |
| | | | | ተግባራዊ የተደረገ የተቋም እሴት ግንባታ ብዛት በቁጥር | 2 | 5 | 10 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 |
| | | | | ከባለደርሻና አጋር አካላት ጋር የተፈረመ የመገባቢያ ሰነድ ብዛት በቁጥር | 2 | - | 9 | 3 | 3 | 3 | - | - |
| | | | | የተደራጀ የስፖርት መዝናኛ ክበባት ብዛት | 1 | - | 3 | 1 | 1 | 1 | - | - |
| | | የቴክኖሎጂ አቅም በማሳድግ የመረጃ አስተዳደር ሰርዓት ማሻሻል | 4% | በቴክኖሎጂ አጠቃቀም የክህሎት ስልጠና የተሰጣቸው የሰው ሀይል ቁጥር | 1 | 46 | 100 | 10 | 10 | 10 | 10 | 10 |
| | | | | የእንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና የዳታ ቤዝ አሰራር ተጠቃሚ ማ/ቤት ቁጥር | 1 | - | 3 | 1 | 1 | 1 | - | - |
| | | | | የቴክኖሎጂ ግብዓት አቅርቦት ያሟሉ ማ/ቤት ብዛት በቁጥር | 2 | 1 | 3 | 1 | 1 | - | - | 1 |

## 2.8. ስትራቴጂክ ግቦችን ለማሳካት ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች

1. የፖሊስ አባላት የአቅም ግንባታ ስልጠና
2. የአድስ ፖሊስ አባላት ቅጥርና ስልጠና
3. የአሶሳ ዞን የማስፋፍያ ግንባታ
4. የመተከል ዞን ማ/ቤት የማስፋፍያ ግንባታ
5. አዲስ  የቅርንጫፍ ማረ/ቤት ማዕከል ግንባታ /በመተከልና በአሶሳ/
6. የት/ት ደረጃ ማሳደግያ የማስፋፍያ ግንባታ
7. የአገልግሎት መሰጫ ማዕከላት እደሳትና ጥገና
8. አማራጭ የሃይል ምንጭ ግንባታ ባዮ ጋዝ
9. በዞን ማ/ቤቶች ላይ ሴፍቲ ታንከር ግንባታና የፍሣሽ ማስወገጃ መስመሮች ዝርጋታ
10. የታራሚዎች የመኝታ አገልግሎት ማሚያ
11. የዞን ማ/ቤቶች የልዩ ልዩ ሙያ ክህሎት ስልጠና ማዕከላት ግንባታ
12. የፖሊሰ አባለት የመኖሪያ ካምፕ ግንባታ
13. ዘመናዊ የኤሌክትርክና የማገዶ ቆጣቢ ምድጃ ማሰፋፊያ ዝርጋታ ግንባታ

## 2.9. በልማትፕላኑ ዘመኑ 2013 -2017 ዓ.ም በካፒታል ፕሮጅክት የሚሰሩ ስራዎችና ለስራው የሚያስፈልገው የበጀት ግምት

| ተ/ቁ | ነባር ፕሮጀክት | የፕሮጀክቱ ባለበት | ፕሮጀክቱ የሚካሄድበት ቦታ | የተጀመረበት | የሚጠናቀቅበት | የተመደበለት ካፒታል መጠን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የፖሊስ አባላት የአቅም ግንባታ ስልጠና | ቤ/ጉ/ማ/ቤቶች ኮሚሽን | በክልል ማ/ቤቶች | ከ2008 | እስከ 2022 | 8,000,000 |
| 2 | የአድስ ፖሊስ አባላት ቅጥርና ስልጠና | ቤ/ጉ/ማ/ቤቶች ኮሚሽን | በክልል ማ/ቤቶች | ከ2014 | 2022 | 14,238,000 |
| 3 | የአሶሳ ዞን ማ/ቤት ማስፋፍያ ግንባታ | ቤ/ጉ/ማ/ቤቶች ኮሚሽን | አሶሳ ዞን ማ/ቤት | 2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ | እስከ 2014 | 6,191,465.45 |

**ጠቅላላ ድምር 28,429,465.45**

| ተ/ቁ | በስትራቴጂክ ዘመኑ አድስ ወደ ትግበራ የሚገቡ ፕሮጅክቶች | የፕሮጀክቱ ባለበት | ፕሮጀክቱ የሚካሄድበት ቦታ | የሚጀመረበት | የሚጠናቀቅበት | የተመደበለት ካፒታል መጠን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የመደበኛ ት/ት የማስፋፍያ ግንባታ | ቤ/ጉ/ክ/መ/ማ/ቤቶች ኮሚሽን | በ3ቱ ዞን ማ/ቤትና በቀጣይ በሚገነቡ 2 የማ/ቤት ማዕከላት | 2014 | እስከ 2022 | 28,000,000 |
| 2 | የዞን ማ/ቤቶች የልዩ ልዩ ሙያ ክህሎት ስልጠና ማዕከላት ግንባታ የግብዓት ማሚያ | ቤ/ጉ/ክ/መ/ማ/ቤቶች ኮሚሽን | 3ቱ ዞን ማ/ቤትና በቀጣይ በሚገነቡ 2 የማ/ቤት ማዕከላት | 2014 | እስከ 2021 | 22,000,000 |
| 3 | አዲስ የቅርንጫፍ የማረ/ቤት ማዕከል ግንባታ | ቤ/ጉ/ክ/መ/ማ/ቤቶች ኮሚሽን | በአሶሳና በመተከል ዞን በተመረጡ ወረዳዎች | 2016 | አስከ 2022 | 25 ,000 ,000 |
| 4 | የአማራጭ ኃይል ግንባታ /ባዮ ጋዝ/ | ቤ/ጉ/ክ/መ/ማ/ቤቶች ኮሚሽን | በአሶሳ፤መተከልና ካማሽ ማ/ቤቶች | 2014 | 2017 | 12,000,000 |
| 5 | የታራሚዎች የመኝታና የአልባሳት አገልግሎት ማሚያ | ቤ/ጉ/ክ/መ/ማ/ቤቶች ኮሚሽን | በአሶሳ፤መተከልና ካማሽ ማ/ቤቶች | 2013 | አስከ 2022 | 30,000,000 |
| 6 | የማዕከላት ዕድሳትና ጥገና | ቤ/ጉ/ክ/መ/ማ/ቤቶች ኮሚሽን | በአሶሳ፤መተከልና ካማሽ ማ/ቤቶች | 2014 | እስከ 2022 | 12,000,000 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 7 | የፖሊስ አባለት የመኖሪያ ካምፕ ግንባታ | ቤ/ጉ/ክ/መ/ማ/ቤቶች ኮሚሽን | በአሶሳ፤መተከልና ካማሽ ማ/ቤቶች | 2017 | 2022 | 15,000,000 |
| **ጠቅላላ የካፒታል ፕሮጀክቱ ገንዘብ መጠን 144,000, 000** | | | | | | |

| ተ/ቁ | በጥናትና ዲዛይን ደረጃ ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች | የፕሮጀክቱ ባለቤት | የሚተገበርበት ቦታ | የሚጀመርበት ጊዜ | የሚጠናቀቅበት ጊዜ | የተመደበለት ካቲታል |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የመተከል ዞን ማ/ቤት የማስፋፍያ ግንባታ | ቤ/ጉ/ክ/መ/ማ/ቤቶች ኮሚሽን | መተከል ዞን ማ/ቤት | 2013 | 2015 | 7,000,000 |
| 2 | ዘመናዊ የኤሌክትርክና የማገዶ ቆጣብ ምድጃ ማስፋፍያ ዝርጋታና ግንባታ | ቤ/ጉ/ክ/መ/ማ/ቤቶች ኮሚሽን | በአሶሳ፤መተከልና ካማሽ ማ/ቤቶች | 2014 | እስከ 2017 | 2,500,000 |
| 3 | የዞን/ማ/ቤቶች የፈሣሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ላይ ሴፐቲ ታንከር ዝርጋታ | ቤ/ጉ/ክ/መ/ማ/ቤቶች ኮሚሽን | በአሶሳ፤መተከልናካማሽ ማ/ቤቶች | 2014 | 2017 | 7,000,000 |
| | **ጠቅላላ የካፒታል ፕሮጀክቱ ገንዘብ መጠን 16,500,000** | | | | | |

## 2.10. የልማት ፕላን የሠው ኃይል ፍላጎት በትምህርት ደረጃ /በሙያ መስክ

| የት/ት ደረጃ ሙያ መስክ | የ2012 መነሻ ዓመት | ትንቢያ | | | | | የ5 ዓመት ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | |
| በጤና 3ኛ ዲግሪ | - | - | - | - | 1 | 1 | 2 |
| በተፈጥሮ ሳይንስ 2ኛ ዲግሪ | | | | | | | |
| ማቲማትክስ | 1 | - | - | - | - | - | - |
| ሶሻል ሳይንስ 2ኛ ዲግሪ | | | | | | | |
| ሶሻል ፖሊሲ | 1 | - | - | - | - | - | - |
| ማነጅመንት | - | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 10 |
| አካውንቲግ | - | - | 1 | 1 | 1 | 1 | 4 |
| ፐብሊክ አደምስትሬሽን | - | 1 | | | 1 | | 2 |
| ኢኮኖሚክስ | - | - | - | - | - | - | - |
| በተፈጥሮ ሳይንስ የመጀመሪያ ዲግሪ | | | | | | | |
| ጤና | 3 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 5 |
| ስታስቲክስ | 1 | | 4 | | 4 | 3 | 11 |
| ግብርና | 7 | | 2 | 2 | - | - | 4 |
| ስነ- አኢምሮ | - | | - | - | - | - | - |
| ተክስታይል ኢ/ር | - | | 3 | | | | 3 |
| ኮምፒዩተርሳይንስ/አይሲቲ/ | 1 | 3 | - | - | - | - | 3 |
| በማህበረሰብ ሳይንስ | | | | | | | |
| ህግ | 2 | 1 | 1 | 1 | 1 | - | 4 |
| ሳይኮሎጅ | 4 | 3 | | 3 | - | - | 6 |
| ማኔጅመንት | 26 | 8 | 7 | 1 | 5 | 4 | 25 |
| አካውንቲግ | 14 | 3 | - | 8 | - | - | 11 |
| ፖሊስ ሳይንስ | - | - | 2 | - | 2 | - | 4 |
| ሶሾሎጅ | 1 | - | - | 1 | - | 2 | 3 |
| ኢኮኖሚክስ | - | | 2 | 2 | 2 | 1 | 7 |
| በቋንቋ | 2 | | 2 | 1 | 1 | - | 4 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **በተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ ዲፕሎማ** | | | | | | | |
| ነርስ | 12 | | 3 | 5 | - | - | **8** |
| ላብራቶሪ ቴክኒሻን | 6 | - | - | 1 | 1 | - | **2** |
| ፋርማሲስት | 6 | - | 3 | - | - | 1 | **4** |
| ግብርና | 4 | - | - | 3 | - | 4 | **7** |
| ኮንስትራክሽን | 3 | - | - | 1 | 1 | - | **2** |
| አይሲቲ | - | 2 | | 2 | | | **4** |
| ጋርመንት | - | - | 3 | - | - | - | **3** |
| ኤለክትሪክ ሲቲ | - | 3 | - | - | - | - | **3** |
| ቧንቧ ሰራተኛ | 2 | - | 1 | - | - | - | **1** |
| ውድ ወርክ/እንጨት ስራ | - | - | 3 | | | | **3** |
| የብረታ ብረት ስራ | - | | 3 | | | | **3** |
| የሴቶች ውበት ሳሎን/ስራ/ | - | - | 3 | - | - | - | **3** |
| **በማህበራዊ ሳይንስ ዲፕሎማ** | | | | | | | |
| ማኔጅመንት | 30 | 4 | 4 | 4 | 4 | 1 | **17** |
| አካውንቲግ | 38 | | 2 | - | - | - | **2** |
| ፖሊስ ሳይንስ | 3 | 8 | - | - | - | 10 | **18** |
| ፅህፈት ቢሮ አስተዳደር | 14 | 6 | 4 | - | 4 | 2 | **16** |
| ፐርቼዝንግ | 1 | 5 | 2 | 2 | - | - | **9** |
| **በቴክኒክና ሙያ /በደረጃ የሰለጠኑ/** | | | | | | | |
| ደረጃ /level | 53 | - | 32 | - | 10 | | **42** |
| ደረጃ /level 3 | 10 | - | - | - | - | - | **-** |
| ደረጃ /level 1 | 7 | 25 | 25 | 22 | 7 | 27 | **106** |
| ✓ ከ9-12ኛ ክፍል | 230 | - | 200 | - | 200 | - | **400** |
| ✓ ከ7ኛ-8ኛ ክፍል | 37 | - | - | - | - | - | **-** |
| ✓ ከ4ኛ-6ኛ ክፍል | 7 | **-** | **-** | **-** | **-** | **-** | **-** |
| **ጠ/ድምር** | 526 | **75** | **315** | **63** | **248** | **60** | **761** |

# 3. ክፍል-ሦስት

## 3.1. የክትትል ፣ ግምገማና ግብረ- መልስ ሥርዓት

የዕቅድ ክትትል፣ ግምገማና ግብረ-መልስ ሥርዓት ዓላማው ዕቅዱ በተያዘለት ጊዜ፣ የሰው ኃይል ፣ በጀትና ቁሳቁስ ተቀናጅቶ እየተከናወነ መሆኑን በመከታተልና ክፍተቶችን በመፈተሸወቅታዊ ማስተካካያ እርምጃ ለመውሰድ እንዲያስችል እንዲሁም በአቅድ አፈፃፀም የሚሳተፉ ባለድርሻ አካላትም ስለሁኔታው አውቀው ተገቢውን ማስተካከያ እንዲያደርጉ ግብረ-መልስ መስጠት ማስቻል ነው፡፡ በመሆኑም የዕቅዱ አፈፃፀም የክትትል፣ ግምገማና ግብረ-መልስ ሥርዓት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 3.1.1. ስትራቴጂውን በማስተዋወቅ ወደ ትግበራ መግባት

- የተቋሙን ስትራቴጂክ እቅዱን ከተገልጋይ ማህበርሰብ ፣ ከባለድርሽና ተባባሪ አካላት፣ከህዝብ ክንፍ ፣ አባላትና ሰራተኞች ጋር የጋራ ግንዛቤ መፍጠር ፣
- ለአመራሩ፣ለአባላቱ፣ለፈፃሚውና ለባለድርሻ አካላት ማስረፅና ድርሻቸውን እንዲወጡ ለማድረግ መነሳሳትን መፍጠር፣
- ስትራቴጂክ ዕቅዱን በየአምስት አመትና በየአመቱ በስራ ሂደቶች (የትኩረት መስኮች ) ለይቶ በማዘጋጀት መተግበር፣
- ጠንካራ የምዘና ስርዓት መቅረፅና በመተግበር፣ በየበጀት አመቱ ማጠቃለያ እውቅናና ማበራተቻ ስርዓት (የማቲጊያ) ተግባራዊ ማድረግ፣
- ስትራቴጂውን አፈፃፀም ለመከታተል፣ ለመገምገም፣ለሪፖርትምና ግብረ-መልስ ለመስጠት የመረጃ አያያዝ ስርዓት በማሻሻል በዓመት ፣ በየሁለት አመት ተኩልና በየአምስት አመት የተጠቃለያ ሪፖርት ማዘጋጀትና ለቀጣይ የዕቅድ አፈፃፀም በግብአትነት በመጠቀም፣ የስትራቴጂክ ዕቅዱ አፈፃፀም ራዕዩንና ስትራተጂያዊ ግቦቹን ማሳካቱን በመገምገም እንደ አስፈሊጊነቱ ዕቅዱን የሚከለስ ይሆናል፡፡

### 3.1.2. በዳይሬክቶሬት ደረጃ የሚደረግ የክትትል ድጋፍና ግምገማ አግባብ፣

- በየዘርፉና በማዕከላት ድረጃ በየሳምንቱ የስራ ግምገማ ያደርጋሉ የመረጃ ልውውጥ ግን በየቀኑ ይከናወናል፡፡ሁሉም ማዕከላት በየቀኑ ለዋናው መ/ቤት የስልክ ሪፖርት ያደርጋሉ፡፡

- የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች የ1ኛ ሩብ ዓመት ፣የ6 ወር ፣ የ9 ወር እና የአመቱ ማጠቃለያ ሪፖርቶች በመመሪያው ፣በፎረማትና በዕቀዱ መሠረት የሚቀርብ ይሆናል፡፡
- በአመት አራት ጊዜ ሁሉም የአመራር፣አባላትና ሠራተኛውበተገኙበት መድረክ በክልልና በዞን ማ/ቤቶች ደረጃ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ግምገማ ይካሄዳል፡፡
- የተቋሙ የሶስት ፣የስድስትና የዘጠኝ ወራትና አመታዊ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ሩብ አመቱ ከተጠናቀቀ በኋላ በመጨርሻው የሩብ ዓመቱ ሳምንትለገ/ኢ/ል/ቢሮ፣ለክልል ም/ቤት፣ለክልል መሰ/ም/ቤት እና ለሰላም ግንባታና ፀጥታ ቢሮይቀርባል፡፡
- የተቋሙ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች አፈፃፀም በመሰረታዊ ፍላጎት ዘርፍና በተሃድሶ ዘርፍ ደረጃ በአሰራ አምሰት ቀን ክትትል ሲደረግ አመራሩ በየወሩና በየሩብ ዓመቱ ግምገማ ያደረጋል፡፡
- የማ/ቤቶች ኮሚሽን፣የዞን ማረ/ቤቶች መምሪያ ፣ ከባለድርሻና ተባባሪ አካላት እናከህዝብ ክንፍ ተወካዩች የጋራ ምክክር ጉባዔ በየስድስት ወሩ ይካሄዳል፤ በወይይት መደረኩ የሁሉም ዞን ማ/ቤቶችናየኮሚሽኑ ኃላፊዎች በተገኙበት በዋና ዋና ጉዳዮችና በተቋማዊ ለውጡ የ6 ወራትና የየዓመቱ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች ያቀርባሉ፤ ይገመገማሉ ፤በተገኙ ውጤቶች ፣ባጋጠሙ ችግሮችና ዕጥረቶች፤የጋራ አሰራርና የጋራ ውሳኔ በሚሹ ጉዳዮች ላይ በመወያየት የልምድ ልውውጥ ያደርጋል፡፡
- የዞን ማ/ቤቶች በወር 1 ጊዜ የክልል ማ/ቤቶች የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች በ3 ወር 1 ጊዜ ከተጋልጋይ አካላት ጋር ቋሚ የውይይት መድረኮች በማዘጋጀት በተቋማዊ አገልግሎት አሰጣት የስራ አፈፃፀም ዙርያ ውይይቶችን ያደረጋሉ በውይይት ሂደቱ ለሚነሱ ቅረታዎች የማስተካከያ ስርዓት በማስቀመጥ ችግሮቹ እንድፈቱ ይደረጋል፡፡

### 3.1.3. የመስክ ክትትልና ግምገማ

- ኮሚሽን በተደራጀ መልኩ በአመት አራት ጊዜ በየዘርፉ ለዞን ማ/ቤት መምሪያድጋፍ ይሰጣል፡፡
- በየዘርፉ ያሉ ሙያተኞች በየሩብ ዓመቱ በቼክ ሊስት መሠረት ድጋፍ ማድረግ ፤
- በዞን ማ/ቤት ማዕከላት የሚካሄዱ ሥራዎች የዕቅድ አፈጻጸም ሂደትን የሱፐርቪዥን፤ የክትትልና ድጋፍ ሥራ በየሩብ ዓመቱ በዓመት አራት ጊዜ ይደረጋል፣
- በመስክ ድጋፍና በግምገማ ሪፖርቶች በሚገኙ ምርጥ ተሞክሮዎች፤ ድክመቶች የማስተካከያ እርምጃዎችና ያከተቱ ግብረ-መልሶች ይሰጣሉ ፡፡

## 3.2. በስትራቴጂክ ዘመኑ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና

### 3.2.1. ለችግሮቹ የተቀመጡ የመፍተሄ ሀሳቦች

#### 3.2.1.1. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች፡-

- የሎጀስትክ ፣ የግብዓትና የበጀት አቅርቦት ውስንነት
- ለታራሚዎች አገልግሎት የሚውሉ የመሰረተ ልማት አቅርቦት የገበያ አለመረጋጋት ችግር መኖር
- የሰው ሃይል መጠን ፣የሙያ ብቃት ማነስ ፣ የስነ- ምግባር ችግር መኖር በማረም ማነፅ ውጤታማነት ላይ ጫና ማሳደር
- ከውስጣዊና ዉጫዊ ፀጥታ ስጋቶች መኖርና ከዚያጋር ተያይዞ የታራሚ ቁጥር መጨመር
- በሀገር ደረጃ የተከሰተ የኮሮና ቨይረስ ወረርሽን
- ከባለድርሻ ፣ አጋርና ተባባር አካላት ጋር ተቀናጅቶ የመስራት ክፍተት መኖር

#### 3.2.1.2. ለችግሮቹ የተቀመጡ የመፍተሄ ሀሳቦች፡-

- የተቋም ተልዕኮ ስኬት ቀጣይነት ማረጋገጥ የሚያስችሉ የሎጀስትክ የግብዓት አቅርቦት ማሟላት የሚያስችሉ ፍትሃዊ የሀብት አመዳደብ እንድኖር መንግስትን በማሳመን ተፈፃሚ እንድሆን ማድረግ
- በማ/ቤት ያለውን ሰፊየሰው ኃይል አቅም ለልማታዊ ተግባራት ተግባራት በመጠቀምበውስጣዊ አቅም የኑሮና የገበያ ጫና መቀነስ የሚያስችሉ አሰራሮችን ተግባራዊ ማድረግ
- ተቋማዊ የስራ ባህል የአቅም  መገንብያ፣የማትጊያ ስትራቴጂ መንደፍንመተግበር
- ወጫዊ የፀጥታ ስጋቶች ወደ ማ/ቤት እንዳይዘመቱ የማ/ቤቶት ሰላምና ደህንነትን ማረጋገጥ እና የወንጀል ተግባራት ከማ/ቤቱ የሚወጡ ታራሚዎች  በወንጀል ተግባር ላይ በመሰማራት ለወንጀል መፍፋፋትን አስተዋፆ እንዳያበረክቱ የማምረም ማነፅ ውጤታማነትን በማረጋገጥ ለወንጀል መከላከል ስራ ተቋማዊ አስተዋፆ  ማበርከት
- ማ/ቤቶች ለኮሮና ቫይረስ መስፋፋት ተጋላጭ ሊሆኑ ከሚችሉ ተቋማት አንዱ እንደ መሆኑ መጠን የበሽታውን ተጋላጭነት መቀነስ የሚያስችሉ አሰራሮችን በመዘርጋትና የክትትል ስርዓትን የማጠናከር ስራዎችን ተግባራዊ ማድረግ
- የተቋሙ አመራር እስከ ባለድርሻና አጋር አካላት ጤናማ የስራ ትብብርና ቅንጅት መፍጠር የሚያስችሉ አሰራሮችን በመዘርጋት ስራዎችን በጋራ መምራት